


t.me/OLDBOOKSPDF

# ኩርቢት



ዓለማየሁ ገላጋይ

ሰኔ 2004ዓ.ም



t.me/OLDBOOKSPDF

© የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

አንደኛ እትም ፡ ሰኔ 2004ዓ.ም

ለአስተያየትዎ ፖ. ሳ. ቁ. 70491 አ/አ

## የደራሲው ቀደምት ስራዎች

- ✓ አጥቢያ
- ✓ ቅበላ
- ✓ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት

t.me/OLDBOOKSPDF

# ማውጫ


1. ዘናባቢል........................................ 5
2. ገሃነሙ ሰውጥ........................................ 11
3. እንቁራሪት........................................ 13
4. ቅሌባን........................................ 19
5. ሙትና ሐውልት........................................ 25
6. የቦና እናት........................................ 31
7. ሚሊኑሰብለ ወእንስሳት........................................ 37
8. ኩርቢታ........................................ 45
9. ጨርቆሱን ጥበታ........................................ 73
10. ያውሰታ ቀስተደመና........................................ 77
11. ከወደ ጠጅ ቤት........................................ 81
12. አንድ ለእናቱ........................................ 97
13. ባሻ ወኔ........................................ 111
14. ፈረጃ........................................ 123


t.me/OLDBOOKSPDF

# ዘሩባቤል

"ነፍስ ይዋደቃል!" ነው የሚለው የከሩ ልብ። ወደ ጠጅ ቤቱ ሲያመራ…

"ኳ! ኳ! ኳ!... ጠጅ!"

ደንበኞች በጊዜ ተሰይመዋል። ሁሉም የአንድ ሰው ልጆች ይመስላሉ። ጥሌታቸው ተመሳሳይነት አለው። ምስቅልቅል ያለ ፊት፣ የሞት ንብረትነት ፅላሎት። ሞት የሚልሰው'ንጂ ጨርሶ የማይጎረሰው ገላ፣ ለማዳዎቹ ናቸው ለሞት። ያመልጡኛል ሳይል፣ ሳይጠራጠር እንዲቃርሙ ይለቃቸዋል። ዞረው ዞረው እነው ታዛ ሥር ይሰበሰባሉ። ሞት በባለቤትነቱ ኮርቶ ቆቅ ቆቁን ለማጥ፣ወድ ወደ ዱር ይወርዳል። እነዚህ ተቀማጮቹ ናቸው ቢፈልጋቸውማ በአንድ ምሽት ይጠራርጋቸውም አልነበር?... የከፉ ጊዜው ናቸው ሲያጣ።

"ኪ! ኪ! ኪ!... ና ወዲህ!"

እነዚህ የአንድ እጅ ዝሪቶች ይፎክራሉ። በልባቸው... የሞት አሽከር! ከሞት ጋር ውሎ ከሞት የሚያድር። ሞትን ታክው፣ ተሻሽተው ተላምደውታል። ሞት መሃሪያቸው ሆኗል፣ ተቆጥቶ ይተዋቸዋል። ታማኛቸውም ነው። ወስዶ ይመልሳቸዋል።

"ነፍስ ይዋደቃል" ነው የሚለው የከሩ ልብ።

ከሩ ውርደት ሲበዛበት ከሞት ጋር ፊት ለፊት ይገጥማል... ብዙ ጊዜ የሞት እጅ የሆነው ደቦጭን ይሰድበዋል። ደቦጭ ግን በበላይ አለቃው በሞት ይመከራል። ደቦጭ ሰበብ እያጣም "ናቅኩህ" ይልና በማላገጫ ምላሱ እየላሰ ያሚሚዋል።

"ኪ! ኪ! ኪ!... ድገም!!"

ከሩ የደቦጭ ንቀት ከሞት ገዝፎ ይታየዋል። ፍጭርጭር ያደርገዋል። ደቦጭ ደግሞ በክረታም እጁ እንደ ልጅ ይኮረኩመውና ይስቃል። አለበለዚያም ጆሮውን ይዞ ያንጠራራዋል። የጉረቤት ሴቶች ይስቃሉ።

አንዳንዴ አምሽተው ከተገናኙ... ጥላውን ይጠልበትና

"እንደ ወንዶቹ አምሽተሽ መግባትሽ ነው?" ይለዋል። ከሩ እንጀቱ ይንፈጨፈጫል "እ-ሃ ሥጋም" ተደበልኛል? የኛ ባለሚስት" የማብሽቂያ ሳቅ አለው። ደቦጭ ለሌሎች ቢሆን ምህረት የለውም። ከሩን ግን...

ከሩ ወደ ቤቱ ሲገባ በመግባቱ ሲናደድ፣ ሚስቱን "ምናባሽ!" ይላታል። ዝም ስላለችው ይበሳጫል፣ ደሞ ቀስስተኛ ነች። የምትፈጥነው ሽንኩርት ስትከትፍ ብቻ ነው። ስትራመድ ከተመለከታት ጨረቃ ላይ የሚኖር ይመስለዋል። የሚያመልጣት ዕቃ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንኳን ቀስ እያለ ነው ከእጁ ላይ ወድቆ የሚሰበረው፡፡ የእነሷ ግዝፈት እግዚአብሔር ቸሩ አምላካችን የተባለው ለሷ አካል ሥጋ በገፍ በማሸከሙ ሳይሆን አይቀርም" እያለ ያስባል፡፡

በቃ ንዴት... ንዴት ብቻ ይሆናል፤ ዱላ ይጀምራል የንዴት ትኩሳቱን ማብረጃ፡፡ እንድትሮጥ ቢፈልግም "እህ እህ" እያለች የክፍሉን ጥግ ትዞራለች፡፡ እጁን ያከርና ተንጠራርቶ የሚደርስበትን ጀርባዋን ይደልቀዋል፡፡ ሲደክመው ዝቅ ብሎ ጭኗ ላይ ይወርድባታል፡፡ ጥጃዋን አላጠባም እንዳለች ላም ከሩን ከስርዋ አስከትላ ያገኘችውን ዕቃ ታተረማምሰዋለች፡፡

"ኪ! ኪ! ኪ!... የዛሬ ጠጅ ምንድነው?"

የባልና ሚስቱ ገላጋይ ደቦጭ ነው፡፡

"በቃ! የምን ጉረቤት መበጥበጥ ነው? ደክሞን አንተኛበትም?" ካለ በኋላ ሚዶ የመሰለ ጥርሱን እያሳየ ነገር ለማብረድ ሴቷን ወስዶ እሱጋ ያሳድራታል፡፡ በሌሊት አምጥቶ ቢያስታርቃቸውም የጎረቤት ሴቶች ነገሩን ይደርሱበታል - ይስቃሉ፡፡

ከሩ ነገር ያከራል

የጉረቤቱ ሴቶች "ኢዲያ ነገር አታክር!" ይሉታል - ይንቁታል፡፡

አንድ ቀን ቢመረው፡-

"ና ይጥባልን" አለው ደቦጭን፡፡ ምሥቅልቅል ፊት ያላቸው የጠጅ ቤቱ ደንበኞች ድንግጥ አሉ-በጥ፡፡ ደቦጭ ግን ሆዱን ይዞ ተንፈቀፈቀ፡፡

"ምኑን ጉልበተኛ አያችሁት?" ሲል አፉን ከፍቶ ሳቀ፡፡ ከሩ የደቦጭ ላንቃ ይታየዋል፤ ባይታየው ኖሮ ይመኛል... ጥቁር ላንቃ አለቀያማ፡፡ የአንድ እጅ ዝሬቶቹ፤ ቡቱቶ ፊቶች ሳይፈልጉም ቢሆን ደቦጭን ከላት ያቅዶቁ ያጅቡታል፡፡ ንጉሳቸውን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያች ቀን ጀምሮ "የኔ ጉልበተኛ" እያለ ነው ክሩን የሚጠራው። የክሩ አስቂኝነት ይበልጥ ጉላ፤ ይኼንን የሰማ ሳይንፈቀፈቅ አያልፍም።

የሰፈሩ ሴቶች

"እይ ክሩ ብትወድቅበትም ቢጠድቅብህም ትሞታለህ" ይሉታል።

"ዋናው ልብ ነው" ይላል ክሩ የሚሰማው ጆሮ ቢያጣም "ደቦጭ ፈሪ ነው!" ሴቶቹ ወሬ ያገኛሉ - ለደቦጭ።

"ካ! ካ! ካ!... ቅዳ!!"

ትናንት ማታ... ደቦጭ ከሞት እጅ የክሩ አባባል በሴቶች ተግለብላቢ ምላስ ቢራገብለት ተበሳጭቶ እንደ ላስቲክ ወተት እንገቱን በጥሶ ደሙን እንደሚጠጣው ለሴቶቹ ምሏል።

"ነፍስ ይዋደቃል!" ነው የሚለው የክሩ ልብ።

ክሩ ወደ ጠጅ ቤቱ ሲገባ ሞት የቀማመሳቸው ፊቶች በመደነቅ ነበር የተመለከቱት። አሁን ግን ድንጋጤው ለቋቸው የየግል ወሬያቸውን ይዘዋል። ክሩም አምስተኛ ጠጁ ላይ ጉብ ብሏል። አጠገቡ ያሉት ቂስ ጆሮውን አፋቸው ላይ ለደቀነው ሞት ያንሾካሹካሉ። እዚያ ማዶ "አትወራጭ!" ይላል የፊት ጥርስ የሌለው ጡረታ የወጣ አስተማሪ።

"አትወራጭ! እደግመዋለሁ፣ አትወራጭ!"

· ክሩ ወደ ደቦጭ ቦታ ለአስረኛ ጊዜ አይኑን ጣል አደረገ - ክፍት ነው። ባለመደገፊያ ሣር የተጉዘጎዘበት ዙፋን። ፊት ለፊቱ ነጭ ሸንኩርት የተከደነች ብርሌ ጠጅ ተሞልታለች። ደቦጭ ወደ ጠጅ ቤቱ ከመምጣቱ በፊት ነው ነጭ ሸንኩርቱን ለጠጅ ቀጂው የሚልከው። ተቀድቶ ያቺ ነጭ ሸንኩርት ተከድና ትጠብቀዋለች - አይቀርም



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲመጣ ጠጁ ነጭ ሽንኩርት ተከድኖ ካልጠበቀው ቤቱን ያምለዋል - ተናቅሁ ይላል።

"አትወራጭ! እደግመዋለሁ - አትወራጭ!"

"ዝም በል!" ደቦጭ ገባ። ጡረታ የወጣውን አስተማሪ አይወደውም። የፊት ጥርሶቹን አንድ አንድ እያለ የጨረሳቸው እሱው ነው።

ጡረታ የወጣው አስተማሪ በደቦጭ እጅ ከሞት ጋር ለደቂቃዎች መተሻሸት ስልችቶታል። እህሉ እንደ ተራገፈ ጆንያ ጭርምትምት ብሎ ጥጉን ያዘ። የአንድ ሰው እጅ የዘራቸው ፈቶች ከደቦጭ ወደ ክሩ የሚያመሳልስ የዓይን ሐዲድ ሰርተው ይንሸራሸሩ ገቡ።

ክሩ አጠገብ ያሉት ቄስ የሞት ቅኔ ለሞት ጆሮ ይቀኛሉ...

"የወደቀ ምን ይሆናል፣ አባ?" አላቸው ክሩ

"ይወደሳል - ልጄ" አሉት በልጉምጉምታ

"የጣለስ?"

"ጠዋት ቢሆን ይወቀሳል..." ወደ ደቦጭ እያዩ

"የሞተስ?"

"ዛሬ ሐሙስ አይደል? የዓርብ አፈር የት ተገኝቶ" ቀና ብሎ ወደ ደቦጭ ተመለከተ። ደቦጭ በአንድ ሰው እጅ በተዘሩት ዓይኖቹ ምሪት ክሩን ተመልክቶ ኖሯል። እንደሌላው ቀን ማላገጫ አላደረገውም። "የኔ ጉልበተኛ" ብሎ በሚያደ ጥርሱ አልሳቀም። ፊቱ እንደደፈረሰ "አገኘሁሽ አንቺ ዶሮ" አለና ብድግ አለ።

ክሩ ዙሪያውን ቃኘ። ቄሱ ከአጠገቡ ከነብርሌያቸው ተነስተው ሾታ ቀየሩ። ኩራት ለክሩ ተሰማው... ደቦጭን የመግጠም ኩራቱን ኮርቶ ሳይጨርስ ለሰልፍ ተነሳሳ። ደቦጭ የብርሌ ጠረጴዛውን አግዳሚ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሻገር ብሎ ወደ ክሩ አመራ። ክሩ በብርሃን ፍጥነት ጠጅ የያዘች ብርሌውን አንስቶ ወረወራት።

የአንድ እጅ ዝራዮቹ በብርሌዋ አየር ላይ መዘግየት ተገረሙ... የብርሌዋ ጉዞ ቀጠለ... ግልብጥ፣ ድብልቅ፣ ፍንጥቅ... እያለች የአየር ላይ ጉዞዋን በደብሟ ሰፊ ግንባር ተገድባ አቋረጠች። ደብልቅልቅታ።

ሞት ያቦጭን እንደሊያሾ ተማምሶ ሊመልሰው አልፈቀደም።

ቃሉ "አን ተራራ በዘሩባቤል ፊት ምንድነህ - ደልዳላ መሬት ትሆናለህ" ሲሉ ለሞት ጆሮ ሹክ አሉ።

"አትወራጭ!"



t.me/OLDBOOKSPDF

# ዝግመተ ሰውኛ

"እንጋባ" ሲል ጠየቃት፣ አሳምነው።

አልተቀበለችውም አስማሩ። "ወንድምና እህትነት ይበልጣል" አለችው።

ተስማማ።

ቤቷ እየመጣ ይጠይቃታል።

ቡና ታፈላለች ይጠጣሉ፣ ካላት ታቀርባለች - ይበላሉ።

አውግተው ይለያያሉ።

የትዳር ነገር ዳግም አልተነሳም።

አሳምነው አንድ ቀን በጠራራ ፀሐይ መጣ።

እንደመጣ የደረበውን ሹራብ አውልቆ አስቀመጠ። ስለሙቀቱ ብዙ አውርተው ተለያዩ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አስማሩ አሳምነው እረስቶት የሄደውን ሹራብ ልብሷን ስታጥብ አጠበችለት።

ዳግም ሲመጣ ደርቦ ደራርቦ ነበርና የሚያወልቀው እንጂ የሚደርበው ልብስ አላስፈለገውም።

ጃኬቱን አውልቆ ሄደ።

አስማሩ እሱንም አጥባ አኖረችው።

ሱሪውን ደርቦ መጣ "ወበቀኝ!" አወለቀው።

አስማሩ አጥባ አኖረችው፣

ካፖርቱን ጥሎ ሄደ፣

አጥባ አኖረችው።

አንድ ቀን በጠራራ ፀሐይ ብርድ ልብሱን ለብሶ መጣ፣

አስማሩ "ምነው?" አለችው።

"በጠራራ ፀሐይ ብርድ ሆዴ ገባ" አላት።

"ምች ይሆናል" አለችው። የምች መድኃኒት ብታሽለት ተሻለው።

ሲሻለው ብርድ ልብሱ አላስፈለገውም ጥሎት ሄደ።

አስማሩ አጥባ አኖረችው።

ትንሽ ቆይቶ፣ ፍራሹን ተሸክሞ መጣ።

"ምነው?" አለችው።

"ላሳድሰው መሄዴ ነው። አይቼሽ ልለፍ ብዬ ነው" አላት።

አመነችው።

ጨዋታው ደራ፣ ፍራሹን እረስቶት ሄዶ ኖሮ እኩለ ሌሊት ቢመጣ አስማሩ ቦታ ስላጣች ፍራሹን ፍራሿ ላይ ደርባው ደረሰ። ያኔ "ተነሽ" ከማለት "ጠጋ በይ" ማለት ቀልሎ ተገኘ።

ጠጋ አለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

# እንቁራሪቱ

ጨረቃ ሰፊ አፍ የገመጣት ሻጋታ ሸልጦ መስላለች፡፡ ከአዘቅት የተረፈ ሩብ ገላዋ የሚያነባው ብርሃን ደሳሳዋ ጎጆ ላይ ያካፋል፡፡ ምናልባትም የተደቀደቀው የጎጆዋ ጣሪያ እንደ ምንጭ ውሃ የተንዠለለውን ብርሃን በባለቤቷ ላይ ያንጠባጥብ ይሆናል፡፡ መከራና ውርደት በአስረሽ ምቺው ተዳርተው የፀነሱት የቤቱ ባለቤት ጎስቋላ ገላ ፊቱ ላይ ተደቀነ፡፡ ይህም ሆኖ እርምጃዬ አልተገታም ነበር፡፡

ወደዚያች ጎጆ የማመራው የራሴ አማጭ ሆኜ ነው፡፡ እንደሚገርምህ አልጠራጠርም፡፡ እጅጉን አብዝቶ ይግረምህና ይቺ የማጫት ባልቴት እድሜዋ 47፣ 48፣ 49፣ 50፣ 51፣ 52፣ 53፣ 54... ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነው ነው፡፡ "ታዲያ ለምን?" በሚል ጉዳዩን እንደራስህ ጉዳይ አይተህ እንደምትብከነከን አልጠራጠርም፡፡ እጅጉን አብዝተህ ትብከበከን ዘንድ በዚህ ሰዓት ከጀርባዬ ሆኖ



t.me/OLDBOOKSPDF

የማይታየኝን ትዳሬን ከነልጁ ጣጥዬ ወደዚች ጎጆ እንደማመራ እነግርሃለሁ።

«ጡረው፣ ጡረው አማጭህን
ጡረው አማጭህን፤» ማን እንደሚዘፍን እንጃ…

ከስምንት አመት በፊት በብቸኝነት ክርታስ የተሸከፈ ህይወት ነበረኝ። ያ ሕይወት የሆነለውን ተስፋ አምልዤ እየተሳለምኩ በብህትውና ስኖር… አንዲት ፍዝ ፊት ያላት ሴት ታዛዬን መጥኚ አለች። ሴቶች እንደውሻ በጠረናቸው አካባቢን እንደሚገዙ ያወኩት ያኔ ነው። ሆን ብላ ሀገሯን… ሆን ብላ ሽቶዋን… ሆን ብላ… ሆን ብላ።

ወንዶች እንደ እየሱስ ክርስቶስ መጥፊያችን ለዘላለሙ ምልክታችን ይሆናል። ገራምነቷ ያለኝን መጥፎ ነገር ሁሉ ውጦ ቅምም ሳይለው ፍዝ ፊቷ በብቸኝነት ጎጆዬ ውስጥ ድንግዝግዝ ብርሃን ወለደ። ትግል ላይ ነበርን። እኔ በጥንካሬዬ እሷ በደካማነቷ። እቆጣለሁ… ታለቅሳለች፣ እማታለሁ… ትለማመጣለች።

ብርሃን በጭለማ፣ ጭለማም በብርሃን ላይ እንዲሰለጥኑ ባለትዳሮችም እንዲሁ እንዲያደርጉ አወቅሁ። በተለይ ሴቶች በወንዶች ላይ ያደፈጡ አዳኞች ናቸው። ባል ያሉትን እውሬ ካደፈጡበት ሳይንቀሳቀሱ አዘናግተው ይጥሉታል። እተጠራጠር ያ እውሬ ካለመንቀሳቀሱ ፍፁምነት ግቶ ነው ብሎ በደመደመው አዳኝ ቀስቱ ይወድቃል።

ስቶጣ እንድ የነበረው ለቅሶ መንታ ሆነ… ስማታ ነጠላ የነበረው ልምምጥ ጥንድ ሆነ። ጎጆዬ ከበኩር ልጇ ከኔ በተጨማሪ የመንታ ባዕዳን ፅንሶች መጠለያ ማህፀን ሆነች። እና ቁጣዬ ለመንታ ለቅሶ… ዱላዬ ለጥንድ ልምምጥ ተረትቶ እጁን ሰጠ።

ንፋስ ከዛፍ ቅርንጫፎች ጋር ስረያ በያዘበት አንዲት ምሽት፣ በረንዳውን መጥኚ እንዳልኩ፣ ፍዝ ፊት ፊቱን ተሳልሞ ቆመ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"እስሜ" አለችኝ "አለማማው" ብትሉኝ ምናል?

"እ?"

"ምን ሆነሃል?"

"ደስ ብሎኛል መሰል..."

"እሱን አይደለም"

"እንግዲያስ?"

"ሌሊት ቤተሰቡን መበጥበጥ ከጀመርክ ለነባበትክ"

መጀመሪያ አልገባኝም ነበር። ዞር ብዬ ባለቤቴን አየኋት። የበረንዳው መብራትና ጨረቃ ግራ ፊቷ ላይ ድሪያ ይዘዋል። ቀኝ ፊቷ እንደ ጨረቃዋ ግራ ጎን የጭለማ አበቅት ወርዷል። ማስጥሩን ስረዳ ተሸማቀ ያፈገፈገ ትክሻዬ እስከ ዛሬ ሳይመለስ ቀረ። የጨመተው የባለቤቴ ድምፅ ድክመቴን እየተመገበ በኔ ላይ ሲሰለጥን ይታወቀኝ ነበር።

"እንደ እንቁራሪት ሲያንቋርሩ ማደሩን ተወው!"

ሌላ ጊዜ...

"እንደ ሌሊት ነፍሳት ማንጫረሩ ይብቃህ!"

ምን አፍ አለኝ?? አህያውን ስለ ፈራሁ ፈጣሪዬን ተሟገትሁ...

"ጥፋቱ ያንተ ነው። ሰው አድርገህ ፈጥረኸኝ፤ ሰው ነው ብለው የተዋለዱኝ ቤተሰቦቼ የሌሊት ነፍሳት ሆኜ ሲያገኙኝ መላመዱ ተሳናቸው። ባዕድ የሌሊት ድምፅ ነፍሳቸውን በዘበዘው። እኔ ተኝቼ ባደርኩ ቁጥር እንቅልፍ ያጣ መንታ ፊት በዝምታ አቤቱታውን ያወርዳል... አንዳንድ ጊዜ ልጄ ቀን እንቅልፍ ስለሚጥላት ከትምህርቷ ትስተጓጎላለች። ይሄ ሁሉ ያንተ ጥፋት ነው"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዛሬ የሲሲዩ (ልጅ ናት) መምህር ጠርተው ልጃችሁ ክፍል ውስጥ ታንቀላፋለች አሉኝ..." ትለኛለች ባለቤቴ... ምን እፍ አለኝ?? አህያውን ስለፈራሁ ፈጣሪዬን ተማገትሁ

"ስለ ምን ልጅ ሰጠኸኝ?"

እግዚአብሔር ዝም!

ልጆች በውደታ እራስህን መሰዊያቸው ላይ የምታኖርላቸው አጉል አምልኮዎች ናቸው። እግዚአብሔር አብርሃምን ስለልጁ መሰናክልነት መፈተኑ ይህንን ስለጠረጠረ ነበር። የአብርሃም አባትነት በእግዚአብሔር ላይ ቢያገድር ኖሮ? ይሄ ሁሉ የልጅ ጭንቃችን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ባገኘ ነበር... ጣኦቶቻችን ከአብራኮቻችን ዙፋን ተቀምጠው ሳለ "ለራስህ ምስልን አታብጅ" ባላለን ነበር... የነፃነት ክንፋችን ባልተሰበረ ነበር...

...ልጅ በተወለደ ማግስት ክንፍህ መሰበሩ አይደለም ቁም ነገሩ። ልጆች የነዚያ በእግርህ ስር የነበሩ ጨካኝ አድፋጮች (ሚስቶች) ጦርና ጋሻዎች መሆናቸው ነው መጥፎው። በእነርሱ መክተው በእነርሱ ያቆስሉሃል። የተረገጡት አድፋጮች ርጋጭ መብታቸውን ድንበራቸው ላይ ቆመው ከማወጅ ይልቅ ዋስትናቸው ያንተን የመብት አጥር መጣስ እንደሆነ ያምናሉና ሳያንኮታኩቱ አይለቁህም። የሴቶቻችን መብት በተፈጥሮ ፊት ሞገስን የሚያገኘው "ያንተ" በሚሉህና አምነህ በምትቀበለው ስጋህ ውስጥ ባደፈጠ ቁራጭ ስጋቸው ነው።

...እነሆ እሰናከልበት ዘንድ እግዚአብሔር በህይወት ጉዞዬ ላይ ጥንድ ጉድባዎችን ቆፍሮ ጠበቀኝ። ባለቤቴም በልጅ ዘለበት አብታ "በድከመዬ" ሽመል ያለርህራሄ ቀጠቀጠችኝ።

"ሰው ነበርክ" አለችኝ

"ነበርኩ" አልኳት ነበር ተጣብቶኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

"ታዲያ ምን የሴሊት ነፍሳት አደረገህ?"

"እንጃ!" ግን አውቀዋለሁ እግዚአብሔር ነበር ሁለተኛውን ጉድባ ያዘጋጀው።

"ሰለቸኝና"

ስለሰለቸኙኝ ሰዉ ተደርቤ እራሴን ሰለቸሁት። ብትጠላኝም ሰዉ ተደርቤ እራሴን ጠላሁት። እነሆ ጥላቻዬ በለያማን ፊት ሞገስን አግኝቶ እንደፈረሰኛ ውሃ ያገኘውን ያግበሰብስ ገባ። እራሴን መጥላት ተጋባሽ በሽታ ሆኖ ቤተሰቤን አዳረሰ! ጎረቤቶቼን... እናም! እግዚአብሔር እራሴንና ስራዎቼን። ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የጫነውን ሸክሙን ያወርድ ዘንድ ታዛውን መጥኜ ብዬ ጠበሱን ደጋገምኩ። የተፀናወቱኝን ሚስቴን፣ ልጅንና ማንቋረሬን እንዲገላግለኝ። ምንም!

እናስ? ምን ቀረኝ? ምንም!

...ጉሮሮዬ እንደተቸረቸሬ ሲነጋ ነው ሁሉም ነገር የሚገባኝ። እንደ እንቁራሪት ሁሉ እንቱራሪትነቴን ሳልገነዘብ በማንቋረር አሳልፋሁ። የሚስቴና የልጄ ዶቅማ ፊት በዝምታ አቤቱታ ይደረድራል።

እግዚአብሔር ባለማወቅ የዘራውን፣ ሰው ያርመው ዘንድ ወደ ሀኪምና ፊቱንና እምልከቱን መለስኩ። በባለታዊ ግርማ ሞገስ ቃል እንደተገባልኝ ሳይሆን ቀረ። ሃኪሜ ደሜን አማክሮ "ቀዶ ጥገና አትቋቋምም" አለኝ "ትሞታለህ"

"ልሙት!" ነፍሴ ነበረች የወሰነችው።

"መሞት ይሆንልህ ይሆናል። መገደል አይሆንልኝም"

ምን ቀረኝ? ምንም! ጥላቻ ብቻ!!

ቢመሽ ጠላሁ... ቢደከመኝ ጠላሁ... አልጋዬን ጠላሁ... እራሴን ጠላሁ... ከሚስቴ ጋር በእካል ተፋተን ኑሯችንን ለማወሻሸም ጣርን።



t.me/OLDBOOKSPDF

እነሆ የአለም ጨካኞችን ወደ ጭካኔያቸው ተግተው እንደገቡ እንዲሁም እኔም አጠቅሁ። የሞንጎሉ ገገር ጀንጊስ ካሉን በቆረጠው የሰው ጭንቅላት የሚደረድርበትን 80 ፒራሚድ እንዳሰራ፣ የእርሱን ኃይልና ጥበብ እኔም ተመኘሁ። ባገኘውስ? ባገኘው...

...አንድ አዳራሽ ሙሉ ሰው እጠብቀናን እመክዳቸው እንዳሻኝ ሆኜ አተኛለሁ። ጠዋት በሚለዳ የጦር ባለሟሉን አሰግጄ እንዲህ ስል ከሰማይ ቤቶች የሚሰማን ቃሉን አወርዳለሁ።

"እነሆ ጋሻ ጃግሬዎችህን ወዳጓራሽ የምታበልቅበት ጊዜ አሁን ነው። ከአንቀልፉ ተፋትተ ያገጋ፣ በእኔም ላይ ቁጣው የነደደ ካለ እርሱ በሰይፍህ ቀራሽ ይሁን። አዳራሹም ከዋይታ ብዛት ይናወፅ... በዚህ ስህተት ላይ ወድቆ የተገኘ ልጃም፣ ቢሆን እርሱ ይሙት። ደሙ በእኔ ላይ ነው

"የሌሊት አካኋኑን ተላምደው የሚያድሩ እነርሱ ምድርን ይወርሳሉ..."

አንድ ቀን ባለቤቴ በጠዋት ፊቷ "ቤቱን እንልቀቅልህ?" አለችኝ።

"እኔ አለቅላችኋለሁ" አልኳት። እንኳን ከቤቴ ከአለም ብሰደድ በወደድኩ...

...ዘባረቅህ አትብለኝና ልጅ ሆኜ አንዲት ወጣት ሴተኛ አዳሪ መንደራችን ውስጥ ነበረች። ስንረምስ ምራቋን ዋጥ ያደረገች ሴተኛ አዳሪ ነበረች። ስንሰምስ እንደነገሩ ትዳር ያዘች። ባለቤቷ በአውሎ ነፋስ እንደተፋተን ወረቀት አካሉን የሚያንሳፍፍ የሌሊት ድምፅ ነበረው። ታዲያ ሚስቱ በብጤቱ የተበደችለት ትመስላለች። ጠዋት ፊቷ ልቅ እረፍት ውስጥ ሰጥሞ የቀኑን ባህር ለማቋረጥ የሚያስችል አቅም አጠራቅሞ ብቅ ይላል። ያ ሰው በቅርቡ በሞት ተነጥሏታል። ያቺ ሴት እዚያ ተገዝታ ጎጆ ውስጥ ሆና እድሜዋን ትቆጥራለች። 54፣ 53፣ 52፣ 51፣ 50፣ 49፣ 48፣ 47፣ ወይም ከዚያ በታች።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ቅልጣን

ምን እንደሚያማስለው ሳይታወቅ ሰው ሁሉ አደባባዩን ይሽከረከራል። ዐደቱን ከአራቱም አቅጣጫ የሚቀሳቀሰው ሰው ወዳሻው የሚሄድ ሳይሆን በእሽክርክሪቱ ተጠልፎ የቀረ ይመስላል። የአራት ኪሎ ሃውልት ቀጥ ማለቱን ትቶ የትምህርት ሚኒስቴርን ህንፃ ቢደገፍ አማስሎ አማስሎ አረፍ ያለ ወጥ እንጨት በመሰለ ነበር። የሚያቸፈችፈው ዝናብ እሽክርክሪቱ ላይ የሚነሰነስ ብትን ሽሮ መስሏል።

እፍንጫውን ወደ ቤተ-መንግሥቱ አቅጣጫ ተክሎ የሚያነፈንፈው ሚኒባስ ታክሲ አልሞላ ብሎ እያዛጋ ነው። እንደ መሄድ እየቃጣ መለስ ይላል። ገባሁና ቁጭ አልኩ።

ከወደ አደባባዩ እሽክርክሪቱ የተፋቸው አንዳንድ ሰዎች ቢመጡም አቅጣጫችን ከአቅጣጫቸው ስላልገጠመ ቆም እያሉ ሌላ ታክሲ ይጠብቃሉ፤ ሲመጣ ይሮጣሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ካሳንችስ፣ ሃያ ሁለት!"

አየ እሩ ወያላ እስከመንጋጭላው ተበልቅጦ ሲጣራ "ኑ ላንቃዬ ሶ^ር ከዝናብ ተጠለሉ" የሚል የአውቶቡስ ፌርማታ ይመስላል።

"ሰው የማይገባው ሰፊ አፉን በመፍራት ይሆን?" ስል አስቤ ተንጫነጭኩ። እንደ አጠዳደፊ ቢሆን ፊት ለፊት ከተኮለኮሉት ላዳ ታክሲዎች እንዱን ኮንትራት ይዤ በተፈተለኩ። ግን የሒሳቡ ቆንጣጭነት እያስፈራራኝ አልደፈርኩም።

"ካሳንችስ መናኸሪያ፣ ሃያ ሁለት"

"ፌርማታ አፍ" አልኩኝ።

አንድ ወንድና አንዲት ሴት ተጣብቀው የተወለዱ መስለው ድንገት ዱብ አሉ። በማማሰያው ግፊት የተፈናጠሩ ጓጓላ ሽሮዎች ይሆኑ? የሚኒባሱን አለመሙላት በማየት ይመስላል በሩ ላይ ቆመው የሚያልቅ የማይመስል ወሬአቸውን መሸርከት ያዙ። ለዝናቡ ደንታ የሰጣቸው አይመስሉም፣ ለሰው ደንታ የሰጣቸው አይመስሉም። ኧረ እንደውም ለፈጣሪም ደንታ የሰጣቸው አይመስሉም።

ከሁኔታቸው ፍቅረኛሞች መሆናቸውን ተረድቻለሁ። ሴቷ ሁለት እግሯን ይዘው እንደዘቀዘቋት ሁሉ ደሟ የተከማቸው ፊቷ ላይ ነው። ወንዱ ጭልፊት ፊት ነው። ግንባሩ ጠቦ የአፍንጫዋን እትጣጫ ይደባል። ቅንጡ ላይ ያፈጠጡ ደም ስሮች ይታያሉ። ልጅቷ የነተበ ሸሚዙን እየነካካች ተለጥፋ ታወራለታለች።

"ፍቅር ያዘን ብሎ የምን ደንበር ገተር
እኛም" አንድ ሰሞን እንዲህ አርጎን ነበር"

አልኩ በልቤ። አሁንም ችኮላዬ ለሌላ ሳይሆን ሳልጠግበው ለተቋረጠ የጫጉላ ወግ ነው።

"የሞላ ካሳንችስ፣ ሃያ ሁለት!"



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለምን ይሆን የሚያወሩት? ከልብ ታወራለች፣ ከልብ ያዳምጣል። እኔ ከእኔ እንደተረዳሁት የፍቅር ወግ እምንም ውስጥ የማይገባ እንቶ ፈንቶ ነው። ግን ከየትኛውም ወሬ በላይ በስሜት የተሞላ።

እሱ ፀጉሯን ይነካካል፤

እሷ ሸሚዙን ትነካካለች

እግራቸው ስር የሚያቸፈችፈው ዝናብ ከመሬት ጋር ሲጋጭ የአሸን ክንፍ ይመስላል። የሚያወሩትን ማዳመጥ እንጓጓኝ።

"እንቀሳቀሰው" ወያላው ሾፌሩን ያዝዛል። ሄደት መጠነት በል ነው። የማይተዋወቅ ድንገት የተገናኘው ስለ ኑሮ ውድነት የሚያወራው። ፍቅረኛሞች መረጃ አልባ ወሬ ነው የሚሸረክቱት። ፖለቲካ፣ ፍልስፍና፣ ኃይማኖት ርዕስ ቢሆንም የሚደመጠው በወሬው መሀከል የሚተላለፈው ስሜት ብቻ ነው።

ሴቷ ወፍ እግር ናት፣

እሱ ድፎ ከመሰለ ጫማ ውስጥ የብልቃት ቂጥ የሚያክል በጠፈጠፍ የተቀቀለ እውራ ጣቱ ብቅ ብሏል።

ወያላው "ውስጥ ሁኑና እውሩ" አላቸው። ማማያ ሊያደርጋቸው እንደሆነ ገብቶኛል።

"እሷ ናት የምትሄደው" አለ ወንዱ።

"እኮ ውስጥ ሁኑና ሲሞላ..."

ደስ ብሎኛል። የጫጉላ ወሬዩ እስኪደርስ የእነርሱን በተሻ የፍቅር ማቀሻበል ለመኮምኮም። መጥተው ከእኔ ፊት ተቀመጡ።

ወንዱ እንደማኮብኮብ ብሏል።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ካሳንችስ፣ ሃያ ሁለት" የወያላው እና ማጅራቱ ላይ በነጥብ የተሰያየ መሰለ። ያቺ ነጥብ ብትጣስ ከአሱ በላይ ያለው የጭንቅላቱ ክፍል እንደ ክፍያ ወልቆ ወደ ኋላ መውደቁ ነው።

ፍቅረኞቹ ላይ የጣልኩት ጆሮዬ ምንም ደብ አልተመለሰም። ማጉተምተም ብቻ። ነገር ግን እግራቸው አርጥብ ኖሮ ታክሲው ውስጥ ሰዎች ገባ ገባ ማለት ጀመሩ። እንዲህ ያለ ሁኔታ ለፍቅረኞቹ እንደ አድሰቢስነት ይቆጠራል። መለያየትን ያውቻል።

"ነንቺ ቀድሜ አደርሳለሁ" ያላል ወንዱ።

ለቀጣዩ ቀጠር መሆን አለበት። ካሁኑ ወደ ቀጠሮው ቦታ መሄድ ይጀምር ይሆናል። ግንባሯን ሳማት። የረጋው ደሟ በሐፍረት ፊቷ ላይ ገነፈለ። ሰዎች ይገባሉ። ሚኒባሱ እንደመሙላት ብሏል። ከኋላ የተደለውን ሰው ልቆጥር ዞር ስል የሰው ሁሉ ቀልብ ፍቅረኞቹ ላይ መሆኑን ልብ አልኩ። እነሱ እንደ አበባ ይታያሉ እንጂ አያዩም፤ ቀልብ ይስባሉ እንጂ ቀልባቸው ለሌላ አይሳብም።

ወያላው ሚኒባሱ ላይ ወጥቶ በእግሩ ወለሉን እየደበደበ በብልትጥ እፉ ይጮሃል። ወንዱ በወያላው ጀርባ በኩል ተሸማቆ ከታክሲው ወረደ። ቀልቡ ሁሉ ከኛ ጋር ነው። በድኑን እንደቆመ ኪሱን ፈታተሸ። የተጣጠፈ ብር አውጥቶ በመነጣጠል ሁለት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ወደ ወያላው ዘረጋ። ሥጋውን ቆርጦ የመስጠት ያህል ሆኖ ተሰማኝ። ወደ ፍቅረኛው ጣቱን ጠቁሞ "መልሱን ስጣት" አለው በኩራት

"የት ነው የምትሄደው?"

"ሃያ ሁለት"

"ታዲያ የምን መልስ ነው? እንደውም አርባ ሳንቲም ጨምር"

ልጁ ሞጣጣ ፊቱ አመድ መስሎ የሚያቸፈችፈውን ዝናብ መጠጠ



t.me/OLDBOOKSPDF

"የለችም"

ከእኔ በቀር ልብ ያለው ያለ አልመሰለኝም ነበር። ግን ታክሲው ውስጥ ያለ ሁሉ ሳቀ። ዓለም ውርደት ለመሰላት ነገር ቸልተኛ አይደለችም። ሰማይ ጭምር ብልጭልጭ ጥርሱን አሳየ። ዷ! ዷ! ዷ! ዷ! የሰማየ ሰማይ ሳቅ።

የአይን ቅብብሉ ከልጁ ወደ ፍቅረኛው፣ ከፍቅረኛው ወደኛ ተላለፈ።

"ምን ያስቃል? ማጣት ያስቃል ወይ?"

ጭንቅላት ሁሉ በለፍረት አቀረቀረ። እኔ በበኩሌ ቀና ማለት ተሳነኝ። ልጁ እንደ ጥላ የቤተ-መንግሥቱን አቅጣጫ ተከትሎ ውልብ ሲል ታየኝ።

"በደንብ ሳቁ፤ ሌላም ልንገራችሁ። እኔ ስለደከመኝ ነው ያላፈረኝ እንጂ ሁለታችንም የምንሄደው ሃያ ሁለት ነው። እሱ በእግሩ እስኪደርስ እዛ እጠብቀዋለሁ። ሳቁዋ! ምነው ዝም አላችሁ?"

መልስ የለም። ፀፀት ብቻ።

ልጅቷ ዞራ በትክክሉ ተቀመጠች። ታክሲው አንድ ሰው ብቻ ይቀረዋል። ወያላው መጥራቱን አቁሞ ያዳምጥ ኖሯል። "ጥረውና ሳድርሳችሁ" አለ። ያም ሳይበቃው ልጁ የሰጠውን ሁለት ብር ጭና ላይ አስቀመጠላት።

ይሄ አቦ አፍ ከኛ ተሽሎ ተገኘ። ወደድኩት። ከኔ አጠገብ ልብ ያላልኩት ባለመነጽር ብድግ ብሎ አስር ብር በትክሻዋ ላይ አሳልፎ ጭኗ ላይ አስቀመጠ። ታክሲው ውስጥ ያለው ሁሉ የፀፀቱን ዋጋ ጣለላት።

አስር ብር!
ሶስት ብር!
አምስት ብር!



t.me/OLDBOOKSPDF

ሃምሳ ብር!

እኔም የፀፁቴን ያህል እጄን ዘረጋሁ።

ልጅቷ እንደመባነን ብላ ወደ ኋላ አየች። ከዚያም ጭኗ ላይ ያለውን ብር እያየች ለጥቂት ጊዜ ፈዘዘች። "ልውሰድ ልተው" የምትል መሰለኝ። ሳደፋፍራት እጄን ሰድጄ የትከሻዋ አጥንት ላይ አኖርኩት። ከዚህ በኋላ ያሳየችው ፍጥነት ለተአምር የሚመዘገብ ነው። ብሮቹን ሰባስባ ከታክሲው ውስጥ ስትፈተለክ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ብሮች ወለሉ ላይ ወድቀው ቀሩ። ወደ ፍቅሯ በረረች።

ቢጠበቁ አልመጡም። ወያላው በታማኝነት ጠበቃቸው። ቀሩ። የወደቀውን ሁለት ብር ወያላው ሌላ ያጣ እንዲያሳፍርበት በሙሉ ድምፅ ተወስኖ ተሰጠው። በጉደለ ሞልተን ተንቀሳቀስን። ለጥቂት ጊዜ ፀጥታ ሰፈነ። ልጆቹን ለሚጉላው ወሬዬ አሰናዳቸው ጀመር።

መናኸሪያ ሆቴል እንደደረስን አንድ ላዳ ታክሲ ደጋግሞ ጡሩንባ እየነፋ ከወሰደን ሀሳብ አባነነን።

ግማሹ "ከለፍላፊ" እያለ ይሳደብ ጀመር።

"የት ለመድረስ ነው?"

በላዳው ታክሲ የኋላ መስኮት አንድ እጅ ወጥቶ ሲውለበለብ ይታያል። ሰው ሁሉ ቀልቡ ለታክሲው ተሰቧል። በዚህ መካከል ወያላው አዞ አፉን እንደ ሚሳኤል በፊቴ ላይ አሳልፎ ለመሳደብ ከሞከረ በኋላ ፈዞ ቀረ። ብር የያዘበትን እጁን አወናጭፎ አፉ ላይ በመደርገም

"እንዴ፣ ልጆቹ" አለ።

ከታክሲው የሾለከው እጅ ሁለት ሆነ። ባይ ባይ እያሉን ቀደሙን። ከበስተኋላ ስንመለከት እንደተቃቀፉ ያዩናል።

ሌላ የወሬ ርዕስ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሙትና ሐውልት

ፕሮፌሰር ጤናዳም ጥያቄ ምልክቱን መስለዋል (እሱ በድን ሲሆን እሳቸው ግን ፕሮፌሰር ናቸው) ከቢሮዋቸው ከወዲያ ወዲህ ይላሉ። ማጅራቸውን ለመጠበቅ እንዲረዳቸው እጃቸውን ወደ ኋላቸው ልከው አጣመሩ።

ፕሮፌሰር የረበሻቸው በህይወታቸው ገጥሟቸው የማያውቅ ሁኔታ ስላፋጠጣቸው ነበር። ሁለት ሰዎች (አንድ ወጣትና አዛውንት አያቱ) በመኪና አደጋ ተጉድተው ከሞላ ጎደል የአንድ ሰው አካል ብቻ ቀርቷቸው መጡ። ለሁለት። ከሁለቱ ሰዎች የተገኘው አካል በዝርዝር (ማስታወሻቸውን ገለጡ) አም - ሁለት ዓይን (አንዳንድ ማለት ነው) አሁንም ሁለት እግር፣ አንድ ልብና አንድ ሙሉ አንጎል (ልቡ የወጣቱ ሲሆን አንጎሉ የአዛውንቱ ነው)። በዚህ ላይ የወጣቱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀሪ የላይኛው ማቀፊያ አካል ሊገጣጠም በማይችልበት ሁኔታ ተፈረካክሷል።

ፕሮፌሰር ያስጨነቃቸው የቁስለኞቹ አካል ጉዳይ ሳይሆን የሀሳባቸው አለመገጣጠም ነበር። ወጣቱና አባውንቱ የተለያየ፣ የማይጣጣም አመለካከት አላቸው። ሁለቱም በትገርት ላይ ሆነው ወጣቱ "ቴክኖሎጂ" ሲል አባውንቱ "ባጥንቆላህ ይትከል እባክ" ይላሉ። ይኸውም አደጋው ከመድረሱ በፊት ሲነጋገሩበት የነበረ ርዕሰ-ጉዳይ እንደሆነ ፕሮፌሰር ገምተዋል።

"አካል የአንድ ሰው፣ ሐሳብ የሁለት ሰው እንዴት ይሆናል?" ፕሮፌሰር አሁንም እራሳቸውን ጠየቁ። በተደጋጋሚ የሁለት ሰዎች አካል በአደጋ ምክንያት የአንድ ሰው አየሆነ ይመጣል። አብዛኛውን ጊዜ አብረው የሚውሉት በእድሜና በሀሳብ የተቀራረቡ ሰዎች በመሆናቸው አንድ አድርጎ በመተሳሰብ እንዲኖሩ ለማድረገው ሳንካ አልተፈጠረባቸውም ነበር፤ ከዛሬው ክስተት ሌላ። ወጣቱ ለዘመናዊ ትምህርት እውጭ ቆይቶ የመጣ ሲሆን አያቱ ግን ከእምነት ሌላ የማያውቁ ምስኪን በባህትወና የሚኖሩ አባውንት ነበሩ።

"ሁለቱንም ከማጣት አንድ ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ ተገቢ ይመስለኛል" አሉ ፕሮፌሰር - በሀሳባቸው ወስኑም።

ፕሮፌሰር ጫት ሳይቃም፣ ዕጣን ሳይጨስ፣ ሀድራው ሳይወርድ፣ እንደው በሊጣው በሚጠነቁሉበት ምናምን ነገር ላይ አንድ ዓይናቸውን አጨንቁረው፣ አቀርቅረው በመመልከት ትንሽ ከቆዩ በኋላ በሽተኞቹ ወደተኙበት ክፍል "ደፋ-ደፋ-ደፋ" እያሉ አመሩ። አመራር የሚጠብቁትም ሐኪሞች በአክብሮት ተቀበሉዋቸው

"እህሳ? ለውጥ አለ?"

ዶክተር ችግኝ ቀልጠፍ ብሎ "እርሶ የወሰኑበት ከሆነ..." አለ



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ ወስኛለሁ"

"ጥሩ ሲበዛ አድለኞች ነን ለማለት እደፍራለሁ፤ ምክንያቱም የሁለቱም ጉዳተኞች አካል ከግማሽ በላይ ቢጐዳም የሁለቱም ምላስ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። በመሆኑም ሐሳባቸውን ልንጠይቃቸው እንችላለን ብዬ አምናለሁ።"

"ምላስ ብቻ ምን ሊረባ?" አሉና ፕሮፌሰር ወደ ፊታቸው ዘንበል ስላሉ ለማዛን መጠበቂያ እጃቸውን ወደ ኋላ አጣምረው "የወጣቱ አንጐልና የአዛውንቱ ልብ የለም - አይደለም?"

"አዎ፤ ግን እኔ ከእርሶ ባላውቅም ምላሶቻቸውን፤ የወጣቱን ከልቡ ጋር፤ የአዛውንቱን ካንጐላቸው ጋር በጊዜያዊ መልክ አያይዘን እንድ የመሆናቸውን ሀሳብ ብንጠይቃቸው ተገቢ ይመስለኛል" አለ ዶክተር ችግኝ።

"ጥሩ ሐሳብ ነው፤ አንዳንድ እጅ አላቸው አይደል?"

"አዎ"

"እንግዲያው ከውሳኔያቸው ስር አስፈርመህ አምጣልኝ" አሉና "ደኅ ደኅ" እያሉ ወደ ቢሮዋቸው ተመለሱ።

* * *

ሁሉም ነገር ተሳካ - የመዋጮ ኑሮውም። ፕሮፌሰር በሥራቸው ዘጠነኛ ኩራት ተሰማቸው። ምክንያቱም ስምንቱን ኩራት አንድ ባንድ ከዚህ በፊት በሌሎች ላይ ኮርተዋልና። ትንሽም ቅር የሚያሰኛው የአሁኑ ድበላ በአካልም ሆነ በአስተሳሰብ እኩል አለመሆኑ ነው። ሌላው ደግሞ ጉዳተኞቹን ሊያስማማቸው ያልቻለ የነበረው የምላስ ጉዳይ ነበር፤ ምክንያቱም የሁለቱም ምላስ ደህና ሲሆን ‹የኔ ይሁን፤ የኔ› የሚለው ክርክር ፕሮፌሰር ቢያስጨንቃቸውም በመጨረሻ ዘዴ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘይደውለት በአንድ ጭንቅላት ሁለት ምላስ ተዋህዶ እንዲቀመጥ አድርገዋል። የመጨረሻ ሥራ የሚተዳደሩበትን ደንብ ማርቀቅና የሁለት አንድ የሆነ ስም እንዲኖራቸው ማድረግ ነበር። ይህም በዶክተር ችግኝ ተጠናቆ ቀረበ። "ሁሉም የጋራ ነው" ይላል አረቂቁ አፉን ሲከፍት "እግሮች የጋራ ናቸው፣ እጆች የጋራ ናቸው፣ ዓይኖች የጋራ ናቸው፣ ልብና አንጎልም የጋራ ናቸው፣ እንዲሁም ችግሮች የጋራ ናቸው - ደስታዎችም"

ስማቸውም ‹ሙትና ሐውልት› ተባለ።

ሙትና ሐውልት ከተዋሃዱበት ከመውጣታቸው በፊት የመሔድ ጥምረት እንዲኖራቸው እንዲሁም የመብላት ልምምድን ተያያዙት። የሙት እግር ‹ነጠር› ሲል - በዘመናዊነት፣ የሐውልት እግር ደግሞ ‹ኮሰስ› ይላል።

‹ነጠር-ጠር-ጠር፣ ኮሰስ-ሰስ-ስስ፣ ነጠር-ጠር፣ ኮሰስ-ሰስ፣ ነጠር-ኮሰስ፣ ነጠ-ኮስ፣ ነጠ-ኮስ፣ ነጠኮስ፣ ነጠኮስ እያሉ ልምምዳቸውን በ‹ነጠኮስ› ቅንጅት ጨረሱ። ከመዋሃጃውም በደማቅ አሸናፊነት ወጡ።

"ሙትዬ" አለ ሀውልት

"ሀውልትዬ" አለ ሙት

"ምነው አላምን አልኩ? ፍርሃት፣ ፍርሃት ይለኛል"

"ልብህ ስለሌለ ነዋ፣ ይልቅዬ እኔ ደስ፣ ደስ ይለኛል፤ እመን እመን ይለኛል"

"አንጎልህ ስለሌለ ነዋ፣ አንጎል ፍርሃት ነው"

"አንጎል አለመኖሩ እንዴት ጥሩ ነው ጃል"

"ልብ አለመኖሩስ? ዓለም ነው"



t.me/OLDBOOKSPDF

"በፊት አንስማማም ነበር - ሐውልትዬ"

"አሁን ተስማማን - ሙትዬ" አሉና ተጠኮሱ እያሉ መንገዳቸውን ተያያዙት "ሁለት ልብ፣ ሁለት አንጎል። እንዴት መጥፎ ነገር ነው እባክህ - ያጣላል"

"አንድ ልብ፣ አንድ አንጎል እንዴት ጥሩ ነው - ያፋቅራል"

"ሐውልትዬ"

"ሙትዬ"

"እኔ ምንህ ነኝ?"

"ሕይወቴ... እኔስ ምንህ ነኝ?"

"ነፍስ."

ልብና አንጎል፣ ነፍስና ህይወት፣ አንድና አንድ... ሁለትና ሁለት... አራትና አራት... ብዙና ብዙ=ሕዝብ



t.me/OLDBOOKSPDF

# የቦና እናት

እንደ አባብ ወገብ የተጥመለመለው የቁራጭ ሰፈር የውስጥ ለውስጥ መንገድ በአጠና ድርድር ላይ የተነጠፈ የድንኳን ጨርቅ ተከድኗል። ለውትሮው እንደ ውይይት ታክሲ አፍንጫ ለአፍንጫ የሚያላልሰው ደጃፍ በተአምር መሃል ላይ ጠረጴዛ ጨምሯል። በኬር የተሰራው የድንጋይ ንጣፍ ጉዝጓዝ እርሜ ሆኗል።

"ኧረ እኔንስ ጨነቀኝ" አሉ "የቦና እናት" አፋቸውን በአዳፋ ጨርቅ ሸፍነው። እታለማሁ መሃን በመሆናቸውና ለሰፈርተኛው የቦና ውኃ በማስቀዳታቸው ነው "የቦና እናት" የሚል ቅጥል ስም የወጣላቸው። እታለማሁ በቅጽል ስማቸው አይከፋም። እንደውም አንዳንዴ "እኔ የቦና እናት" እያሉ በራሳቸው ያሾፋሉ።

"ምነው?" አሉ አጠገባቸው የተቀመጡት ወ/ሮ ማሚቴ

"ተበልቶ ተጠጥቶ ሲወጣ ምንድነው የሚባለው? ነፍስ ይማር እንዳንል ተዝካር መሆኑ አልተነገረን። እ-እንኳን ፈጣሪ ሰማችሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳንል ስዕለት መሆኑን ማን አውቆ? እንደው ደርሶ ብሉልኝ ጠጡልኝ ሆነ። የጨነቀ ነገር!" ፊት ለፊታቸው ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠ የተፋጠጣቸው የጠርሙስ ጠላ ገና የወረቀት ክንብንቡን አላጠለቀም። የወ/ሮ ማሚቱን ጠርሙስ አዩ። በአፉ በኩል የውስጥ እግሩ ይታያል።

"ጭምጭምታ ስሰማ" አሉ ማሚቱ ጉሮሮዋቸው ውስጥ የተሰነቀረውን እርጥብ ሲጋ በጠላ እያወራረዱ "ጭምጭምታ ስሰማ እሮጊቷ ሊቆርቡ አለበው የቁም ተስካር ነው አሉ።"

"ድንኳን ናቸው የሚቆርቡ?"

"እ?" ማሚቱ የሚሸጡትን እንጀራ በሚያክለው መዳፋቸው ሙሉ የያዙትን ሲጋ ለመቁረጥ ይታገላሉ።

"ጉኔስ አይመስለኝም።" የቦና እናት ከጠገበ ጠርሙሳቸው ጋር ተገለማመጡ። እንደ ጎረምሳ በትክሻው የሚያያቸው መሰላቸው። "ይልቅስ ልጃቸው አጥናፉ ቀለበት ሊያስር ነው ሲሉ ውልብ ያለኝ መሰለኝል።"

"ይቀልዳሉ የቦና እናት። እራስ ሳይጠና ጉተና አሉ። አጥናፉ ለራሱ እናቱ ላይ ተጣብቆ የሚኖር። አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል። ኧረ ዝም ይበሉ አሁን አጥናፉ ሰው ሆኖ ሚስት ሊያገባ? በቀን ሺ ብር የማይበቃው፣ በየደረሰበት የሚያድር ከንቱ..."

"እንግዲህ በስርግ የጠባይ አውጫጭኝ የለ"

"አሁንስ በኖረ" አሉ ማሚቱ - ተሳሳቁ።

ሳቃቸው ስለበረከተ አካባቢያቸውን ቃኙ። ልብ ያላቸው አልነበረም። እንጨት ፈላጩ የደሞዜ አባት ወትሮውንም የሚያዘወትሩት "ውኃ" በመሆኑ ዛሬም ብርጭቆቸውን እንደ እንጀራ እናት ጡጦ አፋቸው ላይ ለግተዋል። መቃብር ቆፋሪው ቢተዉልኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሰዱን ይቆፍር ይመስል ሹል አጅን እንደ ዶማ ይተክላል። የሰፈሩ ሽማግሌ አብዬ ጣሴ ነጩ ሪዛቸው በወጥ እንዳይበላሽ ያሰሁ ይመስል በጥንቃቄ ይመገባሉ። አንደ ዘንዶ ወድ የተጠነው ድንኳን ጥግ ጥጉን የቁጭራ ሰፈርተኞች ደለል እንደተከናነበ የአርከን ድንጋይ ተደርድረዋል። ድንገት…

"ቸብ! ቸብ! ቸብ!" ጭብጨባ

ቀና ቀና አሉ። ወ/ሮ ድንኳኔ እንዲጋቱ የላም ጡት የተንጠለጠለ ፊታቸውን ይዘው ተጋባዡ ፊት ቀርበዋል። በአውራና በጠቋሚ ጣታቸው የከናፍራቸውን ዳርና ዳር ተከትለው ሞገቱና…

"ወገኖቼ አክብራ ስጠራችሁ አክብራችሁ ስለተገኛችሁ አመሰግናለሁ።" አሉ። ለድንገተኛው ንግግር ድንገተኛ ጭብጨባ።

ወ/ሮ ድንኳኔ ያደገደጉትን ነጠላ አስተካክለውና "ዱሮ ድግስ ያስፈለገበት ምክንያት ነፍሳቸውን ይማርና ፊታውራሪ ለእንደራሴነት ሲወዳደሩ እዚችው ቦታ ነበር ድግሼ ያበላሁት። ዛሬ ታዲያ አጥናፉ ልጄ ነፍሴ አውቆ ያባቱ ስም ተቀብሮ አይቅር፣ እኔም ለእንደራሴነት እወዳደራለሁና የቁጭራ ሰፈርተኞችን ድግሴ አብይልኝ አለ። እኔ እንኳን የቁጭራ ሰፈርተኞች የአባትህ ውለታ ስላለባቸው ካንተ ሌላ ማንን ይመርጣሉና ድግስ ያስፈልጋል? ብዬ ነበር። አይሆንም ብሎ አስደገሰኝ እንጂ።"

ለትንሽ ደቂቃ ሁሉም ፀጥ እረጭ እንዳለ ቆዩ። ቀጠሉ ድንኳኔ…

"ይመስለናል እንጂ የጨዋ ልጅ ወድቆ አይወድቅም። ከእንጨት መርጦ ለታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት ነውና የልጄን እንደ ወርቅ የነጠረ ዘር በቅርብ ስለምታውቁት ድምፅ እንድትሰጡልኝ በቁጭራ አድባር ለመጠየቅ ነው።"

ፀጥ - እረጭ



t.me/OLDBOOKSPDF

"ብረትን እንደጋለ ነው" ሲሉ ድንኳን አሰቡ። ዛሬውኑ የቁጭራ መንደርተኞችን ቃል ያስገባሉ። "በሉ እንጂ፣ ቅሬታም ካለ ልስማው" በማለት ቀጠሉ። "መቼም የደጉ ፊታውራሪ እጅ ያላለፈበት ሰው እዚህ አይገኝም። ዛሬ ልጃቸው እፊታችሁ ቆሞ ድምፅ እንድትሰጡት ሲጠይቅ ብትግመመሙበት አጥንታቸው ይወቅሳችኋል" ወ/ሮ ድንኳን ቁልጭ ቁልጭ የሚለውን የቁጭራ ሰፈር እልፍ አዕላፍ ዓይን በሁለት ዓይኖቻቸው ገረፉ።

"እየበላችሁ!"

መጀመሪያ ለመናገር የደፈሩት የቦኖ እናት ነበሩ። "መቼስ" አሉ "መቼስ ልጅዎን ባንወልደውም ልጃችን ነው..."

"ጉሽ፣ እንዲህ ነው" አሉ ድንኳን

"መቼስ ለኛ የምናውቀው የሚያውቀን አጥናፉ ቢመረጥ ጥሩ ነበር..."

"አሬ ቆርጥ ይበል" እንደ ካስ የተድቦለቦለው ፊታቸው ፈገግ ሲሉ ወደጎን ሞለል አሉ። ቀጠሉ የቦኖ እናት

"የቁጭራ ሰፈር እንደ አንድ ቤት ናት። ክፉውንም ደጉንም እናውቃለን። እውነት ለመናገር አጥናፉ ብዙ ሲያስተካክላቸው የሚገቡት መጥፎ ባህርይ አለበት።"

"ልጅ ነው፣ ይመከራል - ያስተካክላል። ብቻ ምረጡት"

"ቆይ እንጂ" አሉና የቦኖ እናት "አጥናፉ ብዙ ጊዜ ይጠጣል። ሁ ትንም እንደምናውቀው ደግሞ ሲጠጣ ክፉ ደግ አይለይም። ታዲያ እንዴት ብለን ነው እሱን ወክለን ም/ቤት የምንልከው? እንደውም እንደው ነን ጭራሽ ለካራም ላኩ እንባል?"

"አይ የቦኖ እናት፣ ጥሩ - ጥሩ መጥተሽ በስተመጨረሻ አከፋሽው" አሉ ድንኳን። ሲናገሩ ሆዳቸው ከፍ ዝቅ እያለ "ሁሉም



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚመርጠው ገመና እየሸፋፈነ ነው። ይሄ ሁሉ እንደራሴ ጤነኛ ነው ብለሽ ነው? አይደለም!"

"ይሄ ብቻ ቢሆን ጥሩ" አሉ የቦና እናት። ይሄኔ ሌሎቹ የቁጭራ ሰፈርተኞች ካደፈጡበት የምግብ ቋጥኝ ቀና - ቀና ማለት ጀመሩ... "ይሄ ብቻ ቢሆን ጥሩ። አጥናፉ ገንዘብ አይበቃውም! ብዙ የምናውቀው አለ። እርሶ ሱቅ በከፍቱለት ጠጥቶበት ጨረሰው። ታክሲ ቢገዙለት ሸጦ አጨበጨበበት። እሄም ልክነው እጁ የገባውን ገንዘብ ቢያወድድም ባላየነው ሰዶ ልንገባ?..."

"የኔ የናቴ ገንዘብ መስሎሻ? መቼም አጥናፉ በሰው ገንዘብ የሚጠረጠር አይደለም። የኔ የናቱን ያባክን እንጂ..."

"ቆይ እንጂ" የቦና እናት በነገር እየጋሙ ሄዱ። "አጥናፉ ሲበዛ ግደለሽ ነው። መንደራችን ውስጥ ጨኸት እየተሰማ ብትም አይል። ሌላው ቀርቶ በበራችን እያለፈ ባሎቻችን ሲደበድቡን ዝም ነው የሚለው። እሄም ልክነው አገር ሲወረር ሲያደፍጥም አይደል?"

"መቼስ ሰው ያላመል አይፈጠር" ድንኪን የሰለቻቸው መሰሉ።

"ይሄ ብቻም አይደለም። ስለችግራችን ለማሰብ ደንታ የለውም። የአገርም ጉዳይ ይዞ ምንግዴ መሆኑ አይቀር።"

"እንዴት ነው ነገሩ?" አሉ ድንኪን ትዕግሥታቸው እያለቀ "መቼም አጥናፉ በና ውኃ ከምታስቀዳው ጋር ሲያስቀዳ፣ እንጀራ ከምትጋግረው ጋር ሲጋግር አይቻለው። እንዴት ነው ችግራችንን ለማሰብ ማለት?" ይሄ የድንኪን አባባል ጉርምርምታ አስነሳ...

ከጉርምርምታው መካከል የገነነው የወ/ሮ ማሚቴ ድምፅ ነበር።

"አጥናፉ ለምክር ቤት የምንወክለው ሰው አይደለም!"

"የኔ ልጅ ምን ያንሰዋል? ደሙ እንደሁ የጠራ ጨዋ ልጅ ነው" አሉ ወ/ሮ ድንኪን። በዚህ መካከል ድምፁ ያልተለየላቸው ሰው



t.me/OLDBOOKSPDF

"የጠራ ደም" የሚያስፈልገው ለም/ቤት ሳይሆን ለቤተሰብ ጉባኤ ነው" አበገናኛቸው፡፡ ግን ዋጥ አደረጉትና

"የናንተ ለማኝ ያደረገንን ቀና ብሎ ማየት ደግ ነው፡፡ የፊቴዋ ልጅ ቢሆን ይሄን አያደርግም!" አሉ፡፡

"ሌላው ይቅር አጥናፉ የንቀቱ ንቀት እኛ ፊት ሳለመቆሙ እቤቱ ተቀምጧል፡፡ ታዲያ እንዴት ነው የሚንቀውን ኀብረተሰብ ልወክል ማለቱ? በኛ የለመደው እዛም ሄዶ መላውን ህዝብ ሲንቅ አይደል?" በማለት ማማሚቱ አከሉ፡፡

"አይወክለንም! አይወክለንም!" የሚለው ቃል እየበዛ ሄደ፡፡

"ያም ሆነ ይህ" አሉ ድንኳን "ማንም ሰው ቦታው ላይ እናቱን አባቱን ማስቀመጥ አይቻለውም፡፡"

"የሚጠቅም" ሰው ከተቀመጠ ያው የናትና ያባት ያህል ነው" አሉ የቦና እናት ግልፍ ብሏቸው፡፡

"አለማወቅሽ! አዳሜ በናንተ ሃሳብ በአድማ አጥናፉን ከመመረጥ አግዳችሁ ሳትሰሩ የምትኖሩበትን ቤት ለማስቀረት፡፡ አይምሰላችሁ! ስንቱ መኳንንት ተወዳድሯል፡፡ ያኔ መግቢያሽን ትፈልጊያለሽ!"

"ነው'ንዴ?" በሚል ሁሉም ተያዩ...

"ባይሆን" አሉ የቦና እናት "ባይሆን የበላነው ተሰልቶ ወደፊት እንከፍላለን..."

ወ/ሮ ድንኳን አቋረጡ "በደግ ጊዜ ቢሆን ይሄ ንግግርሽ አርባ አኮርባጅ ያስገርፍሽ ነበር፡፡ አሁን እኔ ነኝ ባንቺ የምከፈል?..."

ከዚህ በላይ መቀጠል አልተቻለም፡፡ የቁጭራ ሰፈርተኞች እንደደፈረሰ ጎርፍ ተግተልትለው ከሸንቃጣው ድንኳን ወጡ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ዐሚዛነ-ሰብዕ ወእንሰሳት

አቶ ሲበሉት ለአብ የቢያሚራብ በሌሊ የነው በተመረጡ ነግሀ ነበር ማያዩ ስለማናቸውን ይዛው እንዴ የእቴጌ ገበያ ላይ ያገኟቸው።

ከሀገዘብሰብስ ወ እንስሳ ገበያ።

"ባሬስ የሚመዘን አሁንጃ" አሏቸው።

"ሞልቶ" አሉኝ እራሱ ሞልቶ፣ ቃሉ አናቸውን ሞልቶ

"ባሬ የነሱ ቀሪ ነው"

"የነማ?"

"የአብርሃምና ልጁ... ልጅ"

"የአብርሃምና ልጁ...ልጅ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እዎ የስላሴዎቹ አብርሃምና ልጁ...ልጁ"

ጭንቅላታቸውን ወደ ሁለት ትከሾቻቸው ዘንበል ቀና... ደግሞ ዘንበል እያደረጉ አይኖቻቸውንና ጆሮዎቻቸውን ወደ ሚዛንነት ቀየሯቸው።

"ከማን ይበልጣሉ የማይመዘኑት?" አሉኝ።

"እይ ልጁ... ልጁ ሲ - ሲሉ እባክዎ ካይና ሚዛን ያውርዱኝ ሚዛን እፈራለሁ" በአንክሮ ሲያስተውሉኝ የቆየው ወፈፌው ጠበቃ ድንገት አፈፍ ብሎ "ህግ፣ ህግ... ህግን አስቀምጠው ባይና በመመዘኖ ያስጠይቅዎታል" አለ

"ማነህና?"

"ወፈፌው ጠበቃ"

"ማስረጃ"

"ይኸው አይኔ... በርበሬው" ዞር "ያው ኩሲሶ ገጣባ ግጥብጥቡ አህያ"

"እ፦ንም ማስረጃ"

"ይዩኝ"

"አይኒ ታግዷላ"

ወፈፌው ጠበቃ በመሸነፍ አቀማመጥ ቁጭ...

ስብሐት ለአብም ትከሻዎቻቸውን ከፍ ዝቅ እያደረጉ ይጫወቱ ገቡ - ሚዛንኛ ጫዎታ

"በሉ'ንጂ ይመዝኗቸው ተመዛኞቹን" አልኩ

"ቆይ... ይብላላ አህሌ ወስጋዬ እያብሰለሰለው ነው"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጨዋታ መሰሎኝ"

"ሁሉም ጨዋታ ነው ቢሆንም ይመዘናል"

"በሉ ንሱ ይቀጥሉማ"

"ተቃውሞ አለኝ! የአርሶ ሚዛን ያላባቱ እግሬን የባፍ እግር አድርጐታልና አልቀበለውም" አሉ አንድ እግረ-እንጨት ሰው።

ህዝበ-ሰብዕ ወ እንስሳት ከቱናው ላይ ዝርግቷ። አንዱ ባንዱ ላይም ሆነ... የየራስ ድምፅ እስኪጠፋ ተደበላለቀ።

(እንዳንሰላች በማሰብ እዚህ ላይ በተነሳው ሁካታ ፈንታ...) ተውት... የማይመስለው ተረጋግቶ ቁጭ...

"የሚዛን አወጣጥ?" ጠየቅሁ

"ሥጋቸው እንደተቆራኝ ከሳሽና ተከሳሽ ሆነው ይቀርባሉ"

"ማስረጃ!" ወፈፌው ጠቢታ አለና አንድ አስራ ስድስቱ አይኖቹን ገበያተኞቹ ላይ አጉረጥርጦ ሲያበቃ አንገቱን አቀርቅሮ ከሲሶ አህያው ስር ቁጭ አለ።

"እጁ... ዳበሳዬ" አሉና ስብሐት ለአብ "አብርሃምም ከነማስረጃው ከነነራው፣ ይስሃቅም ከነልጅነቱ ከማስረጃው"

"ይመዘን"

"አይመዘንም!" አለ ወፈፌው ጠቢታ

"ለምን?"

"ሚዛን ላይ መውጣት ያለባቸው አብርሃምና ልጁ ሳይሆኑ ይስሃቅና እዚሀር ናቸው" አለ ወፈፌው ጠቢታ። ቁጭ በማለቱ ጆሮው ለኮሲሶ አፍ ቅርብ ነበር። "አብርሃምማ ሚዛን ነው ፍርድ ሰጪ... ከሁለቱ አንዱን ይምረጥ - ወይ እግዚሐርን ወይም ልጁን!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እዚህርን ማን ይጥራ?" አሉ ስብሐት ለአብ ዝም... መሳፈሪያው ሞት ላይመልሱ የሚባለው ያልተገራ ፈረስ ነዋ!

"ወደዚያ የሚሄድ እስከምናገኝ ሁለቱ ቢመዘኑስ?"

"ይመዘኑ፣ ይመዘኑ"

ተመዘኑ... ሚዛኑም በከፍ ዝቅ ካጣጣረ በኋላ በህቅታ እንገቱን ዘለስ አድርጎ አረፈ።

"እንግዲህ በሚዛንኛ ቋንቋ ከፍ ያለው ምንድነው?" አቶ አ. በአማካሪያቸውና በውሻቸው ኮምቡጠር ጉትጎትነት አፍ ሆኑት (እሱን የሚሰማው የለማ)

"የቀለለ"

"ዝቅ ያለውስ?"

"የከበደው ነዋ! ትልቁ"

"እስቲ መዝኑት" አለ ኮምቡጠር ጌታው የጀመሩለትን ሲጨርሰው።

"ምኑን?"

"የቀለለ ከፍ፣ የከበደ ዝቅ ማለቱን። በኛ...በኛ የከበደ ከፍ፣ የቀለለ ዝቅ ነው የሚል"

"በኛ የቀለለ ከፍ ነው'ሚል። በውሻኛ እንመራም" (እዚህ ላይ ስልጣን ስራዋን ልትሰራ ነበር፣ ግን ኮምቡጠርም የዋዛ አይደለም)

"እንዳንዴ ከኛም ተማሩእ። እኔና ጌታዬ አቶ አ. ብንመዘን እሳቸው ዝቅ እኔ ከፍ?... ውሻቸው'ኮ ነኝ"

"ዳግም ይታይ" አቶ አ. አሳስቧቸው ጮኹ

ኮምቡጠር ምስጋና ይግባውና የሚዛኑ-ስልጣኑ ህግ ተቀየረ - ከፍ ያለ ትልቅ፣ ዝቅ ያለ ትንሽ። እንቀጹም በስሙ እንዲሆን ተመረቀለት።



t.me/OLDBOOKSPDF

"የከማ"ቡብር ህግ - አንድ" (አንድ የገባችው ለሁለተኛው ማንሳሻ ይመስላል)

አጋፋሪ እንደሻው በቅሎአቸውን እየኰረኰሩ ደረሱ "የሞተ አለ?" ብለው "የታመመስ?"ን ሊደግሙ ሲሉ ሁሉም አፉን እየተመተመ ዝም አሰኛቸው።

"እስቲ፡ አሁን ደግሞ ሚዛኑ ሚዛን ላይ ይውጣ" ባለ እንጨት እግሩ ጠየቁ።

"እስቲ፡...እስቲ፡..." አሉ አጋፋሪ በህዝበ-ሰብዕ ወ እንስሳት ባህር ላይ በትከሻቸው እየቀዘፉ "ውይ... ውይ... ውይ... አብርሃም፣ ያሌሉት" ብለው ሊስሚቸው ትከሻቸውን ሲያሞጠሙጡ፡-

"እንዳይቀርቡ ሚዛን ላይ ናቸው" አለ ወፈፌው ጠበቃ

"ውይ..." ብለው ያሞጠሞጡ ትከሻቸውን ሰብሰብ አድርገው "እነሱም" ሚዛን ላይ? ደሞ እነሱ ምን አደረጉ? የደግነት አርአያዎቹ፣ የጥድቅ ናሙናዎቹ"

"እሱም" ቢሆን ይመዘናል" አሉ ስብሐት ለአብ

"ጥሩ፣ ማን የማነው ጥላ ሚዛኑ ላይ ያረፈው?"

ሁሉም ጥላውን ፈለገ፣ መፈለግ ያቃተውም አጠገቡ ባለው አስፈለገ። ሁሉም አገኙ የአንድ ሰው ብቻ ጥላው ጠፋ። ትርፍ ጥላ ከትርፍ ሰው ጋር። ምንም ማድረግ አልተቻለም - ጥላው ለስብሐት ለአብ ተሰጠ። "በሉ ጥላዎን ተሚዛን-ስልጣኑ ላይ ያንሱ" ተባሉ።

"ለምን? ማን ባለሚዛን እንዳደረገው ሁላ?"

"ሚካኤልሳ?"

ባይናቸው ሚዛን ሊመዝኑ አሉና ማሯቸው ጠያቂውን



t.me/OLDBOOKSPDF

"በላኤ ሰብዕ ሰባ ሁለት ነፍስን ያህል በልቶ ሲያበቃ የዳነው በጥርኝ ውሀ ብቻ አይደለማ። በዚሁ መዘዘኛ ጥላ ነው"

ስብሐት ለአብ በእግራቸውም በእጃቸውም አቅማሙ "ያስበለዚያ እንደኛ ፊቱን ወደ ሚዛንና ፀሐይ ያድርጉ" የስብሐት ለአብ ስልጣን ውሃ ሲበላው ሆነ። ቀለል ያለውን መርጠው ዞር ሲሉ ጥላውም (እንዴ ለላቸው ተሰጥቼያለሁ ብሎ ይሆናል) አብሯቸው እንደ እባብ እየተንፏቀቀ ዞር...

እነሆ ትንሳኤ ሚዛንም ሆነ።

ሁለተኛው ህግም አብሮ ተጻነሰ... "በሚዛን ከመጠቀማችን በፊት ፊታችን ወደ ብርሃንና ሚዛኑ ይሁን" ግን ተጸንሶ ለመወለድ ከመወለድ በማያንስ ሁኔታ ላይ እንዳለ አንድ ደግባን ባይ ሀሳብ አንገቱን አሰገገ "ብርሃን ሁሉ ጥላ አለው። ይህም በመጽሀፉ ላይ ታይቷል" የሚል። እህያው ኮሲሶ ለእራሱ ሲያጉመጉመው እስሩ ባለው በወፈፌው ጠበቃ ተደምጦ ነው ቢባልም ሀሳቡ ማን ላይ ቆሞ እንዳሰገገ በውል አልተረጋገጠም። እንዲህ ተሆነ የብርሃን ድብቅ ጥላ በድብቅ በአንዱ ተመዛኝ ወገን ላይ ብቻ ሲያርፍ ይችላል።

በዚህ የብርሃን ጥላ ላለመጠቀም ጭለማ ውስጥ በዳበሳ ማረጋገጫነት መሞከር የተሻለ ይሆን ነበር፣ ግን ጭለማም ኃይል አለው - የብርሃንን ያህል።

ወፈፌው ጠበቃ ‹ሃሳብ አለኝ› በሚል አነሳስ ወፈፍ ብሎ "የብርሃን ጥላ ጭለማ፣ የጭለማ ጥላ ብርሃን" አለ

"ዛዲያሳ?"

"በብርሃን የተመዘነው በጭለማ ይረጋገጥ" በቅድሙ ማጉረጥረጦች ላይ አንድ ሶስት ጨምሮባቸው "በጭለማ የተመዘነው በብርሃን ይረጋገጥ" አለ። እፎይታ ተወለደች።



t.me/OLDBOOKSPDF

የመወሰድ ሳቋን አልቅሳም ሳትጨርስ...

"ይሄማ ብርሃንና ጭለማን እንደመመዘን ነው" አሉ ሰብሌት ለአብ

"ቢሆንሳ?"

"የምንመዝነው አልተመዘነም"

(የመስቀል ወፍ፡ የአደይ አበባ ጠጅ መስሳ መጣች። አይናፋርነቷን ለመሸሸግ በቀስተ ዳመና ክንፎቿ እየተጫወተች) እንዲሁ እነሆ ትንቢት ነበር ተፈፀመ። እንዲህም" ስትል አዜመች (ዜማዋ እናንተ ልብ መሆኑን እያስታወሳችሁ፤ በአይናችሁ እንዳትፈልጉ)

የተቃርኖ... ኖኖኖ..

ኑሮ... ሮሮሮ...

ተዋቸው... ቸውቸው... ቸው...

አንድ ናቸው... ቸው.. ቸው.. ቻው...

"ማንን ሳይጠሩ መመዘኛ ቦታ?" የሚል ሀሳብ የሁሉንም ጭንቅላት አጠጋጋው... አጠጋግቶም አንድ አደረገው።

ህዝበ ሰብዕ ወ እንስሳት አንድ ሆኑም።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ኩርቢቷ

## 1

ጀንበሬ፣ ዛፎቹ፣ የቀበና ወንዝና አሞራው የአደራ ልጆቼ ናቸው። አደራ የሰጠኝ አባታቸው ብሩክ ነው። ከደቂቃ በፊት ደውሎልኝ፦

"ባምቢ" አለኝ። ለምን እንዲህ ብሎ እንደሚጠራኝ ስጠይቀው፣ "የምታምር ወፍ ነሽ" ይለኛል።

"እ?" አልኩት

"የምናውቃቸው ደህና ናቸው?"

"የምናውቃቸው" ጀንበሬ፣ ዛፎቹ፣ ወንዙና አሞራው ናቸው።

"ደህና" አልኩት።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሩኬ ስለ እራቱ ሲያወራ ስለ ልጆቹ የተጨነቀ አባት ይመስላል፡፡ ጀንበሯን የሚያያት እንደደረሰች ኮረዳ ነው፡፡ አፍላነት በቀሰቀሰው አመፅ አልገሰፅ ብላ እንዳስቸገረችው አባት ሁሉ ይትከነከናል፡፡

"በውብት ዓይን ማጥመድን ሥራዬ ብላ ይዛዋለች" በማለት ያጉተመትማል፡፡ ጨልሊው ሲንደፋደፍ እንደመባነን ብሎ ወደላይ ይመለከታል፡፡

"እይው ይሄን ገንገበት ጨልሌ፡፡ ስንት ጨሉፉት ጨልሌ ባለበት ሀገር ይሄን ዘኸተት ያጎራብተን? ይሄኒኮ ሲያንጉላጅ የጨበጠውን ለቅቆ ነው፡፡ የእሱ ነገር ለማደሪያ የመረጠው ቅርንጫፍ ደረቅ ሆኖ ተሰብሮበት ይሆናል፡፡"

ከጨልሌው መንደፋደፍ ጋር የዛፉ ፍሬዎች የወርቅ እንባ እየመሰሉ ረገፉ፡፡ የደረቁ እንጨቶች ተንጠባጠቡ፡፡ የብሩኬ አይኖች አብረው ከረገፉበት ቦታ ላይ መነቀል አቅቷቸው እዚያው ቀሩ፡፡ ትክ ብዬ የማየት ዕድል አገኘሁ፡፡ የረሃብተኛ ፊት አለው፡፡ እንደ ነሐስ አምድ የጀንበሯ ጨረር ያረፈበት ፊቱ ወርቅማ ፀዳል ፈስሶበታል፡፡ ሰጋጋ አንገቱ አይን እንዳይስብ አስካርብ ያዘወትራል፡፡ እንደወትሮው ቀለም ቀለም የሚል ሽታ አለው፡፡ ረዘም ያለ ጃኬት ለብሷል፡፡

በእንቅልፍ ልብ እንዳለ ሁሉ አይኖቹን ሳይነቅል መለስ ብሎ ካለንበት በረንዳ ወርዶ አጐነበሰ፡፡ ከተንጠባጠቡት ፍሬዎች አንዷን አንስቶ ተመለሰ፡፡ አጠገቤ ቆሞ እያገላበጠ ያያት ጀመር፡፡ ፍሬ አይቶ የማያውቅ ይመስል ተደምሞ ማጢጢ ድቤ የምትመስለውን ፍጡር አተኮረባት፡፡ ጉኗን፣ ቂጧን፣ አፏን.፡. የፍሬዋ አፍ በእርግጥም ያልተለመደ ቅድ እንዳለው ልብ ያልኩት ዛሬ ነው፡፡ ዳር ዳሩን ዘፋፍ መስሎ በጠርዝ የተከበበው ፊቷ መካከል ላይ ከአራት አቅጣጫ የበቀለ



t.me/OLDBOOKSPDF

አራት ጥርስ ያለው አፍ። ፊቷ የካፖርት ቁልፍ ይመስላል። ብሩኬ ቀና ብሎ ወደተደረደሩት ዛፎች እያየ፡-

"እንዲህ ያለውን ግተር እዚች ኢምንት ሙዳይ ውስጥ ቋጥሮ ማስቀመጥ እንዴት ያለ ጥበብ ነው?" አለ።

ለራሱ እንደሚያወራ ቀጥሬው ልቡ ውስጥ ቁጭ ብዬ የማዳምጥ መሰለኝ። ነገር ግን በስካርፕ ተጠቅልሎ ጉማጅ ግንድ የመሰለ አንገቱን በቀስታ ወደኔ አዞረው።

"እነዚህ ጀብደኛ ዛፎች በዚህ ፍሬ. መውደቅ የቆሙ የድል አምዶች ናቸው። ግትርነታቸው ላይ ሞኛ ሞኝነት አለበትና እስኪገረሰሉ ድረስ መጋፈጥ እንጂ መሸሽ አማራጭ አይመስላቸውም።"

ንግግሩ ውስጥ የዛፎቹ ወገንተኝነት አለበት።

"ተመልከች፤ የቀበናን ወንዝ፤ ዛፎቹ ስር ስር እያለ በባልደረባነት ለፍልሚያ ውረድ እንውረድ ይላል። ቁርጡ ሲመጣ መሬት ለመሬት ለሽ ብሎ ዛፎቹን ለማስደብደብ።"

ስለማንነው የሚያወራው? እኔስ እነዚህ ተተንታኝ ወዳጆቹ ውስጥ አምስተኛ ሆኜ እኖር ይሆን? ስለእኔ ምን ያስባል? ምን ይላል? እንዴት ይገነዘበኛል? ለመጀመሪያ ጊዜ ጣዎሴ የሚለኝ ከእነሱ እንደ አንዱ ቆጥሮኝ መሰለኝ።

## 2

እዚያው በረንዳው ላይ ቆሜያለሁ...

...የአደራ ልክፍቴን እስታምማለሁ።

ጀንበሯ ቁልቁል የተደፋ የወርቅ ዝገዳ መስላለች። የወጨጫ ተራራ እንደ ወለላ ደርበብ ብሎ የሚወርደውን ዝልግልግ ብርሃን አፉን ከፍቶ ወደ ሆዱ ይልካል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የበረንዳችንን ተራዳ ቃቅሌ ዕድሜዋን በመንተራፈፍ፤ የምታራዝመውን ደንበር በትካዜ እያለሁ። እንዳማሩ መሞት የዘውትር ዕጣዋ መሆኑ ሆድን ይበላል። ይሄንን ሐዘን የሚያባብስ ህብረ ዜማ ከወንዙ፣ ከዛፉና ከነፋሱ ይንቆረቆራል። የራሱ የሆነ ዘለሰኛነት አለው። አልቅሽ አልቅሽ አለኝ።

ይሄንን ስሜቴን ለጓደኛዬ ለኤደን ስነግራት ከማዘን ይልቅ ከት ብላ ትስቅና "ሮንቅቀሻል ማለት ነው" ትለኛለች። ላለማመን እንደ ጨሌሌው እንደፋደፋለሁ። እንደዛፎቹ ግትር እሆናለሁ፣ እንደ ወንዙ እስለከለካለሁ...

"እንደኛ ብሩክ ዘመዴ ነው..." ታቋርጠኛለች።

"እሱን ተይው፣ የአያትሽ የሩቅ ዘመድ። ያውም ያልተረጋገጠ፣ በሀዘኔታ ያሳደገት ወይም ያስጠለለት..."

"ከዚያ በላይ ደግሞ ትልቅ ነው፤ በዕድሜ ቢያንስ..."

"ሲሆን፣ ሰውየው ተለሳልሶ ገብቷል፣ ገብቶልሻል።"

"ኤዲ፣ አንቺ ደሞ..."

የሽርደዳ ሳቋ ያሳምማል። እውነቱን ለመናገር ብሩክን አፍቅሬያለሁ ብዬ አላምንም። ግን ስለምን ዕድሜውን እንደ አንድ እንቅፋት አድርጌ አሰብኩት? ተናገርኩት? የከሐዲነት ስሜት ገብ አለብኝ። ብሩክ እኩያዬ፣ አብሮ አደጌ ይመስለኛል። እኔ ልጅ ሳለሁ እሱ ጉረምሳ ቢሆንም የፍላጎት ልዩነት አናሳይም ነበር። ሀሳቤን በአዋቂነት ቸልታ አያይብኝም ነበር። ሙሉ ቀልቡን ሰጥቶ ያደምጣል፣ ለሚያጓጓኝ ይጓጓል፤ ለሚያስደንቀኝ ይደነቃል... ይሄ ሁሉ ግን አላዋቂነቱን የሚያሳይ እንዳልሆነ የገባኝ ቆይቶ ነው። ግልገሏን በእኩያነት እየተላፋ ከቀበሮ እንደሚከላከል እረኛዬ ነበር ልበል?



t.me/OLDBOOKSPDF

"ኢክ ፍቅር ነው" የኢደን ድምፅ የሐሳቤ ጭራ ሆኖ ይከታተለኛል።

አስር ዓመት ቢሆነኝ ነው። ያኔ ብሩክ የአርት አስኩል ተማሪ ነበር። የትልቁ ቤት በረንዳ ላይ የስዕል ሰታውን ደርድሮ የጦር አዋጊ ይመስል አሻግሮ ይመለከታል። እግሩን ከፊት አድርጎ እጆቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ ከወፈጮዬ ተራራ ጋር የሀሳብ ሙግት ይገጥማል። አይኖቹን አጥብቦ ስንጥር የመሰለውን ሸንተረር ሳያቋርጥ እያጠና ይቆያል። ሲጨርስ የተወጠረው ሸራ ፊት ለፊት አግዳሚ ወንበሩን እንደ ፈረስ ተፈናጦ ይቀመጣል። የተራራውን ያህል ባዶው ሸራ ላይ አፍጥጦ ብዙ ይቆያል። ከዚያ ድንገት ሸራ ላይ ያረፈች ዝንብ ይገድል ይመስል በፍጥነት ብሩሹን አውጥቶ፤ ቀለሙን ነክሮ ቅጥ የሌለው መስመር ከወዲያ ወዲህ ያወናጭፋል። ቀና ብሎ ተራራውን ሳይመለከት፣ አእምሮው ውስጥ ከታተመው እያወጣ ስሎ ይጨርሳል። ራቅ… ቀረብ… እያለ ከተመለከተ በኋላ የበረንዳው አግዳሚ ላይ ወጥቶ ይቀመጣል። በቂጡ ተሽከርክሮ ፊቱን ወደ ውጭ በማድረግ እግሮቹን እያወዛወዘ ብሩሹን እንደ ሲጋራ ይዞ ወደ አፉ ወሰድ መለስ ያደርጋል።

ይሄኔ ጠጋ ብዬ ስዕሉን የመመልከት ዕድል ይገጥመኛል። ከሩቅ ስመለከተው ጨሌ የመሰሉ ጤዛዎች ሳይቀሩ ጥርት ብለው እንዳልታዩኝ ሁሉ ስቀርብ ደብዝዘው ቀለም ከቀለም ይደበላለቅና ቅጥ የሌለው ድሪቶ ብርድልብስ ይመስለኛል። መልሼ እራቅ እላለሁ።

"እንዴት ነው? ወደድሽው ወይስ ጠላሽው?" ይላል ብሩክ ጀርባውን እንደሰጠኝ መለስ ሳይል። ከሁኔታው ከነመኖሬም ልብ ያለ ስለማይመስለኝ እደነቃለሁ።

"ጣዎሲ፣ አስተያየት ስጪ እንጂ"

"ስቀርበው ጠላሁት፣ ስርቀው ወደድኩት"



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሩኬ ተስፈንጥሮ ከበረንዳው አግዳሚ ላይ መሬት ዱብ ይልና "ለነገሩ ጥሩ ስዕል አድናቂ ይወጣሻል፣ ስዕልና ሰው ራቅ ብለሽ ስታያቸው ነው የሚያምሩት። በጣም ጥቂቶቹ ስትቀርቢያቸው ያምሩ ይሆናል።" ፊት ለፊቴ ተንበርክኮ ትክሻና ትክሻዬን ይዞ ይመለከተኛል። ከእርጥቡ ሥዕል ይልቅ፣ ከቀለም ቁርቁሮዎቹ ይልቅ፣ እሱ ቀለም ቀለም ይሸታል። "አንድ አዲስ ጨዋታ ይገኝ መጥቻለሁ።"

"ምን?"

"ላሳይሽ አይደል"

ሁሉንም እዚያው በረንዳ ላይ ጥለን ወደሱ ክፍል እንገባለን። ግድግዳ ላይ ከተሰቀለው ኮት ኪስ ውስጥ አንድ ትልቅ ብርቱካን ያወጣና "ይቺን ብዪ" ይለኛል።

"ጨዋታው መብላት ነው?"

በመዳብ የተለበጠ የመሰለ ከንፈሩ ሸሽት ብሎ በመገረም ይስቅና "የጨዋታው አካል ነው" ይላል።

ለጨዋታው በመቸኮል ብርቱካኑን ከመርበትበት ጋር ልጬ መብላት እጀምራለሁ። ብሩኬ ሁኔታዬን እያየ ጭንቅላቱን እንጋሎ ይስቃል። አፌን በብርቱካን ዘለላ እየሞላሁና በላይ በላይ እየጨመርኩ በልቼ እጨርሳለሁ።

"በላ"

"ውሸቱን ነው፣ ቀማሴን ነው" ይለኛል እኔ እንደምሰው።

"እ-ማ-ማ!" እላለሁ ለማልቀስ እየዳዳኝ። እማማ የእኔን ጥሪ ሲጠባበቁ የነበሩ ይመስል የአባባን ጫማ እንዳደረጉ "ኩርኩፍ" እያሉ ይወጣሉ። የአባባን ሀሬ ቆዳ ጫማ ማድረግ ያዘወትራሉ። እግራቸው የጫማው ግማሽ ላይ ቀርቷል። ሠንድ እያቱ ከእሳቸው በቁመት እጅግ



t.me/OLDBOOKSPDF

አንሰው ሳለ ለምን በእግር መዳፍ እንደሚበልጧቸው ዘወትር የሚያስገርመኝ ነገር ነው።

"የት አባቷ ሆና ነው የምትጮኸው?" አሉ፤

ብሩኬ እየተሽቆጠቆጠ እንዳልናገር ይለምነኛል።

"ይሄ ብሩኬ አታሎ ብርቱካን ያበላኛል" አልኩ።

እያቱ "እንዴት ተጎዳሽ እቴ" እያሉ ወደቤት ተመለሱ

ኮርኮፍ፤ ኮርኮፍ፤ ኮርኮፍ፤ ኮርኮፍ...

ሰብቁ ስላልያዘልኝ ትንሽ አበሻሽቆኝ የብርቱካን ልጣጩን ሁለት ቦታ መደበ። አንዱን መደብ ይዞ ሌላኛውን ለእኔ አቀበለኝ።

"ምን ላድርገው?"

"ላሳይሽ ነው" ብሎ ከኪሱ ሁለት ቢክ እስክሪፕቶ አወጣ። መፃፊያውን ከነዘንጉ መዝዞ የአንዱን ጫፍ ክዳን ነቀለና ቀፎውን አስቀረው። የብርቱካን ልጣጩ ላይ የቀፎውን ሰፊ አፍ አስደግፎ በመጫን ሲያነሳው ብርቱካን ልጣጩ በክቡ ተከርክሞ ቀፎው ውስጥ ቀረ። በመፃፊያው የላስቲክ ዘንግ የቀፎውን ውስጥ ብርቱካን እየገፋ እየገፋ ጠባቡ አፍጋ አድርሶ ጫፉ ላይ አቆመው። እንደ ሽጉጥ አፈሙዝ ወደኔ ደቅኖ ሲገፋት የብርቱካኗ ልጣጪ እንደ ጥይት ጮኸ ደረቴ ላይ መታችኝ። አያምም፤ ያልጠበኩት ስለነበር ደነገጥኩ። ብሩኬ ሳቀ።

የዚያን ቀን ግቢ ለግቢ እየተባረርን ስንታኮስ ዋልን። ወንድ አያቴ አባሮ ወይ ተደብቆ በመተኮስ የመታውን ለማድነቅ የትንባሆ መጠጫ ኩርቢታቸውን ከአፋቸው ነቅለው "ይሄ ነው ጀግና" ይላሉ። እናቴ መደነቅም ሆነ መሰልቸት ሳይነበብባት ትመለከተናለች። እሷ ድሄው ናት። ፊቷ ልሙጥ ነው። ሲስቅም ሆነ ሲኮሳ አይታይም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሴት አያቴ ቤት ለቤት ሲንጉዳጉዱ ይቆዩና ወጣ ብለው ተመልሰው ኮርኮፍ፣ ኮርኮፍ እያሉ ይገባሉ።

## 3

ደስታ የማውቀው ከእንዲህ ያሉ ትዝታዎች ጋር ስሆን ነው።

("ፎንቅቀሽል ማለት ነው" ኢዱ.)

አካባቢው በለዘብተኛ ምህላ ውስጥ ያለ ይመስላል። በዚህ ምህላ ውስጥ አንዱ አሸብሻቢ የእኔ ልብ ይመስለኛል። ከወደ ሩቅ የከብቶች ድምፅ ይሰማል። አልፎ አልፎ ደግሞ ጀግንነቱን ለባለቤቱ ለማሳየት የሚሞክር ዋሾ ውሻ ይጮኻል። እሱን ተከትለው ከወዲያና ከወዲህ የሚባዝኑ ውሾች በይሆናል የሳሉትን ጅብ በድምፅ ለመክበብና ለማዋከብ የሚሞክሩ ያስመስላቸዋል። ለዚህ ያቀበና ትዕይንት የበላይ ጠባቂነት ይሰማኛል። እኔ ያልታደምኩ ዕለት ለፍሲጋ ዛፉ እንደ ቀጭኔ ጉንበስ፣ ወንዙ እንደገመምተኛ ከራስጌው ቀና፣ ነፋሱ እንደጠራኝ ቆም የሚሉ ይመስለኛል። እናም ተሰምጧቸው ስልት የማይደናቀፍ።

ጅንበሯ ወጋገኗን ትታ ጠልቃለች። በውሾቹ መዛዘን መካከል የተቆራረጠ ቀረርቶ ይሰማኛል። በስካር የሚወናከር ሰው ለፍርሃቱ የሚያሰማው ማጀገኛ ፉከራ እንደሆን ያስታውቃል። አባ ገልገሌ ነው፤ አውቄዋለሁ። የሴት አያቴ ታናሽ ወንድም። የሚኖረው እኛጋ ነው። ሁሌም አምሽቶ ስለሚመጣ የአካባቢው ሰው "አባ ገልገሌ" ይለዋል። "የምሽት አባት" ማለት ነው። ዛሬ በጊዜ ተጠናቋል።

በሰተግራ አንድ ሁለት ደርባባ ቤቶች አልፉ ያለችው ጥርጊያ መንገድ የበሃ ድንጋይ ተነጥፎባታል። ከሩቅ ሲያይዋት የብር ዘንዶ ትመስላለች። አባ ገልገሌ አስር ጊዜ ጋቢውን እያጣፋና ቆም ብሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዙሪያውን እየገላመጠ ከወደ የካ ሚካኤል አቅጣጫ ይመጣል:: አባባሉው ጭር በማለቱ በጫማው የሚከረሻሽመው በሃ ድንጋይ ይሰማኛል::

"ደጋፊ መስሎ ገፍታሪ፣ አቃፊ መስሎ በርባሪ" ይላል:: "የማያድግ ልጅ እናቱ ጀርባ ላይ ሆኖ ያፏጫል" ይላል፣ ዘልማዱ ነው:: ድምፁን ሲሰሙ ሴት አያቴ ስለሚወጡ እንቅልፍ ወሰደኝም፣ አልወሰደኝም ወደ ክፍሌ ለመግባት ወሰንኩ:: ገና በረንዳውን ለቅቄ ወደ ጓሮ የሚወስደውን አቅጣጫ ስይዝ የትልቁ ቤት በር ተከፍቶ "ኮርኮፍ ኮርኮፍ" የሚል ድምፅ ሰማሁ::

"ወይኔት ነው? ገብተሽ ራትሽን አትበይም?"

"በቃኝ ልተኛ"

"ምን ሆነሻል ሰሞኑን? አልበዛም?"

("ፎንቅቃለች ማዘር" ኤዲ)

ወደ ክፍሌ አመራሁ::

## 4

ወደ መኝታ ክፍሌ ስገባ እናቴ ሸው አለችኝ:: ይሄ ክፍል የእናቴ መጠለያ ነበር:: አንዳንድ ዕቃዎቿን ወርሼ እዚሁ ክፍል ውስጥ ናቸው:: ባለ ረጅም መስታወት መኳኳያ ኮመዲኖዋ አለ:: መለስተኛ የልብስ ቁም ሳጥኗም እንዲሁ ከተደገፈው ግድግዳ ንቅንቅ ሳይል አለ:: አንዳንድ ጊዜ እሷም ያለች ይመስለኛል:: እዚህ አያቶቼ ግቢ ውስጥ የኖረችው በመንፈስ ህልውና ነው ማለት እችላለሁ:: ስትሄድ ኮቴዋ አይሰማም:: ለዚህ ዓለም መቀትና ቅዝቃዜ ምንም አይነት ምላሽ ስትሰጥ አይታይም:: አትስቅም፣ አታለቅስም:: ሆዷ ተከፍቶ ስትበላና ስትጠጣ አጋጥሞኝ አያውቅም::



t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅ እያለሁ በየሄደችበት ሁሉ ታስከትለኝ ነበር። ቤተ-ክርስቲያን፣ ሰውጋ፣ ወፍጮ ቤት፣ ገበያ... አብሬአት ነኝ። ሁለታችን አብረን ስመሄድ እንኳን ባንፈልግ አያቶቼ በጅ አይሉም ነበር። ከሄድንበት ስንመለስ አያቶቼ እኔን ይመረምራሉ።

"የት የት ሄዳችሁ?" ሲት አያቴ ሲጠይቁ ወንድ አያቴ የትምባሆ መጠጫ ኩርቢታቸውን አፋቸው ውስጥ ወትፈው ጆሮአቸውን ጣል ያደርጋሉ። "እንቺ ስትጫወቺ ትታሽ ሀርም አላለች?... አይ ዋሽ... ቀጣፊ!... ካጠገቧም ንትንቅ አላልሽ?..." ሴት አያቴ በሁለት ጉልበቶቻቸው ተወጥሮ የጠነከረ ቀሚሳቸው ወገቤ ላይ እንደ አጠና ተጋድሞ ይመረምሩኛል። ወንድ አያቴ የትምባሆ ጢሱ ሲጋርዳቸው ኩርቢታቸውን በያዙበት እጃቸው እያራገቡ ከፊታቸው ላይ ገለል ያደርጋሉ።

ሁለቱ አያቶቼ ለሙት አባቴ ፋንታ ቀንተው የእናቴን መግቢያ መውጫ በእኔ ለመድፈን እንደሚሞክሩ የገባኝ አሁን አሁን ነው። አባቴን በውል አውቀው ነበር ለማለት ይቸግረኛል። አብዛኛውን የፊልድ ሥራ ስለሚሰራ በጋ ሆነ ክረምት ከጫማው ላይ የማያራግፈው ጭቃ እያጣም ነበር። ወደፊልድ ሲሄድ እኔና እናቴን ከቤታችን አውጥቶ ወላጆቹ ጋ ያስቀምጠን ነበር። ወር ቆየ ሁለት ወር እንጠብቀዋለን። ከፊልድ ሲመጣ የጫማውን ጭቃ እያራገፈ ይዞ የመጣውን ዕቃ ሁሉ ለወላጆቹ ሰጥቶ ሦስታችን ወደ ቤታችን እንመለሳለን። ለእኛ የሚያስፈልገን የሚገዛው ከዛ በኋላ ነው።

ይሄንን የአባቴን አድራጎት እናቴ ተቃውማው ሰምቼ አላውቅም። እኔና እሷ አንድ ነን። እሱ የሚሻውን መፈጸም። የትኛውንም በደል እንደ ሰጎንጅ መጥጦ የሚያስቀር ፊት ነበራት። መከፋትን ብቻ ሳይሆን መደሰትንም ፊቷ አስርጎ ያስቀር ነበር። የስሜት ለውጧን ለማየት፣ ሆን ብዬ ስበጠብጣት "ተይ" ትላለች እንጂ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፊቷ ላይ ምንም አይነበብም። ሴት አያቴ ከትልቁ ቤት "ኮርኮፍ ኮርኮፍ" እያሉ ሲመጡ አረብሻዬን አቆማለሁ።

"ምን መጣ ልጄ? ይቺ ልጅ ባሊጋለች" ይሉና በኮርኮፍ ይመሰሳሉ። አባቴ ለመጨረሻ ጊዜ ወደፊልድ ሲሄድ አራት አመት ቢሆነኝ ነው። የሚቆየው ለረጅም ጊዜ ስለነበር መኖሪያ ቤታችንን አከራይቶት እኛን የተለመደው ወላጆቹ ቤት አስቀመጠን። ያልገባኝን አንዳች ነገር እየተናገረ እናትና አባቱን ካስጠነቀቀ በኋላ ከግቢ ውጭ የቆመችው እንደሚማለው ጭቃ ለበስ መኪና ላይ ተሳፈረ። የቀበናን ወንዝ ዳር ዳር ይዞ ወደ የካ ሚካኤል የሚወስደውን የበሃ ድንጋይ ጥርጊያ ተከተለ። በረንዳ ላይ ሆኜ መኪናው ለአይን እስኪርቅ ሸኘሁት።

ከወር ይሁን ከሁለት ወር በኋላ መርዶው መጣ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የየካ አቅጣጫ ጥርጊያ ወደ ሞት አገር መሄጃ መንገድ ይመስለኝ ነበር። እናቴና እኔ ወደ መኖሪያ ቤታችን አልተመለስንም። አንድ ቀን ድንገት

"ቤቲ" አለችኝ

"እ" አልኳት ጨዋታዬን ሳላቋርጥ

"ከእኔና ከእማማ ከማን ጋር ብትሆኚ ይሻልሻል?"

"ከሁለታችሁም ጋር" በግዴለሽነት

"አንዳችንን ምረጪ ብትባይስ?" ፊቷ ብቻ ሳይሆን ድምጿም ቅዝቅዝ ያለ በድን ነው።

"እማማ ጋ"

እንደ ቀልድ የተፈተለከች ይቺ ቃል እንደ ጥይት ለዘልአለም የመለያያ ጦስ ትሆናለች ብዬ አልገመትኩም ነበር። እንደ ቀንም ሳትሰቅ፣ ሳታለቅስ እንደ መንፈስ ግቢያችን ውስጥ ከወዲያ ወዲህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማለቷን ቀጠለች። እንደ ጀንበር መጥፊያዋ ላይ እሰሁ እሰሁ ማለት አብዝታ ነበር። ከእሷ ጋር ስሆን እቅፍ ታደርገኝ ነበር። አንድ ጠዋት ከቤት ወጥታ ጠፋች፣ ድምጿ ሳይሰማ ሰባት አመት ሆኗታል። አንዳንድ ቀን በህልሜ ጥቁት ጥሬ በነጠላዋ ላይ ቋጥራ ጭው ባለ በረሃ ላይ ስትጓዝ አያታለሁ። መንፈስ ቅልቅል አካሄዷ አልተለወጠም። በሚንቀለቀለው በበረሃ ግልብልባት እየተንቀጠቀጠች እስክትጠፋ አያታለሁ።

## 5

ሲነጋጋ አሸልቦኝ ጥሯል። የአያቴ ጥሪ ከእንቅልፍ እንጦሮጦስ ሰቦ አወጣኝ

"አንቺ ጋድሚያ፣ ስልክ ይፈልግልሻል"

ኤዲ መሆን አለባት። ብሩኬ ትናንት ደውሎ ነበር። ብዙ አላወራንም። መናገር የፈለኩት ነበር፣ ምን እንደሆነ ግን አላወኩትም። ባይዘጋው እነግረው ነበር ብዬ አስባለሁ እንጂ ምን እንደምነግረው አልተገለጠልኝም። ባልዘጋው... ባልዘጋው... ባልዘጋው፣ ዘጋው።

እየተግተለተልኩ ከአልጋ ተነሳሁ። ልብሴን እንደለበስኩ ነበር። ፎጣ አንስቼ ትከሻዬ ላይ ደርቤ ወጣሁ። ኤዲ ይሄኔ ወይ ማትሪክ ወጥቷል ልትል ነው፣ ወይ ጠፋሽ፣ ወይ... ደንዳናው ስልክ ሳሎን ነው። ደባደቦ እጀታው ከማደሪያው ተነስቶ ጠረጴዛው ላይ በአፉ ተደፍቷል። አነሳሁት።

"ሐሎ?"

"ባምሴ፣ አስጠበቅሽኝ"

ትርትር ነው? ስንጥቅ? ምንድነው የሚባለው?



t.me/OLDBOOKSPDF

"አዲስ አበባ መጥቻለሁ"

ሌላ ትርትር፣ ሌላ ሰንጥቅ

"ኢ-ኢ-እንዴት? እ? ምነው?"

"ካንቺጋ ማውራት ያለብኝ ነገር አለ። ድብብቁ ቢበቃን ጥሩ ነው"

ማውራት? ድብብቅ? ምን? ግራ ተጋባሁ።

("ይሄኔ አሉም ሮንቅቋል" - ኢዲ)

ደስታም ቢሆን በእንዲህ ያለ ሁኔታ ማጋጠም የለበትም ስል አሰብኩ። አትሉ የማባሉ ነገር ከማምት ሳይገባ የደስታው ድንገተኛነትና ከመጠን በላይ መሆን ለስቃይ የቀረበ ህመም አለው። ስልኩን እስቀምጠው ስዞር እያቱ በበሩ አንፃር መስኮቱ ስር አደግድገው ቆመው ዳዊት ይደገሙ ኖሯል። በነፍስ አባት ግዝት ያልጣሏት የትንባሆ መጠጫ ኩርቢታቸው ፊት ለፊት ጠረጴዛ ላይ እንደ ውሻ አድፍጣ ተኛታለች። እዚህ ቤት የቀረቻቸው ንብረት እሷ ብቻ ስለምትመስለኝ ያሳዝኑኛል።

ዛሬ ብሩኬን ፊት ለፊት ላገኘው ነው። ለመጨረሻ ጊዜ ከተገናኘን ድፍን ሦስት ወር ይሆናል። ፍርሃት ፍርሃት አለኝ ልበል?

("ሮንቅቀሽ ነው!" - ኢዲ)

ወደ ክፍሌ ተመልሼ አልጋ ላይ ቁጭ አልኩ። ሌላ ጊዜ ቢሆን ብሩኬ የሚመጣው የአጋማሽ ፈተና ተሰጥቶ ትምህርት ቤቱ ለአጭር ጊዜ ሲዘጋና ለክረምት ነበር። በእርግጥም የድብብቆሹን ሰድሜ ለማሳጠር ቆርጧል ማለት ነው። በፊት ክረምት ሲመጣ እማማ ፊት እስኪነሱት ጊዜ ድረስ እዚሁ እኛጋ አርፎ የቀበና ዙሪያ ገባዋን እየተዟዟረ ስዕል ያነሳ ነበር። ከየአቅጣጫው መጥተው ቀበና ውሃ ላይ የሚዋኙትን ልጆች እሩቅ ብሎ ይስላቸው ነበር። ብዙ የተራቆቱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከራር ደረቶች፣ ቆመው፣ ውሃ ውስጥ ሆነው፣ በደረታቸው ተንበልብለው፣ ሲሯሯጡ፣ ሲላፉ... የሚያሳዩ ስዕሎች ነበሩት። ዋና የሚፈሩ ልጆች የዋናተኞቹን ልብስ ከምሪው ሲጠብቁ ሁሉ ስሏቸዋል።

ስዕሉን ሰርቶ ሲጨርስ በትዕግሥት የመጠበቴን ካሣ እንደ ህፃን ሆኖ ያጫውተኝ ነበር። ጨዋታችን ጭቃ ላይ እስከ መንደባለል የቀበጠ ነው። ብዙ የልጆች ጨዋታ ያውቅ ነበር። በክረምት ወራት ጭቃውን እንደ ድስት አጉድጉዶ ከሰራ በኋላ ጠፍጣፋ እለት ላይ በአፉ ወርውሮ ሲደፋው እንደ ጅራፍ ይጮህ ነበር። ድንጋጤ፣ ከዛ መገረም፣ ከዛ ሳቅ... አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፌስታል ቀጣጥሎ ያስርና ጫፍ ላይ ድንጋይ ቋጥሮ በኃይል ያሽከረክረዋል። እንደ ንብ መንጋ ሹሹሹ... ይላል። እንዲሁ ቁራጭ ቦንዳ በሲቶ ያስርና በማሽከርከር ይሄንኑ ድምፅ ይፈጥር ነበር። የጨዋታው አይነት ከእኔ ዕድሜ ጋር እየተለወጠና እየበሰለ ይሄድ ነበር እንጂ እዚያው አይቀርም። የየዕድሜ እርከኖቼ ሁሉ ብቁ ጓደኛ መሆን መቻሉ ይገርመኛል።

በመጨረሻ ባለፉት ሁለትና ሦስት አመታት ውስጥ የእማማ ፊት መንሳት እያየለ መጣ። እኔ ባልናገራቸውም ውስጥ ውስጡን እትከነክን ነበር።

"ለምን?"

ብሩኬ ነበር ግልጥልጥ አድርጎ ያስረዳኝ። "ለአባባ የማደላ፣ የአባባ ወገን ስለምመስላቸው ነው" አለኝ።

"እንዴት?" አልኩት

"ቡ-ታ-እ፣ በፊት የዚህ ቤት ፈላጭ ቆራጭ አባባ ነበሩ። እማማ ይሄን አምነው ኖረዋል። በኋላ ላይ ልጆቻቸው እራሳቸውን እየቻሉና ከለላ እየሆኑ ሲመጡ እማማ የበላይ ለመሆን ‹ቀዝቃዛ ጦርነት›



t.me/OLDBOOKSPDF

ጀመሩ። አባባ እንደ ድሮው ለቆሜ ሲሉ ልጆቹ መሀከል ይገባሉ። ‹የድሮው አይበቃም!?› ይላሉ። ስለዚህ ነገሩ እየተገለበጠ አባባ የቤት ውስጥ ሥልጣናቸውን አጡ።"

"እና? አንተ ምን አደረክ?"

ብሩኬ ፊገግ ይልና አየካርፑን አስተካክሎ "አባባ ትንሽም የሚያልጉመጉሙት እኔን ተመክተው ይመስላቸዋል። ስለዚህ ለእማማ ፍፁማዊ ሥልጣን የኔኑ አቋሜው ላይ አለመኖር ወሳኝ ነው።"

ጦርነት፣ ፖለቲካ፣ ወሬሬ... መለሱኝ ግራ ተጋባሁ።

"የትም ቤት ያለ ነው። ‹ልጅ ደረሰ፣ ቤት ፈረሰ› የሚባለው ለዚህ ነው። እንደማገኘውም የአውሬ ማህበር በሰው ልጆችም ዘንድ እናት ልጆቿ እስኪያድጉ በልምምጥ ትኖርና ሲደርሱላት የበላይነቷን ትቆናጠጣለች።"

የብሩኬ መፈላሰፍ መሰለኝ ነበር። ብሩኬ በእማማ ግልምጫ እግር ከቀነሰ በኋላ አንድ ቀን አባባ በመትከንከን እንዲህ አሉኝ።

"በገዛ ቤቴ የማላገዝ፣ የማልናገዝዝ ሆኛለሁ። ቢሰጡኝ የምበላ፣ ቢከለክሉኝ ጦሜን የማድር። አየሽ አንድ ተረት አለ። በር ሲንኳኳ ‹የማነህ ዘመድ› ትላለች ሴት፣ ‹የወንድ› ይላል፣ ‹በዓይንህ አመድ፣ ይፈድፍድህ ብርድ፣›፤ አሁንም ይንኳኳል ‹የማነህ ዘመድ?› ትላለች ‹የሴት› ይላል። ‹ግባ ከማጀት፣ ይቅረብልህ ፍትፍት፣ ይሙቅህ እሳት› ለካ ተረት አልነበረምና።"

ጉልበታቸውን አዚያው የትንባሆአቸው ኩርቢት ላይ ለማሳየት ማግ ማግ ቢያደርጉ ጭሱ ስለመከነባቸው ውስጡን አይተው ትምባሆ ለመቀየር ወደ መኝታ ቤት ሄዱ። እኔንንኳ አምጪ ብለው ለማዘዝ አለመሞከራቸው ጠቅላላውን ሽንፈት ውስጥ መሆናቸውን ጠቆመኝና አዘንኩ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 6

ዛሬ ባላሰብኩት አካኋኋንና ባልጠበኩት ሁኔታ ብሩኬን ላገኘው ነው።

የተለከፍኩት በእሱ እንደሆነ ሁሉ በትዝታ ስሆረው እውላለሁ። ጥንቢራዬ እስኪዞር እደጋግመዋለሁ። ማሰቤን ትቼ ባወራ ስንቱ በሰለቸኝ ነበር።

("ፉንቅቅቅቅቅ....." ኢዲ)

ወቅቱ ክረምት ነበር። እናቴ በሯ ላይ በበርጩማ ተቀምጣለች። በረንዳው ላይ ስጫወት ቆይቼ ወደ ጓሮ ስዞር ብሩኬ የተወጠረ ሸራውን ማስደገፊያ የክፍሉ በር ላይ ገባ አድርጎ አቁሞት አየሁ። ትርጉም አልባ መስመሮች እየሞነጫጨረ ራቅ ቀረብ ይላል። ራቅ ሲል የጣረያው ጠፈጠፍ ጀርባው ላይ እየነጠረ የፈንዲሻ ቅርፅ ይሰራል። መስመሮቹ እንደ ወጨፎ ከቀኝ ወደ ግራ ፀሰያፍ የሚዘንቡ ነበሩ። መስመሮቹን ከማድመቅ ይልቅ ዳር ዳሩን ቱቢት በመሰለ ቀለም ሲያጀበጀብ መቆየቱ ትዕግሥት አስቆራጭ ቢሆንብኝም መከታተሌን ቀጠልኩ። ዳር ዳሩን የሚያንጃብበው ቀለም ለነስ ትርጉም ኖሮታል። ትንሽ አሎሎ ትልቁ አሎሎ ላይ የተቀመጠ መስሎ እየደመቀ የመጣው የሸራው መካከለኛ ክፍል በጥቂት መነካካት በተፈጠሩ መስመሮች ቁጭ ያለች ሴት ሆነ።

ገረመኝ። በመነካካቱ ቀጥሏል። ጥቂት መስመሮች ሲጨመሩበት ያቺ ቁጭ ያለች ሴት እናቴን መስላ አረፈችው። እጁን ትቼ የብሩኬን ፊት ለማየት ተመኘሁ። አንዴም ወደ እናቴ አይመለከትም። አእምሮው ውስጥ ከትኳት ጨርሷል። ከዛ እያወጣ ነበር የሚስላት። እናቴንና ስዕሉን እያስተያየሁ በመደነቁ ቀጠልኩ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የቱቤት ድንኳን ውስጥ የተቀመጠች የሚመስለው የእናቴ ምስል ቀለሞች እየተደባለቁ ነፍስ ሲዘሩባት ብሩኬ ራቅ ቀረብ እያለ ያጤነዋል። ጠፊጠፉን ከቁብ አልቆጠረውም። ከደቂቃ በኋላ የትልቁን ቤት ተደግፎ ብሩሹን እንደ ሲጋራ አፉ ላይ ሰገተ።

ሴቲቱ ቁርጥ እናቴን። ብቻ የሰሰጰ እናቴ እያለቀሰች ነበር። ሳይታወቀኝ "እንዴ?" ስል አንባረቅሁ።

ብሩኬ "ምነው?" እንደማለት ዞሮ አየኝ።

"ውሸት!" አልኩ

"ምን?"

"እናቴ አታለቅስም"

ብሩኬ የብሩሹን ሰደፍ መልሶ ወደ አፉ ብሎ ለራሱ የሚመስል ቃል ተናገረ። "ለቅሶዋን ልጅ አያየውም"

በዚህ መሀከል እናቴ ቀና ብላ ሁለታችንንም ተመለከተችን። እኔ ግራ በመጋባት ልጅ ስለማያየው ለቅሶ ነበር የማስበው። ሮጬ ወደ ትልቁ ቤት ገብቼ እማማን ጠየኩ። "እማማ፣ እማማ ልጅ የማያየው ለቅሶ አለ?"

"ምን ትላለች ይቺ፣ ኋላ ልጅ የሚያየው ለቅሶ ነው ያለው? ቀብር ጨዋታ መሆኑ ላት?" በኮርኮፍ ወደ ጓዳ ገቡ።

ከዚህ ዕለት በኋላ የማይጌ ማረጋገጫውና የእናቴን እንባ ፊቷ ላይ ለማየት መጣርን ልምድ አደረኩ። ይሄንን ጥረቴን ተረድቶ ፈገግ የሚለው ብሩኬ ብቻ ነበር።

"አድገሽ እንባው የሚታይሽ ቀን እኔ እነግርሻለሁ" ይለኛል።

የእናቴ እንባ እንደ ውሃ ውስጥ ለውስጥ ይሰለከለክ ይመስል ምንጭ ሆኖ ጉንጯን ፈንቅሎ የሚወጣበትን ቀን እጠባበቅ ጀመር።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንባው መንጭቶ ሳላየው ድንገት ተነስታ ጠፋች። የምታስትስበት ቦታ ፍለጋ ይሆን?

## 7

በብሩክ ትዝታ ለመማለል ስሞክር ሐሳቤ ለእናቱ ሲያቀብለኝ ከባድ ሐዘን ልቤ ላይ ያወድቃል። ስለምን መለስ ብላ አልተመለከተችም? እንደ ሎሚ ሚስት የፈለው እምድ የመሆን ንግር ይሂት? ከልጅ በላይ ምን አለ? አንድ ቀን እንዲህ የመረረ ወቀሳ እናቱ ላይ ሰነዘርኩ።

ብሩክ አንገቱ ላይ ያሰረውን ስካርብ ደርቦ ደራርቦ ስለጠመጠመው ጎማ አንገት መሰለ።

"ነገሮችን ከራስሽ አንፃር ብቻ አትይ። ከእናትሽም ወገን ሆነሽ ለመገንዘብ ሞክሪ። ለጎጆዋ እንዳልለፋች፣ ለትዳሯ እንዳልማሰነች በስተመጨረሻ ሆዷን በጥወራ የምታሸንፍ ሬት አይቶ ነዋሪ ተደረገች። የቁም እስረኛ"

"እንዴት? ለምን?..." የምለው ጠፋኝ።

"አባትሽ ሁሉንም ሀብት በእናቱ ሥም አድርጎ ነበር። ሲቀር ቀረ። ባዶ እጅና ልጅ። ላንቺ ስትል ስድስት ዓመት በነፃ ተገዛች።"

ተሰበርኩ። ብሩክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኃይል ተሳተመኝ። እንባዬ ቅልብሽ አለኝ። ደካማነቴ ካደፈጠበት ብቅ ብሎ ገብ አለብኝ። "እኔም ከዳኋት"

## 8

ብሩኬን በዚህ ስሜት ሄጄ እንዳላገኘው ፈራሁ። ብሩኬ ለእኔ ይሄ አይደለም። ደስታ፣ ፍስሃ፣ ዕውቀት፣ ምጥቀት... ነው። ደግነት፣ ሩሁሩሁነት፣ አለኝታነት፣ ውደታነት ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

("ሲሰቱ ፎንትቶሻል" - ኢዲ)

ለእሱ መማሰል ኩራት ነው። የዕድት አከሊል።

("እኮ! ፍትር ነው ጨዋታው" - ኢዲ)

የብሩኪ በአካል አጠገብ መገኘት አይደለም። እንዳለ ማሰብ ዋስትና ነው። የቆምኩበት ቆሟል ብሎ ማሰብ... የተደገፍኩትን ተደግፏል ብሎ ማመን... የማየውን ያያል ብሎ መደምደም... ቀለም ቀለም እየሸተተኝ ነው ብሎ መተበል... ያኔ እርሱ ይናገራል።

"እየሸት ጀንበሯን? የወርቅ ሰሜን የሚጠለባት የቤተ መቅደስ ማጥንት ትመስላለች። አድማሱ በሚትጉለጉል የወርቅ ጢስ ታፍኗል። ያንን አቋርጠን ብናልፍ ጢሱ ተላክኮብን የወርቅ ሜእት መስለን እንመለስ ነበር።"

"ከዛስ?" እለዋለሁ።

"ከዛማ፣ ወደ መኝታ ቤታችን ገብተን ዝናብ እንደደበደበው ውሻ ሰውነታችንን እናርገፈግፋለን። እንደ ዛፍ ቅርፊት እላያችን ላይ የተንከረፈፈው የወርቅ ልስን የአበባ ርጋፊ መስሎ ወለሉን ይሞላዋል።"

"ከዛስ?"

"ከዛማ አልጋችን ለምናችን? የወርቅ ጉዝጓዛችን ላይ እንተኛለን። ጠዋት ስንነቃ ልናባው እንችል ይሆናል። ግድ የለንም። የዕለት ወርቃችንን አይንፈገን እንጂ አመሻሽ ጠብቀን ወደ ጀንበር መጥለቂያ እ-ብ-ስ።"

ዘወር ብዬ አየዋለሁ። የተጉሳቆለ ቀይ ዳማ ፊቱ ከበሰለ ሽክላ የተቀረፀ አስመስሎታል። ኮስማናነቱ ለአይኔ ጉርሻ አመቻችቶታል። የተሰማኝን ደስታ ያህል የቀበጠ ማቀፍ ማከናወን አለመቻሌ ብሶት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀሰቀሰብኝ። ወደ ጀንበሯ መለስ ብዬ የመጣብኝን እንባ ለመዋጥ እታገላለሁ። እፍንጫዬ አሱጋ ቀርቷል። ቀለም - ቀለም...

"እማልክቱ ዘና ማለት ሲያምራቸው ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ ነበር የተባለው እውነት ከሆነ ያ ቦታ ቀበና መሆን አለበት።"

ሳቅ ይከጅለኛል የእኔ ነገር

"ለዚህ የዓይን እማኝ ነኝ። አይኑ-ስውሩ ሆሜር የእኔን እማኝነት ተገን አድርጐ ነው ትኔውን ያቨገኑደገደው። አማልክቶቹ እንደ ቁራ አዚች እኛ ዛኒጋባ ላይ አርፈው በእራሳቸው ተአምር ይደነቁ ነበር"

"መደነቅ ብቻ?"

"ምን አስቸከለሽ፣ ከመጠነኛ መደነቆች በኋላ እራሳቸውን ሀመገሰጥ ከከንፎቻቸው ብብት ፆር የወርቅ ብሩሽና ቀለም ያወጣሉ። አድማሱን በወርቃማው ሲያቀነጀጁ ይቆዩና በገዛ ተአምራቸው መደነቁ ሲገድላቸው ሲሆን ይበርራሉ።"

"እማላክቶች ሰዓሊዎች ነበሩ?"

"እንግዲያስ? ሰዓሊዎችም አማልክቶች ናቸው።"

ኩት ብዬ እስቃለሁ። የሀሳብ ልፊያችን የስሜት ቃናው እየተለወጠ መጣ ይሆን? አይኖቹ እንባ አቅርረው ያንሀባርቁ ነበር።

## 9

አሁን ስሜቴ ደህና ነው። ብሩኬን ማግኘት እችላለሁ። ስለድብብቆሹ ለመስማት ዝግጁ ነኝ። ግን ምን? የምን ድብብቆሽ?

## 10

ሾላ የተላፈርኩት ታክሲ የራስ መኮንን ድልድይን አልፎ አፍንጫውን ወደ ፒያሳ ሲቀስር መላ ሰውነቴ ተሸበረ። እኔና ብሩኬ ምን አይነት ድብብቆሽ ውስጥ ነበርን?



t.me/OLDBOOKSPDF

("የፍቅር የፍቅር ነዋ! - ሌዲ")

ምን ዓይነት ስሜት ውስጥ እንደነበርኩ ያውቅ ነበር ማለት ነው? እንዲያ ከሆነ አሁን ምን ሲሉኝ ነው? እየተረተርኩ ያለሁት የነገር ሜዳ አስፈራኝ፡፡ ሰዓቴን መልከት ሳደርግ ገና አስር ተኩል ነው፡፡ ታክሲው በትንሽ ደቂቃ ውስጥ መሐል ፒያሳ ደርሶ ውረ- ይለኛል፡፡

"ወራጅ!" አልኩ ድንገት፡፡ ብሬቴሽ ካውንስል ህንፃ ፊት ለፊት አወረደኝ፡፡ ቀስ እያልኩ በእግሬ ወደ ቀጠሮዬ ቤት ማምራት ይሻለኛል፡፡ በሐያዎ አተቡት ላይ የተሰሩት ፎቆች ስለሞሏት መንገዱ ላይ ድርብብ ያለ ጥላ ፈስሶበታል፡፡ የፒያሳ ጫጫታ ለጉድ ነው፡፡ ፒያሳ ከቀበና ጋር በእናት አትገናኝ ይመስል ጠባዮቸው ለየቅል ነው፡፡ የቀበናን ዛፎች እዚህ ስልክ እንጨት ተክቷቸዋል፤ የቀበናን ወንዝ እዚህ "ሽንጣም" አውቶቡሶች ይተውኗቸዋል፤ በውሾቹ ፋንታ አውቶሞቢሎች ይዛዝናሉ፤ የቀበናዋን ወጨጫ ጎረምሶቹ የፒያሳ ፎቆች ተፎካክረው አሸንፈዋታል፡፡ የፒያሳ ሰው ሰራሽ ጀንበር ግባት በፎቆቹ አብረት እንደ ደሃ ሥርዓተ ቀብር ይፋጠናል፡፡ ቢያንስ ለሁለት ወር ወደ ከተማ ዝር አላልኩም፡፡ በደሜ የናኘው የቀበና ድባብ በፒያሳ ቅሬ ባህሪ ደፍርሶ ተረበሸኩ፡፡

"ሰዓሊ የተፈጥሮ ጥገኛ ነው" ይላል ብሩክ፡፡ "ሰው ሰራሹን ነገር እንኳን ከተፈጥሯዊ ባህሪ አንፃር ነው ማየት ያለበት፡፡"

ምን ማለት ይሆን? ያም ሆነ ይህ እኔም የተፈጥሮ ጥገኛ መሆኔን ዛሬ አረጋግጫለሁ፡፡ ሰው ሰራሿን ፒያሳ ከተፈጥሯዊ ባህሪ አንፃር እንዴት ማየት እንደሚቻል ግራ ያጋባል፡፡

ሲኒማ ኢትዮጵያ ደረስኩ፡፡ ቀጠሯችን ከርባው ላይ የሆነፃው ተረከዝ መስላ የተወሸቀችው ሰው ሰራሽ ዋሻ ውስጥ ነው፡፡ "ዘ-ኬቭ"



t.me/OLDBOOKSPDF

ዶቺን ቤት ብሩክ ይወዳታል፡፡ ገብቼ አይኔን ከቤቱ ጭለማ ጋር ለማለማመድ እጨንቁሬ ቆምኩ፡፡ እንደ ነጭ እርግብ ክንፍ የሚወለበለብ ነገር አይቼ ወደዛ አተኮርኩ፡፡ ብሩክ ነበር የያዘውን መፅሐፍ እያወለበለበ የሚጠራኝ፡፡ መሀከለኛውን ጠረጴዛ ከከበቡት አራት ወንበሮች ፊቱን ለበር አመቻችቶ ተቀምጧል፡፡

አጠገቡ ደርሼ ስቆም አንገቱ ውስጥ ፊቴን ቀብሮ ጭምቅ የማድረግ ያህል አቀፈኝ፡፡ ቀለም ቀለም ይሸታል፡፡ ልምዱ ነው፣ አይጨብጠኝም፣ አይስመኝም፡፡ ጭምቅ ብቻ! ከመሳምና ከመጨበጥ በላይ ልምድ የሚሆንና ቅር ቅር የሚያሰኝ ሰላምታ ነው፡፡

ተቀመጥን፡፡ መፅሐፉ ውስጥ ስንጥር ከትቶ የደረሰበትን ቦታ ምልክት አደረገ፡፡ ካፌ ውስጥ ጥግ ካልሆነ መሀከል ላይ ስቀመጥ የዋለልኩ ይመስል መረጋጋት አይሰማኝም፡፡

"ለምን ወደ ጥግ አንሆንም?" አልኩት፡፡

ቀድሞኝ ተነስቶ በአይኑ ጥግ ቦታ ፈለገ፡፡ መፅሐፉን ይዤለት ወደመረጠው ቦታ ተከተልኩት፡፡ መፅሐፉ "A Book about Artists" የሚል ርዕስ አለው፡፡ ሽፋኑ ላይ የሦስት ሰዎች ምስል ተስሏል፡፡ በቀይ፣ በአረንጓዴና በሰማያዊ፡፡ ሰዎቹ እሳት፣ ሣር እና ኮፒ ይመስላሉ፡፡

ቀና ስል ብሩክ ባልተለመደ አኳኋን ያየኛል፡፡ ከስቷል፤ ክሳቱ ከጉስቁልና የመጣ እንደሆነ ያስታውቃል፡፡ የአንገት ልብሱን እንደ አጣጥፎ አንዱ ጫፍ ወደ ደረቱ ሌላው ወደ ጀርባው ወርደዋል፡፡ አስተያየቱ ያስፈራል፡፡ የእይታ መስበሪያ ወሬ ፈለኩ፡፡

"ለምንድነው? ጥግ ካልሆነ ነፃነት ተሰምቶኝ አልቀመጥም" ብሩክ ለኔ ጥያቄ ምላሽ አያጣም፡፡ የሚያስቅ ወይም የሚያሳዝን፡፡

"እኔም የሚገርመኝ ነገር ነው፡፡ አንተ ብቻ ሳትሆን ሁሉም ሰው ጥግ መቀመጫ ካጣ ነው መሀከል ላይ የሚቀመጠው"



t.me/OLDBOOKSPDF

ዛሬስ መልስ አጣ...

"ሲመስለኝ ከአውሬዎች የተቀዳ ባህርይ እያስገደደን ነው"

"እንዴት?"

"አውሬ መከላከያው ጥርሱ ነው። ፊት ለፊት ከሚገጥመው ይልቅ ከኋላ የመጣ መለስ እስኪል ያጠቃዋል። ስለዚህ ጀርባውን ለጥቃት አያጋልጥም።"

"እና?"

"እናማ እኛም..."

ከት ብዬ ሳቅሁና "ዘመዶቻችን አውሬዎቹ ብቻ ናቸው? ከብቶቹስ?"

"እነሱም ጀርባቸውን ጠባቂዎች ናቸው። ፊት ለፊት የመጣውን ዘተንድ" እንደ አመለኛ በሬ ግንባሩን አስቀድሞ እንደ መውጋት ጭንቅላቱን ቃጣብኝ።

ዘና ማለት ተሰማኝ። ሳቂ ወደ ውጭ የሚፈስ ሳይሆን ወደ ውስጤ የሚንቆረቆር ልስልስ ቀዝቀዝ ያለ የገመምተኛ መጠጥ መሰለኝ።

"ኪጋማ ከብቶች ጋር ብንዛመድ ኖሮ ወደኋላ መራገጣችንን ተማምነን ፊታችንን ለግድግዳ እንሰጥ ነበር። ሌባን ከኋላ ሲመጣ በኮቴአችን ጥርሱን" እግሩን ወደኋላ ሰነዘረ።

እንባዬ ጠብ እስኪል ሳቅሁ። ውስጤ የሚፍቀለቀለቅ ስሜት ተፈጥሯል። ቅጥ የሌለው፣ ግን ደስ የሚል ስሜት።

"እንዴት ናፍቀኸኝ ነበር?" አፌን ማዘዝ ተሳነኝ። ከተናገርኩ በኋላ የገዛ አፌን ፈራሁት። ምን ያወራ፣ ምን ይዘላብድ ይሆን? የተኮሳቆለ ፊቱ ላይ ሀዘኔታና ፍቅር ተቀላቅለው ሲጫወቱ አየሁ። አለ ኮናጋጁ መጥቶ ፊታችን ሲቆም ሁኔታውን በማደፍረሱ ደስ አለኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለእኔ ነጭ ማኪያቶ" አዘዝኩ

"ለእኔ ጥቁር" አለ!!!

ፀጥታ ሰፈነ። ድብብቆሹ ተጀመረ ማለት ነው። ድብብቆሹ የድብብቆሹን ቀጠሯችንን አስታውሶት ስለድብብቆሹ ባያወራ ተመኘሁ። ፈራሁ። አሁን ያለው ግንኙነታችን ባለበት እንዳይቀጥል የሚያደርግ ይሆን ይሆናል። ማን ያውቃል? አፈቅርሻለሁ ቢልስ? አፈቅርሻለሁ ካለ በኋላ እኔ ላይ ይሄ ነፃነት ይኖረዋል? እኔስ? "እኔም" ብዬ ከመለስኩለት በኋላ...

ማኪያቶአችን ተሰርቶ መጣ። የአውቶቡስ ትኬት ቆራጭ የመሰለው አስተናጋጅ እንዘጭ! እንዘጭ! አድርጎ ብርጭቆዎቹን አስቀምጦ ሄደ። ብሩኬ ስኳሩን ለእኔ መጨለፍ ጀመረ። አጨላለፉ ስኳሩን የማኪያቶው አረፋ ላይ በስሱ የማንጠፍ ጨዋታ አለበት። የስኳሮቹ ቅንጣቶች ለትንሽ ጊዜ በነጭነታቸው ይቆዩና እየራሱ ይጠቁራሉ። አጠቋቆራቸው ከብርሃንነት ወደ ጭለማነት በአፍታ የመቀየር መፈጎዳት አለበት። ተራ በተራ ከዘላለማዊነት ወደ ምንምነት ይሸጋገሩና በአንድ ላይ ወደ ውስጥ ይሰርጋሉ። ማኪያቶው የተበረቀሰ አረፋውን ቦቀስታ ሲገጥመው ውጦ የሚያጣጥም ይመስላል።

"እዚህ አዲስ አበባ መኖር ጀምሬአለሁ" አለኝ። ወደ ድብብቆሹ ወሬ እየገባን ሳይሆን አይቀርም። ማማሰሌን አቁሜ ዞሮ ያቄ እየሁት። እራሱን በአዎንታ ነቅንቆ ቀጠለ።

"በመምህርነት መቀጠሌ ለራሴ ሥራ እንቅፋት ሆነብኝ። መልቀቂያ አስገባሁ፣ ሰጡኝ - መጣሁ።"

እምላኬ፣ ሥራ እጥ ሆኖ ይሆን የተጎሳቆለው? ሆዴ ውስጥ እንዳች ነገር ተገለባበጠብኝ። ሲራብ? ሲጠማ? ሲታረዝ?...



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለስቱዲዮ የሚሆን ክፍል ያለው ቤት ተከራይቻለሁ። ከፈለግሽ ከእኔ ጋር ትኖሪያለሽ"

ወደ ድብብቆሹ መጥቻ የገባ መሰለኝ። አብረን የምንኖረው እንደ ድሯችን በጓደኝነት? ወይስ... ልቤ ተጨነቀች።

"ቤቱ ቅርብ ስለሆነ ከዚህ ስንወጣ አሳይሻለሁ።"

ልቤና ነገሩ እንደተንጠለጠሉ ቀሩ። ቀለልኩ። አብሬው ብኀሳቀል፣ ብከሳ፣ ባልበላ፣ ባልጠጣ፣ ብቃረዝ... እንዴዳ ይሆን? እንዴት? እጭኛዋ ጥሬ እንደ ዓሣ የሰባት ገበያ ሰው አትመስልም? ጥርኝዋ ወይን ሰርገኛ አታሳክርም? ፍቅር ባለበት በረከት ይታጣል? ፀጋ ይጎድላል? ጭንጫው አያብብም? ቋጥኙ ውሃ አያፈልቅም? እሾሁ አይከስምም? ጉድባው አይደለደልም?...

11

ይመራኛል - እከተለዋለሁ...

...እንደ ዝንጀሮ ገደል ላይ ቢኖር... እንደ ጭልፊል ቤቱ ጉድጓድ ቢሆን... እንደ ጨልሊ ቅርንጫፍ እንቅ ቢያድር... ደንታ አልነበረኝም። ከዘኬባ እንደወጣን ቁልቁል ወረድን። ጣይቱ ሆቴል ግራችንን ቀርቷል። ጥቂት እንዳቆለቆልን ከአራ በኩንቱ የሚመጣውን አውራ መንገድ አገኘነው። እንደተሻገርን ጭር ያለች ቀጭን እስፓልት ተቀበለችን። ብዙም ሳንጓዝ ወደ ቀኝ ታጥፈን የግቢዎች ሸለቆ ውስጥ ገባን። በኮረኮንች ጅረቱ ላይ እየተደናቃቀፍን ተጓዝን።

ብሩኬ ቆም ብሎ "ያ ሲጣን ቤት ነው" አለኝ።

ከጅርባው መጥተንበታል ማለት ነው።. ሲጣን ቤት እንደጋማ ከብት ወደ ኋላ አይረግጠን ይሆን? ብሩኬ በስተግራ ያለው የቆርቆሮ ግቢ ውስጥ እጁን አሾልኮ በሩን ከፈተው። ፈገግ እንዳልኩ ገባሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የቤቱ እርጅናና ይዞታ ከአያቶቼ ቤት ጋር የሥጋ ዝምድና ያለው ያስመስለዋል። በረንዳው ላይ ሁለት ህፃናት ይጫወታሉ። እኛን ሲያዩ "ብሩኬ! ብሩኬ!" እያሉ መጡ። ሁለቱም በእጆቻቸው የአስኪሪፕቶ ቀፎ ይዘዋል። በሌላኛው እጆቻቸው ደግሞ የብርቱካን ልጣጭ። ወደኛ እንደ መምጣት ቃጥተው "ማሚ፣ ብሩኬ መጣ" እያሉ ወደጓሮ ሄዱ።

ብሩኬ እኔን አየኝ። ስለሳ እንደሆነ ገብቶኛል። የልጅነት ትዝታዬን የሚዳብሱ፣ በሄድኩበት አቅጣጫ የሚጓዙ እኩዮቼ መሰሉኝ። ትልቋ አምስት አመት ቢሆናት ነው። ትንሹ ከሁለት እስከ ሶስት አመት ይገመታል። የቤቱ አከራዮች ልጆች መሆን አለባቸው።

ብሩኬ እየመራኝ ከትልቁ ቤት ጋር የተያያዘ አንድ ክፍል ውስጥ አስገባኝ። ክፍሉ ልጅ ሆኜ የማውቀውን የብሩኬን ክፍል አስታወሰኝ። እዚያ ከተሰቀለው ጃኬት ኪስ ውስጥ አውጥቶ ይሆን ብርቱካን ለልጆቿ የሰጣት? ምን መሆኔ ነው ግን?

ብሩኬ እጁን ኪሱ ከትቶ መሀከል ላይ ቆሟል። ጅምር ስዕሎች፣ ንድፎች፣ የቀለም ቆርቆሮዎች፣ የቀለም ማዋሃጃ ጣውላዎች፣ አዳዲስ አቡጀዲዎች... እኔ ካደናቀፍኩት የበሩ ብርሃን ሌላ የመስኮቱ ወጋገን አራት ማዕዘን ሰርቶ የቤቱ ወለል ላይ ተነጥፏል። ተጋረደ። የመስኮቱ ብርሃን ተጋረደ። ትከሻዬን የተጫጫነኝ ጥላ፣ ብሩኬን ተመለከትኩት። መስኮቱንና እኔን እያፈራረቀ ያያል። አንገቴ ተገትሮብኝ ከኋትከሻዬ ዞርኩ። አንዲት ሴት በመስኮቱ ክፈፍ ተከባ ከወገቧ በላይ ታየችኝ። ስዕል ትመስላለች።, የምታለቅስ ስዕል። ይሄን ስዕል ከዚህ በፊት ያየሁት ይመስለኛል። የዚችን ሴት ስዕል... ጉልበቴን ብርክ መታው፣ ማመን ተሳነኝ። ወደ ብሩኬ ዞሬ አየሁት። ያየሁትን ማመን እንዳቃተኝ ገብቶታል። እራሱን በአዎንታ ነቀነቀልኝ። እንባዋን ፍለጋ የጠፋችው እናቴ እግኝታው እያነባች ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለጥቂት ደቂቃ የማደርገው ጠፋኝ።

ሕፃናቶቹ በበር ገብተው ሁኔታችን ለጨዋታ ስላልጋበዛቸው ፈዘው ቆመዋል። የብሩኬ ድምፅ ወደኔ መጣ።

"እህትና ወንድሞችሽ ናቸው።"

ወደ እናቴ ዞሬ አየኋት። ስር ለስር ይስለከለክ የነበረ እንባዋ መንጭቶ በአፍላ ግፊት እየተንዶለዶለ ነበር። አንዳች ነገር ውስጤ ከተሸሸገበት እየፈካና እየጐላ ሲመጣ ይታወቀኝ ነበር። ምን? ምን?... አውቄዋለሁ፣ ገብቶኛል... ግን ምን? ወደ ብሩኬ ዞርኩ። ገብቶታል፣ ብሩኬ ውስጤ ያለ ነውና የውስጤ ሀሳይ መግባትና መውጣቷ፣ ይብረድና ይሙቅ ያውቃል።

በጭንቅላቱ ንቅናቄ "አዎ" አለኝ።

ተዝታዬን ተዘረፍኩ፣ ጀንበሬን ተዘረፍኩ፣ ልጅነቴን ተዘረፍኩ፣ ፍፍፍቅሬን ተዘረፍኩ። አንዲት ከጥይት በምትቆጠር የጭንቅላት ንቅናቂ ለዘመናት የለፋሁበት ወረቴን ተዘረፍኩ።

"ከቤት ከወጣች ከአመት በኋላ ፈልጌ፣ ፈልጌ አገኘኋት..."

ባዶ ሆኛለሁ። የብሩኬ ድምፅ ከውስጤ ገመገም ጋር እየተጋጨ ያስተጋባል። ገደል ለገደል ይሽሎከሎካል። ማልቀስ ተሳነኝ፤ ማልቀስ ተጎዳሁ የማለት ቅብጠት ነው። ከእንግዲህ እንዳላለቅስ አውቀዋለሁ። መሣቅም ተደሰትኩ የማለት ቅብጠት ነው። ከእንግዲህ እንዳልስቅ አውቀዋለሁ። አያቴ ሲሞት የእርሱን ኩርቢት እወርሳለሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ጨርቆሴን ጥበቃ

መቼም መዘዜ ብዙ ነው። ብዬ ብዬ ከጨርቆሴ ጋር ተጣልቼ አረፍኩት። አሁን ጨርቆሴ ጠፍቷችሁ ነው? ምነው ያ እንደ ጥንዚዛ ካገኘው ጋር የሚጋጨው ጨርቆሴ... እ-ሱ!

የጠባችን መንስኤ እንዲህ ነው።

ጨርቆሴ የመንደሩ መዛለቂያ ሽለቆ ውስጥ ቆሞ ይሸናል። ቁልቁል እያየሁት አልፌው እኔም ተሰየምኩ። ብዙም አልቆየ ምናምኑን እያራገፈ መጣና "እንዴት መሣቢያችን ላይ ትሸናለህ?" ሲል ደነፋብኝ። እሱ አትክልት ያጠጣ ይመስል።

"ይቅርታ" አልኩት በትህትና።

"ከሸናህ በኋላ የይቅርታው ጋጋታ ምንድነው?" አለኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

መቼም ጨርቆሴ ያሰልኩ ልብ ታጥቋል። የአካሉን መክሰመን ያዩ ወላጆቹ አድጉም ከሕፃኑ ጨርቆስ አይበልጥም ብለው ጨርቆሴ ያሉት ይመስለኛል። ልቡም የህፃኑ ጨርቆስ ነው አይኑ እያየ እሳት የሚገባ...

ዝም አልኩት።

ዝም አላለም። "ተናገር"ንጂ" አለኝ፣ ሲገርፈው እንደሚችለው ህፃን በንቀት እያየኝ። "መግቢያችን ላይ መሸናት በይትርታ የሚታለፍ ነው?" የመንደሩን ወንድ ሁሉ ይንቃል። የሚገርመው ደግሞ ሁሉም በዙር ደብድበውታል። ዛሬ የኔ ተራ ይመስለኛል። መቼም ጨርቆሴ ነገር ፈልጐ የገዛ አካሉን ማስደብደብ ልምድ ሆኖበታል። የጠላቱን ገላ በተውሶ ለብሶ የመጣ ይመስል።

አንድ ደህና ቡጢ እንኳ ሳላሳርፍበት ገላጋይ መሀከላችን ገባ። ጨርቆሴ ባስ፣ ካልገደልኩት አለ። እኔም ደነፋሁ

"እገድልሃለሁ!" አልኩ። የመንደሩ ነዋሪ ንቅል ብሎ የሁለታችንንም ፋከራ አደመጠ።

በመጨረሻም ሴቶቹ "እዩ የጨርቆሴ መጨረሻ ደረሰ። እሱስ አይለቀውም፣ ይገድለዋል" ሲሉ ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ አለ።

ጨርቆሴ ያጋመሰውን መጠጥ ለመጨረስ ሄደ።

እኔ ወደ ቤቴ ገባሁ። ግን አብሮኝ የገባው ነገር እየወዘወዘ አላስተኛኝ አለ። ለምን ሴቶቹ እንደዚያ አሉ? አሁን ጨርቆሴ አያርፍምና አንዱ ቢገድለው በእኔ ሊሳቡብ? በአደባባይ ስፎክር የሰሙ ሁሉ በእኔ ላይ ይመሰክራሉ። ታዲያስ? ዳኛ መልአክ አይደል? ግራ ቀኙን አዳምጦ ይሙት በቃ ይፈርድብኛል። ደነገጥኩ። ቆምኩ...

...አትጠራጠሩ ጨርቆሴ በሰው እጅ ይሞታል፣ በእኔም ይሳበባል፣ ይሙት በቃም ይፈረድብኛል። ከዚህ ሁሉ ባጣ ጨርቆሴን



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳይገሉብኝ መጠበቅ ያዋጣል። ጋቢዬን ለበስኩ፣ ካፖርቴን ደረብኩ፣ ዱላዬን ያዝኩ፣ ጨርቆሴን እንዳይገድሉብኝ ጥበቃ ወጣሁ። ይኸው እሱን እየተከተልኩ ቤቱ ሳስገባው ድፍን አንድ ወር ሞልቶኛል። እቀጥላለሁ...



t.me/OLDBOOKSPDF

# የይሁዳ ቀስተደመና

አጣሁት፣ አጣሁት፣ እንጂ እንደ ችግሬስ ፈጣሪዬን ለሰላሳ ብር• እሸጠው ነበር። ይሄን አድርጌው ቢሆን ይሄን ጊዜ እንደ ከንቱው ገበሬ "እንዲህ ልጠግብ በሬዬን አረድኩት" እል ነበር። ምክንያቱም ትናንት ሎተሪ እንደደረሰኝ አረጋግጫለሁና ነው።

ግን ይሁዳ እግዚሃርን ለሰላሳ ብር ሲሸጥ የነበረበት ችግር ለምን አልተገለፀም? እንደኔ አርቦት የነበረ ቢሆንስ? ወይንም እንደኔ ሚስቱ ወልዳበት ቢሆንስ? እንደኔ እናቱ ታመውበት ቢሆንስ? እንደኔ ከሥራ ተባሮ ቢሆንስ? ኡሺ, ያኔ ሥራ የለም ነበር እንበል፤ የሚያርስበት በሬ ገደል ገብቶበት እንደሆንስ?... ይህን ሁሉ አራቱም ወንጌሎች አሟልተው አልገለጡም። እንዳውም ይሁዳን ያስመሰሉት ለመክዳት ሲል ብቻ መድኃኒዓለምን እንደሸጠው ነው። ከሐዲነት እኮ ያለ ገንዘብ አሳልፎ በመስጠትም ብቻ ይረካል። ታዲያ ሠላሳ ብሩ...



t.me/OLDBOOKSPDF

ኢዲያ! የኔ ነገር። የፈለኩትን ትቼ ሌላ ስዘበዝብ እገኛለሁ። ትናንት ሎተሪ ደረሰኝ።

እስከ ዛሬ ከቤቴ አልወጣሁም።

ኧረ እንዳውም ካልጋዬ አልወረድኩም።

እንደ ሚስቴ የደስታ እራስ ሆኛለሁ። እንደ ሚስቴ ጨቅላውን ደስታ ታቅፌ ያጋት የምኞቴን ጡት አጠባለሁ። እንደ ሚስቴ ሁሉ ከዘመድ አዝማድ ለአራስ ጥሪ የመጣውን እየተማመስኩ መጋደም፣ ጉጂችን የሁለት አራስ ቤት ሆኗል። ሚስቴ የታቀፈችው ጨቅላ የጋራችን ነው። የኔ ደስታ ግን የግሌ፣ አልነገርኳትማ!

ምነው አለመንገሬ? እኔን የመታኝ የደስታ ፍላፃ እርሷ ላይ ቢያርፍ አትተረተርም። እርግጠኛ ነኝ እሁለት ትከፈላለች። ሎተሪ ሻጩን ጠርቼ በሹራ እጁ ሳሻሽት የምትመስጠኘን የሳምንት ወዳጄን ያቺን ሎተሪ ከማውጫው ጋር አመሳከርኩ። መጀመሪያ እግዚሃር ሲያላግጥብኝ መሰለኝ። መቼም ሙተክዣው አድርጉኛል...

ግን እውነት ነበር። ይሄን ላረጋግጥ አንድ ስል ስሜት ከደመና በላይ ተወርውሮ የአናቴን እኩሌታ ከፍሎ ወደ ልቤ በማድላት እየተረተረኝ ወረደና ሙሐሊቴን አቋርጦ አለፈ። አልፎም እንደ መብረቅ ከንድ መሬት ሰንጥቆ ገባ። ግራ እካሌና ቀኝ እካሌ ተፋትተው ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ በየፊናቸው የወደቁ መሰለኝ።

ሎተሪውን ዳግም ያመሣከርኩት ማውጫውን ከሎተሪ ሻጩ ላይ በሃያ ሳንቲም ገዝቼ አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ነበር። ጉደኛው ደስታ በተረጋጋ ስሌት በለመደው እካኄን ዳግም እካሌን ጉበኘው።

እነሆ እስካሁን አልተነሣሁም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ደስታ ስሉት ብቻ አይደለም። እንደ ማር ያለ ጣፋጭ ነው። ከመጠኑ ሲያልፍ ለሃጭ ያዝረበርባል።

ተዝረበረብኩ።

እንደ አራሷ ሚስቴ ወገብ ያልጠናው በራችን እየተልመጠመጠ ተከፍቶ እማማ አስላኩን አስተናገደ። ከገቡም በኂላ በራችን ልምጥምጡን ለሰላሳ ሴኮንድ ያህል መቀጠሉ አበሳጨኝ። እርግጥ ያበሳጨኝ በሩ ብቻ አልነበረም። የእማማ አስላኩ በትር እና ጉድጓዳ ለሃን ግራና ቀኝ እጆቻቸው ላይ ውለው፣ እኔ እቀድም እኔ እቀድም እየተሯከከሩ ሲመጡ አበሳጩኝ። ለወትሮው በትሩንም ባይሆን ጎድጓዳ ለሃኑን እናፍቅ ነበር። ዛሬ ግን በውስታ ሥም እንጀራ ተሸክሞ የሚመጣው የእማማ አስላኩ ጉድጓዳ ሰሐን ከሎተሪው ብር ካልተሞላ እንደማይወጣ ሆኖ ተሰማኝ።

"ጉድጓዳ ሰሐን ምግብ፣ በጉድጓዳ ሰሐን ብር!" መሮሁ ከጀለኝ።

"እንክ. እስቲ ደቺን ቅመሺ የማሪያም አራስ" አሉ እማማ አስላኩ።

ገብተኛል። እኚህ ቀበኛ አሮጊት ውለታቸውን ለማሪያም ያስተላለፉት ቤተሰቡ ምንም እንደሌለው ስላወቁ ነው። ሎተሪ እንደደረሰኝ ሲሰሙ ግን ባለውለታ ጉድጓዳ ሰሐናቸውን በብር የመሙላት ዕዳ ይጭኑብኛል።

ዘለግ አድርጌ ተነፈስኩ።

ብዙዎቹ ጐረቤቶቼ የአራስ ጥሪ ያመጡበትን ዕቃ ይዘው ከእማማ አስላኩ ኂላ ይሰለፉሉ። ፔርሙስ፣ ብረት ድስት፣ ስፌድ፣ እንትብ፣ ደንበጃን... ውሃ የቀዱልን ሁሉ ባሊያቸውን ይዘው ሰልፉን ከአድማስ ያሻግሩታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንግዲህ ምን ተረፈኝ? ስም፣ ስም ብቻ!! የውስታ ቀስተ ደመና የህይወቴን ሰማይ ከቦታል።

"እዳዬን እንድከፍል ነሯል ሎተሪ ያወጣህልኝ?" ስል እግዚሃርን ተደናቅልኩት።

እንደውም በደንብ ሳስላው ስራ የፈታው ህይወቴ በጉረቤቶቼ ዳቦ የቆየበት ሦስት ዓመት በደረሰን ሎተሪ አይሸፈንም። ገንዘቡን ማከፋፈል ሳያንስ ያልተወራረደ ውለታ ያላቸው ጉረቤቶቼ የውለታ ዕቃቸውን እንደያዙ የወቀሳ ክረት እየለቀሙ ቤቴን፣ እኔ፣ ቤተሰቤን፣ ነፍሴን... ይደበድባሉ።

ምን ፈረደብኝ?

ሆዴ ከጉረቤቶቼ ጋር አድሞ እሱም የውለታ ዕቃውን ይዞ አጉረመረመ።

ምን አልኩህ፣ ፈጣሪዬ? ስለምን በስምህ የተዳፈነውን የውለታ ሰደድ በሎተሪ ስም ቀሰቀስከው? ስለምንስ በዕድቅ ስም ያሸለበውን የሶስት አመት ውለታ እንደ አላአዛር ከጥልቅ ሞት አስነሳኸው?

ዕዳዬ ውለታ ብቻ እንዳልሆነ አውቀዋለሁ።

"መድፉ ሎተሪ ደረሰው" ሲባል የሰማ የስራ-ፈት ጅጊ ተውረግራጊ ቤቴን ይከባታል። ከቦም ያስጨንቃታል። ያኔ ደግሞ በራሴ ላይ ነው።

ምን ፈረደብኝ?

የሚወተውተኝን ሆዴን ለማስታገስ ወደ መጸዳጃ ቤት ሄድኩ። ለእኔ ከማበሻነት በላይ ጥቅም የሌላት ዕድሌን በቀኝ እጄ እንደጨመደድሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ከወደ ጠጅ ቤት

**(ፍፁም ያልሆነ እውነት)**

አራት ኪሎን፣ በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ እንዲሁም በመሀል 20 ጠጅ ቤቶች ያዋስኗታል። በሰሜን ከመጣን "ይገባዋል ጠጅ ቤት" ዘብ መስሎ ደጃፏን ይዟል። በደቡብ ለመጣ "ጂጂጋ ጠጅ ቤት" አለ፣ በምሥራቅ ወደ አራት ኪሎ ለሚሰርግ የ"ሻምበል ባሻ ጠጅ ቤት" እጅ አስታጣቢ መስሎ ይገኛል። በምዕራብ ከተፍ ለሚል "እማሆይ ጠጅ ቤት" ይጠብቀዋል። እንደ አሸን ከመካከል ለሚፈላ ደግሞ "ለጥ ይበሉ"፣ "ቆንጥጥ"፣ "እግረ ሙቅ"፣ "ሹልክ ብሎ ቅምስ"... ጠጅ ቤቶች አሉ። "እያምሰራ" ጠጅ ቤትም እዚያው ነው።

እንደ ፀሐይ በምሥራቅ ወጥተን አራት ኪሎን እንይ። ሻምበል ባሻ ጠጅ ቤትን አገኘን አይደል? ጠጅ ቤት እንደ ሀገን በይሆናል ሥም



t.me/OLDBOOKSPDF

አይሰጠውም። ግብሩ ቃዶቶ ነው። "መልካም ስም ከመልካም ሽቱ ይልቃል" የሚለው የጠቢቡ ቃል እዚህ አይሰራም። ምክንያቱም እራት ኪሎ ካሉት ጠጅ ቤቶች ውስጥ ብዙዎቹ አስደንጋጭ ስም ቢኖራቸውም ገበያቸው ግን አልቀነሰም። "ውሻ መግደያ"፣ "ሕግረ ሙቅ"፣ "ቆንጥጥ"... ሁሉም እንደሞሉ ናቸው። ጠጅ ቢጫ ወኔ ነው መሰል "እስቲ አባቱ" ባይ ጠጅ ጠጪ ይበዛል።

እናላችሁ፣ ሻምበል ባሻ ስሙን ያገኘው በሁለት መንገድ እንደሆነ የተምታታ መረጃ አለ። አንዱ ባለቤቱ ሻምበል ባሻ ስለሆኑ ነው የሚል ነው። ሌላው ከወደ አቧሬ የሚመጣ የጠጅ ቤቱን ደንበኛ የተመለከተ ነው። ይኼ ደንበኛ ሻምበል ባሻ ነበር አሉ። ሹክክ ብሎ ይገባና ሲወጣ እንደ ጆፌ ክንፍ እጁን እንከርፍፎ ነው። ኩራቱ፣ ንቀቱ፣ ትዕቢቱ፣ ሶብሪቱ... ይኼ ሁሉ የጠጅ ቤቱ ተግባር ተደርጎ ስለተወሰደ እንደ ሻምበል ባሻ ለመሆን ያሰበ ሁሉ ወደዚያ ይጎትዳል። እናም "ሻምበል ባሻ" በዚሁ ሥሙ ሆኖ ረጋለት።

ሻምበል ባሻ ጠጅ ቤት ሙዝ ተራ፣ ከሥላሴ መሳለሚያ ከፍ ብሎ ይገኛል። የጠጅ ቤቱ መሿለኪያ፣ እንደ ግራና ቀኝ መደርደሪያ ላይ መጽሐፍ በራቸው የተገጠገጠ የሴተኛ አዳሪ ቤቶች አሉ። (በነገራችን ላይ ጠጅ ቤቶችና የሴተኛ አዳሪዎች ተሳሳቢ ናቸው) ከጠጅ ቤት የሚወጣ እንጂ ወደ ጠጅ ቤት የሚገባ የሴቶቹ ድምፅ አያጅበውም። "በሰላም ግቡ" ይመስላል።

ሻምበል ባሻ ጠጅ ቤት የመሿለኪያው ጫፍ ላይ አለ። እበት የተለሰነ የንብ ቀፎ ይመስላል። በሩ ሽንቁር ነው። እዚያ ውስጥ "ኢምምምምምም" የሚል ጠጅ ጠጪ ታጭቋል። ከበር ለሚገባ እንግዳ ተቀባዩ ትንፋት ነው። ጫማው፣ ድሪቶው፣ አምቡላው... ተደበላልቆ ስለሚብላላ አለምን ለማደበላለቅ የሚያስችል ኃይል ፈጥሯል። ትንፋት በባለጋራነት የሚማታው ለትንሽ ደቂቃ ብቻ ነው። እርስዎም



t.me/OLDBOOKSPDF

የትንፋት ተባባሪ አባል ሆነው አዲስ ገቢን ማጥቃት የማጀምሩት ወዲያው ነው።

የቤቱ ውስጣዊ አደረጃጀት መሿለኪያ ሸለቆ ያስመስለዋል። በቀጭኑ ወደ ውስጥ እየጠበበ ሄዶ ጫፉ የማይታይ የሳንቃ ዋሻ።

የጠጅ ቤቱ ምሰሶ መሰሉ መሀከል የሚቆመው ታረቀኝ ጅቡ ነው። ቁጭ ብሎ አይጠጣም። በጠጅ የገነተረ ፊቱን እያተረማመሰ ቃል ሳይወጣው ያወራል። ከንፈሮቹ እንደተገጠሙ ሲያንቀሳቅሳቸው አፉን የሚጉመጠመጥ ይመስላል። የጉሉትዝ መርፌ በተገጠመ ከንፈሩ መሀከል አስገብቶ ወደ ሰርክር ቢተጠልና የሚናገረው ቢሰማ… ያንጓል።

እናቴ ላከችኝም አላከችኝም አባቴን ፍለጋ እሄዳለሁ። በአይኔ ስማትር ከብዙ ግንትር ፊቶች መሀከል የአባቴ ፊት ተወሽቆ አየዋለሁ። ብዙ ጊዜ ቀድሞ የሚያየኝ እሱ ነው። ጥርሱን እንደገጠመ፡-

"አንተ አ-ሙ-ሴኛ!" ይለኛል።

"ተወው ተወው" ይላሉ ብዙ ግንትር ፊቶች። ስፈራ ስቸር አቀርባለሁ።

"እ-ማ-ዬ…" ስለው ንዴቱ ወደሷ ይዞርና፣ "እ-ቺ አ-ሙ-ሉ-ኛ" ይላል አባቴ። ልምዱ ነው።

"ተ-ው-ው" ይላሉ ግንትር ፊቶቹ። የሶጋ እምቦቲቶ ይታዘዝልኛል። ለጠጅ ማጣጫ እንዲሆን ሚጥሚጣው ይበዛል። እየተንገበገብኩ እበላለሁ። ላቤ በግንባሬ ላይ ችፍ ይላል። አባቴ ለስላሳ እንዳይገዛልኝ ከጠጁ ያቀምሰኛል፣ ያቀምሰኛል፣ ያቀምሰኛል… በኋላ ብርሌውን ለእኔ ትቶልኝ ለሱ ሌላ ያዛል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሻምበል ባሻ ጠጅ ቤት አንድ ደመኛ ጠጪ አለው። የቤቱ መንግሥት ሥራዬ ቤት ነበር አሉ። የንጉሱ ጠጅ ጣዪ ነበር እየተባለ ይወራል። የቀን ግብሩ አራት ብርሌ ጠጅ ነው። ግብሩ ከልጋባለት መሀከል ላይ ይቆምና፦

"ቅዳ" ይላል ጮክ ብሎ።

ይቀዳለታል። ብርሌውን ከፍ አድርጎ በቂጡ በኩል ይመለከተዋል። እሱን ጠጪው ይመለከተዋል። በጥርጣሬ ወደ አፉ አስጠግቶ ይቀምሰውና ፊቱን ያኮመዝዘዋል፦

"ጥ-ጥ-ጥ... የባሬ ጠጃችሁ ልክ አይደለም! ሒሳብ!" ከፍሎ ይወጣል። ቢያንስ የቤቱ ሩብ ጉዳይ ደንበኛ ተከትሎት ይወጣል። ስለዚህ ጠጅ ቀጂው አራት ብርሌ መጋበዝን ይመርጣል። የተጋበዘ እንደሆን መሀከል ላይ ይቆምና፦

"ቅዳ!" ይላል ጮክ ብሎ

ይቀዳለታል። ብርሌውን ከፍ አድርጎ በቂጡ በኩል እየተመለከተ ፈገግ ይላል። ከደስታ ጋር ይቀምሳል። ፊቱን አስደስቶ ድጋሚ ብርሌዋን ያያታል፣ ያንደቀድቃታል በእርካታ፦

"እንዲህ ነው'ንጂ ጠጅ!"

ህጥ ያለው ጠጪ ወደ እ-ም-ም-ም-ምታው ይገባል - ይረጋጋል።

አባቱን ሻምበል ባሻ ጠጅ ቤት ካጣሁት እወጣና ወደታች እወርዳለሁ። ከፓርላማ ፊት ለፊት ቁልቁል ወደ እሪ በከንቱ የሚወስደውን መንገድ ዝቅ እንዳልኩ ገባ ብሎ ሁለት ጠጅ ቤቶች አሉ። የአንዱ ስም ተረስቶኛል። ሁለተኛው ግን "እግረ ሙቅ" ነው። የ"እግረ ሙቅ" ጠጅ ቁጭ ብሎ ሲጠጣ ሰው ስካሩ አይታወቅም" አሉ። ለመሄድ የተነሳ እንደሆን ነው ጉዱ። እንደ ካቴና አሳስሮ ቁጭ! ብዙ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠጪዎች መንፈሳቸው ሳይሰክር እግራቸው አልታዘዝ ብሏቸው በሰው ተደግፈው ሲወጡ አይቻለሁ።

“እግረ ሙቅ” ስምን እንደ ክፉ በሽታ እጅ እግር እንደሚያሳስር ብዙ መላምቶች አሉ። ከሁሉም ገንኖ የሚሰማው ጠጁ ውስጥ ሲሚንቶ መደረጉ ነው። ቶሎ እንዲደርቅ። ይሄን ስሰማ የአባቴ ሆድ ውስጡን የጠለለ ሲሚንቶ እንዳዘለ ሆኖ ይታሰበኝ ጀመር። እንደ ሰባራ ጋን ልክክ ያለው ሲሚንቶ ውሃ ባልጠጣ ቀን ደርቆ ቅርፊት የሚሰራ እና አንድ ሰው ለቀልድ እንኳን ሆዱን ቢመታው እየተንኳኳ የሚወርድ። አባቴ ጠግቦ ሆዱን ባሻሸ ጊዜ “ተው ሲሚንቶህ እንዳይፈርስ” ለማለት ይዳዳኛል።

“እግረ ሙቅ” በብዙ ቆሻሻ የሴተኛ አዳሪ ቤት የተከበበ ንፁህ ግቢ አለው። ከጠጅ የተረፈውን ሲሚንቶ የግቢውን ወለል ለስነውበታል። የቤቱ ቁመና ባለ አንድ ደርብ ነው። ታችኛው ጠጅ ቤቱ ሲሆን ላይኛው የባለቤቶቹ መኖሪያ ነው። የውስጥ አደረጃጀቱ እራት ኪሎ ካሉ ጠጅ ቤቶች ሁሉ የላቀ ነው። ንፅህናው ጠጪዎቹን ያሳጣል። ለነፍስ ይማር ድግስ የተጠሩ የኔቢጤዎች መስለው ጠጃቸውን ያንደቀድቃሉ።

ያደግሁት እዚሁ ግቢ ስለሆነ ቤቱን በደንብ አውቀዋለሁ። የቤቱ ባለቤት የታወቁ ሴት አርበኛ ነበሩ። ከመኖሪያው አንስቶ ያሉ ቤቶች ሁሉ የሳቸው ናቸው። ቀይ ምጥጥ ያለ ፊት አላቸው። ቀጭን ረጅም በሳሎን ጊዜ እንደ ሰንጎት ከፍ ያለ ሰፋ ላይ ቁጭ ብለው ሰሚታቸው ሲቅበለበጥ የሚፎክሩ ይመስላሉ። የቤቱ ዙሪያ ግድግዳ በጉራዴ፣ በጋሻ፣ በጦር፣ በጠብመንጃ፣ በባንዲራ ያሸበረቀ ነው።

ዘወትር ያጎነቆለ ባቄላ ተቀቅሎ ከፊታቸው በገበርጌ ሰሐን ይቀመጣል። ስገባ አፈስ አድርገው ይሰጡኛል። የሳመው የባቄላ ሆድ ከገለፈቱ አፈትልኮ ጣት ላይ ፈስሶ ሲታይ ያብረቀርቃል። እያንዳንዱን



t.me/OLDBOOKSPDF

ባቂላ ወደ አፌ እከትና በተበጣው ቆዳው በኩል እጠባዋለሁ። ሻክር የሚል ወተቱ ከባቂላው ሆድ እየወጣ ምላሴ ላይ ሲያርፍ ይሰማኛል። ባቂላ ሲጠረጠር አርበኞዋ ስለማይወዱ አኝኬ እውጠዋለሁ።

ለእኔ ብቻ የሚሰቁ ይመስለኛል። ጥርሳቸው ሳይታይ ሞጣጣ ፊታቸውን አስደስተው "ዘንቦለል" ይሉኛል። "ና ወዲህ" እቀርባለሁ።

"አይ ሱሪው ጅል፤ በደንብ አትታጠቅም? ወንድ እንዲህ ነው?" በፋከራ መልክ ያዋሩኛል፣ እግራቸው ሥር አስቀምጠው ከባቂላው ይዘግኑልኛል። እሳቸው ሲበሉ አይቼ አላውቅም። ሰው ሲበላ እያዩ የሚደሰቱ ይመስለኛል።

በሰውነቱ የአርበኞቱ ጌታ የሚመስል አሽከር አላቸው። ሽፋፋ፣ ጥቁር፣ ጠረንገሎ ነው። ቤተ ክርስቲያን ያለ ይመስል ዘወትር ነጠላውን አደግድጎ ከወዲያ ወዲህ ይላል።

"አየለ" ሲሉ

"ኢመይቴ" ይላል። "እመት" አይልም። እሱ የሰራውን ወጥ ብቻ ነው የሚበሉት ይባላል። "እብሲቱን ጥሎ ሲጋግር ላየው..." እየተባለ ይወራል።

ከአርበኚቷ በስተቀር እዚያ ቤት ያለ ሁሉ ደዘደዝ ነው። የልጅ ልጃቸው እንካን የእኔ ታናሽ ሆና የእኔን ሁለት ታከላለች። ከግቢዋ ወጣ ብላ ያገኘች ልጅ ሁሉ ያጠቃታል። እኔ እንካን እያቷን ሳልፈራ እመታታለሁ። እያለቀሰች ወደ ቤት ስትገባ እያቷ ይገፏሏሉ።

"ታለቅሻለሽ? አትያቸውም? አፈር ብይና፤ ያውልሽ ጕራዶ በያቸው" ያላሉ።

ልጅቷ ጕራዶዋን መሬት ላይ እየጎተተች ትመጣብናለች።

"እኔ ነኝ ሀላፊው፣ በያቸው!"



t.me/OLDBOOKSPDF

እኛም እንኳን በብመንጃ አልለሟት እያልን እንሸሻለን። ለጅቷ እያለቀሰች ጉራይዎቿን ይዛ ለማባረር ትሞክራለች። ለውሻቷ የተቀባበረ ስላልሆነ ቆማ ታለቅሳለች።

ከዚያ በኋላ አዘናግቼ አሄዳለሁ። ልጅቷ ሰው ስለሚናናቃት በዐዲ አትፀናም። ሽንክ ብዙ ትልቁ ቤት ለመግባት ሳስግ…

"ዘንቦለል - ሱሪው ጆሌ! የት ጠፋህ? ግባ እስኪ! ምን ያሽኮረምምሃል?" ህይወት በሌለው እጃቸው የተንቀለ ባቄላ ንፍሮ ይሰጡኛል። እሳቸውም እንደ ልጅ ልጃቸው ሰው ሳያናናቃቸው አያቀርም። ከእኔና ከአንድ ቤት አርበኛ ውጭ ማንም ደፍሮ የትልቁን ቤት ደጃፍ አያረግጥም።

"የጊታዩ ልጅ" ትላለች እንግዳዋ አርበኛ። አውቃታለሁ። ስትሰክር በመንባረር ትፎክራለች። ደስታ ምታቴ ነው ስሟ። የአባቷ ስም ሁሉም ግራ እንዲጋባኝ ነው። ምታቴ ነው? ወይስ እምታቴ?… ብቻ ዘወትር የቤት ፈትል ትለብስና ወገቧ ላይ ዝናር የመሰለ ክዘርቸሊ የመጣ የጥልፍ ቀበቶ ታስራለች። ስትሄድ ጠቆም ጠቆም ነው።

"ነቃ ነቃ በይንጂ ይተቢያኮ የማይተኙላት ጠላት አላት" ትላለች አርበኛዋን።

"እርግጥ" እንደማሳት ጭንቅላታቸውን ይወዘውዙላታል።

"አበበ ይሙት፣ እኔ እንደሁ ክንዴን ሳልንተራስ…"

ለምን "አበበ ይሙት" እንደምትል አይገባኝም ነበር። በኋላ አባቴ ሲነግረኝ ለካ የምትምለው በራስ አበበ አረጋይ ኖሯል። በእሳቸው ሥር ሆና ነው አምስቱን አመት በአርበኝነት ያሳለፈችው። ከነፃነት በኋላ ራስ አበበ ስትፎክር አድምጠዋት፦



t.me/OLDBOOKSPDF

"ነይ እስኪ፣ ምን እንዲደረግልሽ ትፈልጊያለች?" አሏት አሉ።

"ጉታዬ የፈተድከውን" አለች ደስታ

"በይ ርስት እንዲሰጥሽ እናዝዛለን"

"የለም! ርስት እንዴ ጉልበተኛ ይቀማኛል። ይልቅ ጥበብ ልብስ ስጡኝ" አለች አሉ። ይሄንን የሰሙ ሁሉ በቂልነቷ ይስቃሉ። አርበኚቷ ብቻ፡-

"ድንቅ ብላለች" ይላሉ እያጉረመረሙ

"እንዴት?" እላለሁ አስራቸው ሆኜ ባቂላውን አፌ ውስጥ እየጠረጠርኩ

"እንዴት ነው እንዴት? እንኳን መሬት የብሽሽቷን ርስት በወጉ አልጠበቀች።"

"ምንድነው የብሽሽቷ ርስት?"

ከእንቅልፍ እንደባነኑ ሁሉ ወደ እውነታ ይመለሱና "እፈር አባክ ብላና ከኔ ጋር ወግ ጀመርክ? እንዴት ያለው ጉድ ነው። ናኮ ውጣ" እኪታልፈው ያባርሩኛል።

እንግዲህ "እግረ ሙቅ" ጠጅ ቤት የተመሰረተው እኒህ ሴት ከሞቱ በኋላ አስከብረውት የቆዩት ቤት ተደፍሮ ነው። ቢኖሩና ይሄንን ጉድ ቢያዩ...

"ከእግረ ሙቅ" ጠጅ ቤት ስወጣ ፊት ለፊት ባቡር መንገዱን አቋርጦ "ቆንጥጥ ጠጅ ቤት"ን ያያል። ትልቅ ቀይ በር ግቢ ውስጥ ጠጅ ቤቱ ተመሥርቷል።

አሁን አሁን ሳስበው በየጠጅ ቤቱ የሚያጋጥሙት ምን እንደሆን አላውቀውም። አባቱ አስር አመቱን ሳልደፍን ነው



t.me/OLDBOOKSPDF

የሞተው። ክፉ በጎሳም" እንዝህላል ሆኜ ቆሎ፣ ሲጋራ፣ ማስቲካ ከሚሸጡ ልጆች ጋር ገጥሜ ነበር። እናቱ ለንግድ በሥመጠጥ ቤቱ ሲሄዱ አብሬአቸው እንከራተት ነበር።

ቆንጥጥ ጠጅ ቤት ስገባ ጠጅ ተጂው እያከታተለ ያስጠጣኛል። ለዚያ ያደላ ብስል ቀይ፣ ደልዳላ ሰውነት ያለው፣ እግሮቹ የፈናጅር የሚፈግገው። በአባቱጭ ተቆርቋሪነት አናግሮ፣

"ባለጌ፣ ውጣ ከዚህ" ይለኛል። ለጠጅ ጠጪዎች ትሁትና የለውም። "አድርሺ" ሲሉት "አትድረስ" ይላል። ድንገት ከጠጅ ቤት ወጥቶ ወደ ላይ ወይም ወደታች ይሮጣል። ሲሮጥ የሸርጡ ኪስ ላይ የእጆቹን መዳፎች እንደ አፍላላ ከድኖ ሳንቲሞቹን እያንኳኳሸ ነው። ወዲያው ታዲያ አንድ ሰካራም እንደ በቅሎ "ልጓሙን" ይዞ ይመጣል። ሒሳብ ሳይከፍል አጭበርብሮ የሸሸ ነው። የተያዘበት ቦታ ላይ አይከራከርም። "ግፋ ካለም" የሚማታው እዚያ ጠጅ ቤት ውስጥ ነው። ለዚህ ድርጊቱ ሁለት ምክንያቶች አሉት። አንዱ ከሱ ጋር ቆሞ ሲከራከር ሌሎች እንዳይሸልኩ ሲሆን ዋነኛ ምክንያቱ ግን የተያዘውን ጠጪ ለመሸለክ ላሰቡት ጠጪዎች መቀጣጫ ማድረግ ነው።

"አፈር የጠጣህ" እያለ ያንሳቀሳል - ይማታል።

ይህን ስመለከት አንድ ቀን እኔንም "አፈር የገባህ" እያለ እንደሚያንሳቅለኝና እንደሚመታኝ አስቤና አፈራለሁ። ቆንጥጥ አልገባም። ሹክክ ብዬ ከአካባቢው እጠፋለሁ።

አልፎ አልፎ ወደ "ሹልክ ብለሽ ቅምስ" ጠጅ ቤት እሄዳለሁ። ጠጅ ቤቱ የአንድ ብር አልጋም ስላለው ከሌሎቹ ይልቅ ሴት ጠጪዎች ይበዙበታል። ከአርበኛዋ ደስታ ምታቱ በተፈሪማሬ ብርቱካን፣ አስቴር ቲሊሊ፣ ፀጊቱ ደንበጃን፣ አስካለ ማብረጃ፣ ሽዋንሽ ቁንጦ... የሚባሉ ጠጪዎች በመጠጥ የ[illegible]ታቸውን በቀዳዳ ነጠላ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመጋረድ እየሞከሩ ብቅ ጥልቅ ሲሉ ይታዩ ነበር። እርስ በእርስ ሲባሉ ከመግዳዳት ይልቅ መሳቂያ መሆናቸው ይጎላል።

ተጣይዎቹ ፊት ለፊት ዝርፍጥ ብለው በመዳበስ አይነት ይሰነዛዘራሉ። ፀጉር ለፀጉር ከተያያዙም እንትልፍ የወሰዳቸው ያህል ንፍዘት ይታይባቸዋል። አልፎ አልፎ እንደመጣነን ያለ ስድብ ጣል ይደራረጋሉ። እኛ ከጥሉ ይልቅ የተበተነ ሳንቲም እንዳለ በሚል ጉጉት ስር ስራቸው እንላለን።

ከ"ሹልክ ብሎ ቅምስ" በተጨማሪ አካባቢው ላይ ሶስት ጠጅ ቤቶች አሉ። "አሰለፊች"፣ "እያምሶሪ" እና "ጅጅጋ"። የእያምሶሪ ጠጅ ቤት ባለቤት ዘመናይነት የሚሰማቸው ባልቴት ናቸው። ዘወትር ባለጥልፍ የሀበሻ ቀሚስ ለብሰውና ፀጉራቸውን ተተኩሰው ፊት ለፊት ይቀመጣሉ። የሚጠጡት ቢራ ነው። ጠጪ የማይመስል ነገር ከተናገረ "እያምሶሪ" ይላሉ። ለዚህ ነው ጠጅ ቤቱ የሳቸውን ብሒል ስሙ አድርጎ የቀረው።

አራት ኪሎ ውስጥ ካሉ ጠጅ ቤቶች ሁሉ ስሙ በባለቤቱ የወጣለት "ጅጅጋ" ብቻ ነው ማለት ይቻላል። ወይም የፀደቀለት። የጠጅ ቤቱ ባለቤት በሶማሌ ወረራ ከጅጅጋ የተፈናቀሉ ነበሩ። ሥርዓት የሚያበዙ ቀይ ንቅሳታም። ጠጅ ቤቱ እንደነገሩ አልጋ ቢኖረውም ሴቶች እንደ ሹልክ ብሎ ቅምስ አይዳፈሩትም። ግድግዳው ላይ "አዛሪ ሴቶችን አናስተናግድም" የሚል የድፍረት ማስታወቂያ ተለጥፏል። አባቴ እነዚህን ጠጅ ቤቶች ስለማያዘወትራቸው አካባቢው ላይ የመቆየት ልምድ የለኝም።

ብዙ ጊዜ ከኤደርሳ ጎሮ ሆቴል ጀርባ ወዳሉት ጠጅ ቤቶች ሄጄ ጓደኞቼን እፈልጋለሁ።

"ለጥ ይበሉ" ጠጅ ቤት ግቢው የቆርቆሮ ዳስ ለብሶ ከትልቁ ቤት ጋር ተቀላቅሏል። የበረንዳ ትራቱ ላይ ባለቤቷ ወ/ሮ ዘነበች ቁጭ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብለው ከሳላፊዋ ጠጅ እያስቀዱ ይጠጣሉ። የንግዱ አካል ነው። እሳቸው ሲጠጡ ያየ በንዕህናው እየተደፋፈረ ይጨልጣል። ጠጅ ቤቱ "የግጥም" ይሞካሻል።

የዘነበች ፍርዷ

ለጥ ይበል ከሆዷ፤ እየተባለ። ጠጁ አይጣላም። ገፅም ብሎ ሙቀትና ሞቅታ ይለቅቃል። የአራት ኪሎ ጎረምሶች ግን በልስላሴው ይንቀታሉ። "ለጥ ይበሉ እንጋብዛችሁ" ከተባሉ "ዳቦ ይገፍ ልምጣ?" ይላሉ። ሻይ እንጂ ጠጅ አይደለም ለማለት።

ጓደኛዬ "አተር" አዚያ አይጠፋም። እናቱ ለጥ ይበሉ ሲለሚጠጡ ብዙ የቆሎ ደንበኞች አሉት። እናቱ ጉያ ውሽቅ ይልና ጭንቅላቱን ከተደባበሰ በኋላ የአተር ቆሎውን ማዞር ይጀምራል። "አተር" የተባልኩት አተር ቆሎ ስለማዞር ነው" ይበል እንጂ ጉዳዩ ወዲህ ነው። አንገት የለውም፤ ወገብ የለውም፤ ቂጥና ሆድ ለጉድ ነው። ከብለለለለል እያለ ጠጅ ቤቱ ውስጥ ገባ ወጣ ሲል ይውላል።

"አተር" ጠራሁት

እራሱን የለጥይበሉ አስረኛ አድርጎ ስለሚቆጥር እንደሆን እንጃ ጓደኞቹ ሲመጡ በተጠያቂነት ፍልቅልቅ ይላል። ደብረክ ደብረክ እያለ መጣ።

እናቴ አተርን ስታየው "የደሃ ጥጃ" ትለዋለች። ለምን እንዲህ እንደምትለው ስጠይቃት። "ደሃ ጥጃው አንድ ነው፤ ብርቅ ስለሚሆንበት ያገኘውን እያጉረሰ እንዲህ ያድበከብከዋል" ትላለች።

እናቴ ጥሩ አይታዋለች። እናቱ ወደ ጠጅ ቤት ሲመጡ ጥሩ ምግብ ሰርተው አስቀምጠውለት ነው። ባሰኘው ሰዓት ወደ ቤት ሄዶ ይበላል።

"ዘሲቴ፤ መጣሽ? ነሽ ጭነሻል አይደል?" ጫን ጫን ይተነፍሳል።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ኧረ ቼላ (ሃምሳ ሳንቲም) ብቻ ነው ያለኝ።" ቁማር እንጫወት ሲለኝ እንደፈለገ ገብቶኛል። ከአተርፎ ጋር ቁማር መጫወት ደስ ይለኛል። ከተበላ "እናቴ እንዳትሰማ" ይላል'ንጂ አተካሮ አይገጥምም። ቋበላም ልጆች ለእናቱ እንደሚናገሩ አስፈራርተው ይቀበሉታል። ታዲያ ለምን ይጫወታል? ሁሉም የሚገርመኝ ነው።

"መደቡ ዲናሬ (አስር ሣንቲም) እንጫወት እንዴ?" በጣም ስለተረበኝ የሰውነቱ ወላፈን ይሰማኛል።

"ኩሽ ነው?" (በብርቱካን ልጣጭ የሚከናወን ቁማር)

"እማዬ ታየኛለች። እዚያ ጥግ ቁጭ ብለን ጥፍጥፍ" እንዳለው አደረግን። በመካከል ማርዬ መጥታ ቁማሩን ተቀላቀለች። የአተርፎ ተቃራኒ ናት። ሙጥጥ ያለች ነገር። በወትር ከፊቷ ላይ የእንባ ሰንበር አይጠፋም። የምትሸጠውን ቆሎ ሒሳብ ከተበላች መንገድ ላይ ሊያለቀሰች ከአላፊ አግዳሚ ትቀበላለች። አሁን አሁን ያመጣችው ኣዲስ ዘዴ ደግሞ ሐምሳ ሳንቲም ተደብራ ቆሎ ከጓደኞቿ ትገዛና ጠጅ ቤት ፊት ለፊት መሸኛ ቦታ ላይ ትደፋዋለች። ከዚያ እያለቀሰች ትለቅማለች። ተመልካች ይዘገንነዋል።

"ምን ልታደርገው ነው?"

"አቤት ስለሚቆጡኝ ለቅሜ እሸጠዋለሁ" እያለች ትነፈርቃለች።

"በል፣ በል ተው" እየዘገኑናቸው የጠየቀችውን ይሰጡዋታል። እንደዚያም ሆኖ ፊቷን አትታጠብም። "ነገ ከተበላሁ መሸቀያዬ ነው" ትላለች። አንዳንድ ተንኮለኛ ልጆች እጃቸውን ውሃ አስነክተው ሳታያቸው ፊቷን ያበሰብታል። "ወይኔ እንባዬን አጠፉብኝ" እያለች ታለቅሳለች። የእንባ መስመሯ በዚያው ይተካላታል።

ከአተርፎም ሆነ ከማርዬ ጋር ቁማር መጫወት ደስ ያለኛል። አያለቃቅሱም። አፋራም አይደሉም። ከቻሉ ለምነው ጥቂት ለማግኘት



t.me/OLDBOOKSPDF

ይጣራሉ። በቃ። "ዝሆኑ"፣ "ጉርናና" ብንል ቆይተን እኔ ጠተለልኳቸው።

ብዙ ጠጅ ቤቶች ደጃፍ ላይ የተቀረጣጠፈ የጌሾ ቅልጥም አምቡላ ተከናንቦ መንገድ ላይ ይሰጣል። አጠገቡ ቢሜ የእንጀራ ፍርፋር የመሰለው የማር ሰፈፍ ይንጠፋል። ከጌሾው ይልቅ የሰፈፉ ሽታ ደስ ይለኛል።

አንድ ጊዜ እናቴ ብቅል ቶሎ ገዝ እንድገዛ ላከችኝ። እኔ አተር መንገድ ላይ ጥፍጥፎችን እየጠረፈው ደረስኩ። ስተወስነ ጊዜ ቆመው አየኋቸው።

"ዝሆኑ! ጉሬር! ግባ! ውጣ" ይላሉ።

ፈራ ተባ እያልኩ ጥጉርኩ የተላከሁባት ጉደለች። እሷን ለማሟላት ሊሳሆን ሰተትኩ። አጣደፉኝ፤ ይባስ ብዬ ጉል አልኩ (ፍራንክ እየፈለመርኩ ከመደቡ በላይ ተሟጠጥኩ)። የተላክሁበት በሙሉ ተበላ። ባለቅስ ብፈርጥ ሁሉም ጨለነ። በመጨረሻ አተር አንድ ሀሳብ አመጣ። ከሰጥ ይበሉ ጠጅ ቤት ፊት ለፊት ከሚደጣው ጌሾ ዘግነን በውኃ ካጠብን በኋላ ለእናቴ እንድሰጥ። ይሄንን ላላሰበው ስጨነቅ በመቆየቴ ተሀወትኩ። ጌሾውን አፍሰን ፌስታል ውስጥ ከሞላን በኋላ አተሮ ውሃ እያመጣ አጠብነው።

"ሰቋል! ሰቋል" ይላል አተር።

"በኦሞ ብናጥበው ጥሩ ነበር" አልኩ። ኦሞ ከየትም ማምጣት አልተቻለም። በኋላ በውሃ ብቻ የታጠበ ጌሾዬን ይዤ ወደ ቤት ለመግባት ተገደድኩ። መሽቶ ስለነበር የአምፖሉ መብራት የአምቡላውን ቀለም አደናግዞ ግንዛቤያችንን አጥፍቶብን ነበር።

ገና ወደ ቤት ስገባ ነበር እናቴ "የት ቆየህ? ደሞ ምን ምንድነው የምትሸተው? እስቲ እፍህ። ጠጅ ጠጣህ እንዴ? የምን ጉድ ነው



t.me/OLDBOOKSPDF

ታዲያ? እዚያ ጠጅ ቤት አትሂድ አላልኩም? ልብስህ ነው እምቡላ ውስጥ የተነከረው? እስቲ ጊሸው? እ? አንተ?...."

ከዚህ በኋላ ያለውን አለማስታወሱ ይሻላል። በጥርሷ ብቻ እንጠልጥላኝ ቆመች። ምንም ነገር አልጠትም አላት።

የማይጠገን ሰባራ፣ የማይጠግግ ቁስል፣ የማይመለስ ወለምታ፣ የማይታሽ ሶተር መዞር... ይገዩ እልጋ ላይ ከረምኩ። እናቴ ከንዴቷ ማየል የተነሣ ጭንቅላቴን ሳይቀር ነክላዋለች (ነው ግባዋለች?) እዚያ ተኝቼ ውል የሚለኝ የእነ አተርሮ ልፊያ፣ ቁማርና ብሽሽት ነው። እነሱም አንዳንዴ ብቅ ብለው "ካሲቲ፣ ካሰሽ!" እያሉ ያፏጫሉ። እናቴ እጇ የገባ ነገር ይዛ ታሳድዳቸዋለች።

እስካሁን ድረስ የጠጅ ቤት ጌሾ ሽታ ወይም እንቡላ በሽተተኝ ቁጥር ያ የመከራ ቀን ውል እያለ ያንገሸግሸኛል። ለጥ ይበሉ ጠጅ ቤትማ ሳይኑም አስጠላኝ።

ቀስ በቀስ ከጠጅ ቤቶች ጋር የነበረኝን ቅርርብ እየጠላሁት መጣሁ። በተለይ ቢጫ ጥላ የሚያንገፈብበት ጌሾ በሩ ላይ የሚሰጣ ከሆነ ያንገሸግሸኛል።

ያ ስሜት የለውጥ ፍላጎት የቀሰቀሰው ባይሆንም በህይወቴ ላይ ለውጥ አስከትሏል። ከነ አተሮ ይልቅ እነ መቱን፣ እነ ግንቦን፣ እነ ዮሴፍ ጢሪሪን እንድቀርብ አድርጎኛል። እዚህ ጓደኝነት ውስጥ ፀቡና ፍቅሩ የሚመነጨው ከእግር ኳስ ጋር በተያያዘ ብቻ ነበር።

አሁን ላይ ሳስሁት እኔ ሁለቱም የልጅነት ምዕራፎች ከትዝታ ያለፈ የህይወት ተፅዕኖ አላሳረፉብኝም። ጠጪም ሆነ እግር ኳስ ተጫዋች አልሆንኩም። ያም ቢሆን ፍፁም ነፃ ነኝ ማለት አልችልም። ቁጭት አለብኝ። ባለፈው መንግሥት ኳስ ያሳደድኩበት ሜዳ ብዙ የወንበሮች እንጀት የሚጠማዘዝበት ሆድ ያለው መሰብሰቢያ አዳራሽ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኗል። የአሁኑ መንግሥት ደግሞ የአራት ኪሎን ጠጅ ቤቶች አንዱንም ለወሬ ነጋሪ ሳያስቀር አውድሟቸዋል። ተመንጥረው ጠፍተዋል። ታሪኮቻቸው ብቻ በእኛና በመሰሎቹ ልብ ላይ በደብዛዛው ይንቀዋለላሉ። ሻምበል ባሻ፣ ቀኝጌታ፣ ዶር፣ አማርያ፣ ሐቻ፣ ኤርፎርስ፣ እንጉሬ መልቲ፣ ጆጆ ገ፣ ይገባዋል፣ ሰጥ ይበሉ፣ ወለተማሪያም፣ ጀርመን....?፣?፣?፣?፣?....



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሽንድ ለእናቴ

በአማትና ምራት መጣቆስ ቤታችን ወገግ ያለ የነገር እሣት ተቀጣጥሎባት ደረስኩ። እናቴ ከታላቅ ወንድሜ ሚስት ጋር የነገር እሳት እየተጫጫረች የቻለችውን ያህል ታቀጣጥላለች።

አንድ ያረረ ድስት ይዛ ከጓዳ የወጣችው እናቴ እየጨሰ መሬት ላይ ጣለችው። ድስቱ የወፍ ጉጆ የመሰለ ነገር ውስጡ እየጤሰ በቂጡ ጠርዝ ተሽከርክሮ እስኪደላደል "ከ ረ ረ ረ ረ ረ " የሚል ረባሽ ድምፅ አሰተጋባ።

"እዬ እዬ መከረሚያህ ነው የሚያሳስበኝ" አለች ጉጉት መስሎ የተቀመጠው ወንድሜን እያየች "እንዴት ያለ ትዳር ይዘህ ባጀኸው? ኧረ አፈር በሆንኩት! ሴትነት እንዲህ ሆነና አረፈው? ድስት ሲያርም አይሰማሽ አንቺ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"የጣድሽው እኮ አንቺ ነሽ" ትላለች የወንድሜ ሚስት፡፡ እናቱ አጠር ቀጠን ማለቷ የወንድሜን ሚስት የበለጠ አጉልቷታል፡፡ ግርንድስ ነገር ነች፡፡ አካሏ ብቻ ሳይሆን ስሟም ያስደምመኛል፡፡ እንኰዬ ትባላለች፡፡ እንኰዬ፣ እንኰዬ፣ እንኰዬ... ስሟን ስደጋግመው ተረት ተረት ይለኛል፡፡ እንኰዬ የዱር ፍሬ እንደሆነ ተነግሮኛል፡፡ እንዴት ያለ እንደሆን ግን በውል አላውቀውም፡፡ እንኰዬ እና እንኰዬ የተረት ፍሬና የተረት ገጸ ባህሪዎች ናቸው ብዬ ደምድሜያለሁ፡፡

እናቱ እየተውረገረገች ያቀጣጠለችው የነገር እሳት እንዳይጠፋ ጣረች፡፡

"ቢሆንላ! አንቺ አለሽ መስሎኝ ቡናውን ተረጋግቼ ለማከተም ልቤ የረጋው?"

"መለስ ብለሽ አታይውም ኖሯል?" እንኰዬ በፍቅር ጊዜ የጀመረችው አንቺታ በእንዲህ ያለ የፀብ ወቅት የማዋረጃ ሽመል የቆረጠች ስለሚያስመስላት ጣልቃ ለመግባት ይዳዳኛል፡፡

"ይብጭቅሽ! ማጀት ብትገቢ ክብርሽ የሚነካ ሁኖ ነው?"

"ኧረ ስለእግዚአብሔር ጉማዬ" ወንድሜ የተቀበረ አንገቱን እንደ አንቱና መዘዘ

"ገልጃ አንተ ዝም በል" እናቴ ሆን ብላ ወንድሜን ለማናደድ በልጅነት ቅፅል ስሙ ትጠራዋለች፡፡

"ለዚህ ለዚህ ለምን ትጠሩናላችሁ?"

እኔም የሚገርመኝ ይኸው ነው፡፡ የእማትና ምራት መጣቆስ እንደጥዋ ማህበር ተቆጥሮ "መጡብሽ ቅመሱ" ይባባላሉ፡፡ የዛሬ ፀብ ደጋሽ እናቴ በመሆኗ ወንድሜና ሚስቱ ወላጆቼ ቤት ተገኝተዋል፡፡ ነገ ወይም ከነገወዲያ ደግሞ እናቴ ወንድሜ ቤት ሄዳ "ልጆች፣ ምነው ድምጣችሁ ጠፋ?" ትላለች፡፡ ከጥቂት የፍቅር ንግግር በኋላ በፀብ እስከስታ መደነከም ይይዛሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ወንድሜ ብድግ ብሎ የፖሊስ ጃኬቱን መላባበስ ያዘ። የመቆናጠር ያህል ከለበሰ በኋላ ሚስቱን ቁልቁል እያየ "ተነሽ እንሂድላት" አለ።

"ሁዱ ሁዱ" አለች እናቴ ወደጓዳ መለስ እያለች። ቀጣዩ ንግግሯ ምንነቱ ያልለየ ማልጉምጉም ሆኖ ይሰማኛል።

"እንደምን አመሻችሁ" አልኩ ገና እንደመጣሁ ሁሉ። ወንድሜ ገልመጥ ብሎ አይቶኝ ዝም አለ። እንኳንዴ መናገር ያለባትን እንዳላገባደደች እያስታወቀባት ላለመሄድ ዳር ዳር ትላለች።

እናቴ ከጓዳ በጆግ ውኃ ይዛ መጥታ በቀሚ ድስቱ ውስጥ ገለበጠች። ጢሱ የበሰለ እንጀራ ተትጉልጉሎ የመጥፋት ድምፅ አሰማ። የውሃው ፍንጥርጣሪ ወንድሜና ሚስቱ ላይ እንዳደርስ እናቴ መፈለጓ ያስታውቃል። ወንድሜ በንዴት ሲመለከታት "ለሚስትህ አገዝና ደብድበኝ። የቀረህ እሱ ነው" ብላ ጆጉን ይዛ ወደጓዳ ተመለሰች።

ወንድሜ ቱግ አለ። በንግግር ያልታገዘ፣ በመቅበጥበጥ ብቻ የተሞላ ቱግታ።

ጣልቃ ለመግባት ያህል "ምነው? ዛሬ ተረኛ ነህ እንዴ?" አልኩት።

ወንድሜ ንዴቱ ወደ ግርምት እየተለወጠ እራሱን ግራ ቀኝ አማታና "እረ አዳሪስ አይደለሁም፤ አሁን ሁለት ሰዓት ድንገተኛ የመንገድ ላይ ፍተሻ ስላለ..."

"የምን ፍተሻ?"

"የፖሊስ አሰራር የተለመደ ነው። የከተሞችን ህገወጥ ጦር መሣሪያዎች የምናስስበት ድንገተኛ ፍተሻ ነው። ሰርፕራይዝ እንለዋለን።" ወደ ሚስቱ በመዞር "ተነሽ እንሂ" አላት።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ኢትዮ" አለች ወደኳዳ እያየች በመነሳት "ከእንግዲህ ቀብሬ ላይ እንዳትደርሺ፣ ቀብርሽ ላይ አልደርስም" እንኪዶ ይሄንን መቁረጫ ሀሳብ ከአስር ጊዜ በላይ ስትለው ሰምቻለሁ። እናቴ ወደ ወንድሜ ቤት ሳትሄድ ሁለት ቀን ካለፋት በህልም አባብ ትመጣለች። ፊንግ ስል ወንድሜ አይቶኝ የበለጠ ተብሳጨ። የሚስቱን እጅ ይዞ የመቆናጠር ያህል ወጣ።

ወንድሜ ያሳዝነኛል። በእማትና ምራት መታክስ መካከል ቆሞ የሁለቱንም ጥይት እየቃመ ይቆስላል። ለጦርነቱ እሱ ያለውን አስተዋፅኦ ልብ አይለውም። ሁሉም ነገር ያበረደ እየመሰለው ወደ ሚስቱ በማድላት እናቱን ይገስጻል። ችግሩ እዚህ ላይ እንደሆነ አይረዳውም።

ቆሞ ብዬ ሰዓቱን መልከት አደረኩ። አንድ ሰዓት ከሃያ አምስት ይላል። የፍቅረኛዬ የሶስና መምጫ ደርሷል። ከማታ ትምህርቷ ላይ አንድ ክፍለ ጊዜ ቀንሳ እዚህ እንድንገናኝ ተቀጣጥረናል። በእንዲህ ያለ ቀጠሮ ቀን ሶስና ቀይ ፊቷን ገርበብ ባለው በር በኩል ብቅ ታደርግና ሳታንኳኳ ትስልላለች። እናቴ ጓዳ ከሆነች ደስታዋ ነው። ዘው ብላ አንገቴ ላይ ጥምጥም ትላለች። ውርጭ ባነማተረው ከንፈሯ ጥብቅ አድርጋ ትስመኝና አይን አይኔን ታየኛለች። ሁኔታዋ ደስ ቢያሰኘኝም ስሜቱን እየተቆጣጠርኩ አያታለሁ።

"ምን ያኮራሃል?" ትላለች ኩራቱን እንደማትወደው ሁሉ። የበለጠ እኮራለሁ። "ወንዳወንድ ባል ነው የምፈልገው" እንዳላለች የተከፋች ትመስላለች። እናቱን ከተል ብዬ ወደ ጓዳ ለመግባት ከሞከርኩ እንኳን እራሷን መቆጣጠር እየተሳናት ቱግ ትላለች።

"ሴት ይመስል ጓዳ ምን ታደርጋለህ?"

ለእሷ እጩ ባሏ ብሆንም ለእናቴ ልጅ መሆኔን ትዘነጋዋለች። የሴቶች ሚዛን የሚያጋድለው ይሄኔ ነው። ሴት እናት ስትሆን ልጇ



t.me/OLDBOOKSPDF

በዘላለማዊ ልጅነቱ እንዲቀጥል ትሻለች። ሴት ሚስት ስትሆን ደግሞ እናት አሟጭታ ያቆየችውን ወንድነት አነቃቅታ ፍፁም ባል ልታደርገው ትደክማለች። የእማትና ምራት ጦርነት ይሄኔ ይነሳል።

ጭው ያለ ፀጥታ እንደሰፈነ ነው። ለካ ፀጥታ የሚጮኸ ልጅ ሆኗል እያልኩ ዳግም ሰዓቴን አየሁ። ረጅም ጊዜ የመሰለኝ አምስት ደቂቃ ብቻ ሆኖ አገኘሁት። አልፎ አልፎ እናቴ የምትነካቸው ድስቶች፣ ሰሀኖች፣ መከተፊያዎች፣ ማንኪያዎች... ሲንኳኩ ይሰማኛል። እናቴ የምትወደኝ ልጅ ሆኜ በማደጌ የጓዳ ዕቃ ድምፆችን ለይቼ አውቃቸዋለሁ። ለላው ቶርቶ የዝርግ እና የጎድጓዳ ሰሀን ድምፅ ለይቼ አውቃለሁ። የማንኪያና የሸክላ እንዲሁ። የትልቅና የትንሽ ድስት... ይሄንን ሰስና ብታውቅ ምን እንደሚሰማት ይገባኛል። ያስመችኝ አይነት ወንድ እንዳልሆንኩ ታረጋግጣለች።

ሰዓቴን መልከት አድርጌ ገና እንደሆነ ሳረጋግጥ ተነስቼ ወደ ጓዳ ዘው አልኩ። ዜሮ ሻማ አምፖሏ ብርሃን ያቆረች የደሃ እንባ መስላለች። ያፈከፈከው ግድግዳ ላይ የተለያዩ የማዕድ ቤት ዕቃዎች ተሰቅለዋል። የእናቴ ሽቦ አልጋ የራስጌና የግርጌ ብረቱ ፍርግርግ የእስር ቤት በር መስሎ ደብዝዞ ይታያል። እናቴ እየተንጐዳጐደች ነው። የጋለ ብረት ምጣድ ላይ ያረፈ ሊጥ ድምፅ ለጆሮዬ፣ ሽታው ለአፍንጫዬ ደረሰኝ። ደግሞ ቂጣው የጤፍ ዱቄት መሆኑን ጭምር ለይቻለሁ።

"መጣህ አለሜ" አለችኝ ፊቷን ሳትመልስ። የቀድሞው ናር ናር ማለቷ ጠፍቶ ድምጿ ውስጥ መረጋጋት ረብቧል።

መልስ ሳልሰጣት ተጠጋኋት። እንደምመጣ ስለምታውቅ ለእኔው እንደምታዘጋጅ ገብቶኛል። እናቴን በልጅነት የምከሳት ትርክምክም የጓዳ መብል ሰርታልኝ አሱን ጉረስ ጉረስ ሳደርግ ነው። ቂጣ፣ ገንፎ፣ ቆሎ፣ አነባበሮ፣ ሬሚጦ...



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሪሚጦ ወንድ አልወድም" ትላለች ሶስና።

"ገልጆ ክደ?" አለች እናቴ፣ ባደረገችው የተፀፀተች መሆኑን በሚያሳብቅ ድምፀት። ዝም ብዬ አፍንጫዬንና ጆሮዬን እከተላለሁ። እናቴ እንጀራ ለመጋገር እንደተሰናዳች ያስታውቃል። ትኩስ እብሲት የገባበት ሊጥ ይሸተኛል። የት እንዳለ ባይታየኝም በሽታው ለይቼዋለሁ። የአልጋዋ መጋረጃ ወደ ግድግዳው ተሰብስቦ ገመድ ላይ የመሰብ ጉዝጓዝ ላስቲክ ተቋጥሮ ተንጠልጥሏል። ላስቲኩ ደንገዝገዝ ባለው የአምፖል ብርሃን ሲመለከቱት ሲነጋ ያሰበ የሰማይ ሆድ ይመስላል። የልጅነት አለሚ እዚች ጓዳ ውስጥ የምትከናወን ናትና ሁኔታውን እወደዋለሁ።

ሶሲ ዘሆን ሰበዘ ቀድማ ብትመጣ የሚል ስጋት ሰቅዞ ስለያዘኝ ወደ ሳሎን ተመለስኩ። አዳም ክንነት ሲባረር'ንኳ የእኔን ያህል መነጠል አልተሰማውም ይሆናል። የእናቴን ልጅነት ይሄን ያህል ብወደውም አሁን ያለሁበት ሁኔታ ላይ ጥላሎቱን እንዳያሳርፍ መጠንቀቅ ይገባኛል። የወንድሜ ችግር ይሄ ነው። መርምሬ ደርሼበታለሁ። ስለ እማትና ምራት የሚያትት ዳጉስ ያለ መፅሐፍ ለማዘጋጀት የሚያስችል ዕውቀት አለኝ።

የወንድ ልጅ ህይወት ባለ አራት ተቃራኒ ግድግዳዎች ነው። ግድግዳዎቹም እናት፣ ሚስት፣ ሴት ልጅና እህት ናቸው። ያደለው ወይም ያወቀበት ወንድ እነዚህን ሳጋ፣ ማገር፣ ቱቫ፣ ልጥፍ፣ ልስን... የማይሉ ግድግዳዎቹ ላይ ጣሪያ መክደን ብቻ ባለ ጎጆ ያደርገዋል።

እንግዲህ ወንድ ልጅ እዚህ "ጎጆ" ውስጥ አራቱን ግድግዳዎች የሚያቻችል የአማካይ ትክል ምሰሶ እንጂ ነዋሪ አይደለም። እናት ወደ ዘላለማዊ ልጅነት ትጎትተዋለች። ወንድ ልጅ በጉተታው አማካይ ሥፍራውን መግት የለበትም። ሚስት ደግሞ የተቀማለት ባል እንዲሆን ወደ እራሷ መሳቧ አያቀርም። አሁንም እዚያው አማካይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ሆኖ የሚሰነቱ አሳሳብ ከመጠን እንዳያልፍ መቋቋም ነው። ሴት ልጅና እህትም በየፊናቸው ወደ እባትነትና ወንድምነት ይስቡታል "ሐይ!" ሳይባሉ ለአሳሳባቸው በልዝቡ መልስ መስጠት ተገቢ ነው።

የወንድሜ ስህተት እዚህ ላይ ነው። ቀጥ ማለት ሲገባው ከእናቱ ሸሽቶ ወደ ሚስቱ ያዘነበለ "ምሰሶ" ሆነ። የሰላም "ጎጆው" መዋቅሯ ተናግቶ እላዩ ላይ ተደነባች። እናቱና ሚስቱ ድንበር ተጣጥሰዋልና ምንጊዜም ጦርነት ላይ ናቸው። እሱ ደግሞ እነሱ ተኩስ መሀከል። ይሄኔ ሚስቱም ብቻዋን ስትሆን ስለእናቱ ትወጋው ይሆናል።

እኔ እንድም ሦስትም እንደሆንኩ አውቃለሁ። ለእናቴ ልጅ ነኝ። ለሚስቴ ባል፣ ለልጄ ደግሞ አባት! ልጅነቴ ባልነቴን አይሚነውም። አባትነቴን በልጅነቴ አላስደፍርም። ባልነቴንና አባትነቴን ጎን ለጎን አስኬዳለሁ። ለነገሩ ገና ባል አልሆንኩም፤ አልወለድኩም፤ እህትም የለኝም...

ገርበብ እንዳለ በተውኩት በር በኩል የሰሲ ፊት መስስ ብሎ የምሽት ጀንበር መሰለ። ወድቶ እንደተገኘ ዕንቁ ልቤን ተረተረችው። የፊቷ አማካይ መዋቅር አፍንጫዋ ነው። ግራና ቀኝ አይኗን ብቻ ሳይሆን ግንባሯንና አገጯን መሀከል ሆኖ ያዋስናል። የእናቴን አለመኖር ስታረጋግጥ ጡል ብላ በርሳዋን አጠገቤ ጣለች። ድምፅ ላለማሰማት እየተጠነቀቀች ቀርባኝ አቀፈችኝ፤ በብርድ የተርበተበተ ከንፈሯን ከንፈሬ ላይ አስቀምጣ ከመሳም ጋር አወራች።

"እንተ ቤት እንሂድ"

ወንድ ልጅ "ለምን?" የማይላቸው የሴቶች ጥያቄዎች አሉበት። ማንገራገርም ተገቢ አይደለም። በጭንቅላቴ ንቅናቄ እሺ አልኳት። ሁኔታዋ የፈጠረባት ሀፍረት ከብርዱ በልጦ ፊቷን ከመቅዕበት ሲያግመው ይሰማኛል። ፊጥኜ ተነሣሁ። እናቴን ለመሰናበት ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሶሲ ምን ልትሆን ነው? በሚል መልክ ስታየኝ ወደጓዳ የቃጣሁትን እግሬን ቀጣሁ። ፊጥና ወደ ጓዳ እንደ መግባት ካለች በኋላ ደፉ ላይ ወደተቀመጠው ድስት እየት አድርጋ ወደኔ በግርምት ዞረች።

"ምናለ አንሱት እንኳን ብትል"

"ይሄ የእኔ ስራ ነው?" በማለት የልብ ማሞቂያዋን ቃል ጣል አደረኩላት።

ደስ ያላላት ይመስል "ወንዶች ስትባሉ እንደው፤ የእኔም አባት ጀበና እየገነፈለ እያየ ዝም ነው" ድስቱን አንስታ ውሃውን እያንቦጫቦጨች ወደ ጓዳ ገባች። ከእናቴ ጋር ተከታትለው ሲወጡ አፍታም አልቆዩ።

"እሰሜ፤ የኔ፤ አንተ? ትኸዱ እንዴ?" አለች። እናቴ ሶሲን ስታይ አንዳች የሚያሽኮረምማት ነገር አለባት። ይሄ ደግሞ የእኔ አቻችሎ የመያዝ ውጤት እየመሰለኝ ኩራት ቢጤ ይዳስሰኛል።

"ትንሽ የማስጠናት ነገር አለኝ" አልኩ፡ አፌ ላይ እንደመጣ። አባባሌ ተተርጓሚ ነገር እንደሆነ የገባኝ ሶሲ በሐፍረት ፊቷ ሲቀላ ነበር።

"እ? - ነው?" አለች እናቴ።

የሶሲ ሐፍረት የበለጠ ስለጨመረ ወደ ቦርሳዋ ሄዳ መፈታተሽ ያዘች።

"እንግዲያው ደግ" የሹራቧን እጅታ ሰቅሰቅ አድርጋ የዓይን ሽኝት ለማድረግ ተዘጋጀች። ሶሲም ሐፍረቷን በቦርሳ ብርበራ አከናውና ቀና አለች። አከታልፌ ለመውሰድ እጇን አፈፍ አደረኳት።

"ኡፍ እጅህ'ኮ ሲያም። ብረት ነው" እያለች ብትነጫነጭም ለመመንጨቅ አልሞከረችም። እኔም ከማላላት ይልቅ ማጥበቁን



t.me/OLDBOOKSPDF

ገፋሁበት። ሶሲ ደስ የምትሰኘው ይሄኔ ነው። በድርበቡ ሆኜ እናቴን በመስናበት ራት ብዬ የእነሱን እንክ እንክ የበዛበት መሰያየት ማጤን ቀጠልኩ። እናቴ የሶሲን ፊት በእጇ አይበሉባ እየዳሰሰች

"ምነው ከሳሽ? ጠቆርሽ ለበል? አይ እራስሽንማ ጣል ጣል አታርጊው" ትላታለች። እንዲህ ያለው የመተሳሰብና የመፋቀር ምንጩ የእኔ ብልሃት የታከለበት እየያዘ እንደሆነ ይገባኛልና ሳደምጠው ደስ ይለኛል።

እናቴ ሶሲን ሸኝታ ከኋላዋ መልከት አድርጋት ወደ ቤት ገባች። አውቃ እንደሆን አውቃለሁ። ሶሲ ራቅ ካለች በኋላ ጉዳይ እንደረሳ አስመስላ ትጠራኝና የፍቅሯን፥ ሌሊት የምበላውን ትሸጉጥልኛለች። ያ የጤፍ ቂጣ ትዝ አለኝ።

"አንተ የኔ፣ አለሚ?"

ይኸው ጠራችኝ ሶሲን ቆይ ብያት ተመለስኩ። እናቴ መምጣቴን ስታይ ወደ ውስጥ ገባ አለች። ተከተልኳት።

"ሌሊት የምትጉራርሰው አሰናድቼልህስ..." ወደ ጓዳ ገባች። አፍታም ሳትቆይ እሁለት ቦታ የታጠፈ ቂጣ በላስቲክ እየጠቀለለች መጣች።

"በምን እይዘዋለሁ?"

አካባቢዋን ዕቃ እንደሚፈልግ ገልመጥ ገልመጥ ብላ፣

"እንደሁለዜው ወገብህ ላይ ታጠቀዋ" አለችኝ።

ተቀበልኳት። ይሞቃል። እሳቱን መለስ አድርጋ እዚያው ብረት ምጣዱ ላይ ስላቆየችው ደርቋል። ሹራቤን ገለጥ አድርጌ እንደ ሽጉጥ ቀበቶዬ ስር ሸጉጥኩት። ቅድም እንደነገሩ አልክስክሼ የተውኩትን ሠላምታ ጉንጯን በመሣም አካክስኩና ወደ ሶሲ ፈጠንኩ። እናቴ ከኋላዬ ቆማ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

"ደሞ እንዳትረሳ፣ ያንተ ነገር" ትላለች። የእናቴ ማደናገሪያ ነው። ሶሲ ላይ ግራ እጇን ጣል አድርጌ ከእናቴ ቤት አስር ደቂቃ የሚያስኬደውን የቤቱን መንገድ ተያያዝኩት። ቸኩያለሁ፤ ሶሲ ከእሷ ሲመጣ እንዴት ባለ ሁኔታ እንደምታስተናግደኝ አውቃለሁና መጣደፍ ሲያንሰኝ ነው።

የመንገድ መብራት የሌለውን መንደር ከየቤቱ ባፈተለከ ብርሃን እየታገዝን አገባደድነው። ሶሲ በእኔም ድጋፍ ጭለማውን ለመውጣት ወገቤን ያዝ አድርጋ እሳት እንደነካት ሁሉ በፍጥነት ሰብስባ "ምንድነው?" አለችኝ።

"ጉድፈላ" አልኩ በልቤ። ቂጣ መታጠቁን ብታውቅ...

"ጩቤ? ምን ሊያደርግልህ?"

ቀዳዳ ሰጠችኝ "ለማንኛውም፣ መቼም ወንድ ልጅ ሲሆን ሽጉጥ..."

"ያንተም በዛ" በማስመሰል ኩርፊያ ቀደም አለች። በማስመሰል ልምምጥ ኩተል አልኳት።

"ምን መሰለሽ፣ ወንድ ልጅ መውደቂያውን አያውቅም.... እና" አፌ ይሄንን ቢወተውትም" ልቤ የሚያስበው እቤት ስንገባ ቂጣውን ሳታይ እንዴት ከሻጥኩበት አውጥቼ እንደምደብቅ ነው። ከኋላዋ ደርሼ በልምምጥ አቀፍ እንዳደረኳት አውራ መንገዱ ደረስን። ቡና ቤቶች ስራ ጀምረዋል። ቀድመው የጀመሩ ጠጪዎች ቀድመው ለከረው በመለፋደድ ላይ ናቸው። ስለተሻጠው ቂጣ ድብቃ እያምሰለሰልኩ ጣደፍ ጣደፍ ስል አንድ እጅ ደረቴ ላይ ድግፎ አቆመኝ። ደነገጥኩ። ፖሊስ ነበር።

"ፍተሻ ፍተሻ"



t.me/OLDBOOKSPDF

መንገዱን ዘግተው የተደረደሩት ፖሊሶች የድንገተኛ ፍተሻ ላይ ነበሩ። አመዶ ቡን አለ። ሶሲ ደንገርገር ቢላትም ለሴቷ ፖሊስ ቦርሳዋን ከፍታ እያስፈተሸች ነበር። እኔን ለመፈተሽ ፊት ለፊቴ የቆመው ፖሊስ "እጅ ወደ ላይ" ይለኛል።

ወደ ኋላ ለመሮጥ ከጀለኝ። ሶሲ ፍተሻዋን ጨርሳ አልፋ ትጠብቀኛለች። ፈታሹ ፖሊስ ቶሎ ፊትሸኝ ወደ ሌላ ለመዘዋወር ቸኩሏል። ሳልወድ በግድ እጄን አነሳሁ።

ከብብቴ የጀመረው ፍተሻ ወገቤ ላይ ሲደርስ ተደናቀፈና ቆመ።

"ምንድነው? አውጣው!"

ሶሲን በተደናገዘው ብርሃን በኩል አየኋት። ጩቤ በመሰላት ቂጣ መደናገሟ ያስታውቃል።

"ምንድነው? አውጣውኮ ነው የምልህ"

ፖሊሱን "ቂጣ ነው" ልለው ጢጋ ስለው "አትጠጋኝ!" ብሎ አምባረቀ። ከፈታሾቹ ኋላ የነበሩት ሌሎች ፖሊሶች ወደኛ ቀልባቸውን ጣሉ። "አውጣው!"

"አይደለም..."

"አውጣው፤ አውጣው!"

በእኔና በፈታሹ መካከል ነገር መክረሩን ያዩ ፖሊሶች የታጠቁትን ጠብመንጃ ካነገቱበት አውርደው በእጃቸው ያዙ። አንዳንዶቹ አቀባበሉ።

"አውጣው!"

እንዴት ብዬ? ከነቂጣዬ እዚሁ ድፍት እላለሁ እንጂ. ሶሲ ፊት፤ ሬዲዮ የያዙ ፖሊሶች በሚቀባበለው ጠብመንጃ ታጅበው "ቁጥር 11 -



t.me/OLDBOOKSPDF

33" ማለት ጀምረዋል፡፡ "ጊዜአዊ ፍተሻ ኬላ 15 ላይ ችግር አጋጥሟል"

"ጉድ ፈላ! ወይኔ እናቴ!" ሶሲን አየኋት የምትሆነውን አጥታ ሲመቱኝ ለመጮህ ተዘጋጅታለች፡፡ የታጠቁት ፖሊሶች አካባቢውን ከሰው እያጠሩ የቆምንበትን ቦታ አስፉት፡፡ ሶሲ ራት ትብል እንጂ የሚሆነውን እያየች ነው፡፡ ፖሊሱን ጠጋ ብዬ ላስረዳው ስል ጮኸ

"አትጠጋኝ፣ እዛው የቆምክበት ሆነህ አውጣው!"

የሬዲዮኑ ንግግር ቀጥሏል፡፡ "አንድ መሣሪያ የታጠቀ ሰው አልፈተሽም" ብሎናል፡፡ ምን ዓይነት መሣሪያ እንደታጠቀ ገና አልተረጋገጠም"..."

እናቴን መርገም አሰኘኝ፡፡ እሷ ምን ታድርግ፣ ይሄን እያሰላሰልኩ በጭንቀት በመናወዝ ላይ ሳለሁ ልብ ሳልለው በጀርባዬ የዞረ ፖሊስ ዘሎ ተጠመጠመብኝ፡፡ መያዜን ያዩ ፖሊሶች ሁሉ እላዬ ላይ ተከመሩ፡፡ ተረባርበው ጣሉኝ፡፡ እንገቴ፣ እጀ፣ ብብቴ፣ ጭኔ... ሁለመናዬ በጠንካራ እጆች ውስጥ ዋለ፡፡ መተንፈስ ተስኖኝ ስፈራገጥ አንድ እጅ ሸራቤን ገልጦ የታጠኩትን መዠረጠው፡፡ አይኔን እንደጨፈንኩ የሞት ያህል የከበደ ሀሞት መፍሰስ መላ ሰውነቴን ተቆጣጠረው፡፡ ይሁንና ጆሮዬ ከመቼውም በላይ ነቅቶ ያዳምጣል፡፡

መጀመሪያ ሳቅ፣

"ምንድነው? ምንድነው?"

እኔን ከመሬት ጋር አጣብቀው የያዙት ፖሊሶች ሳይቀሩ ጠየቁ፡፡

"ቂጣ"

"ምን?"

"ቂጣ ነው!... ቂጣ ነው!" የሳቅ አጀብ ከበበኝ፡፡ ወዲያው ባለሬዲዮኑ "ሐሎ 11 - 33... ከጊዜአዊ ፍታሻ ኬላ 15 ነው፣ ...



t.me/OLDBOOKSPDF

ጦር መማሪያ ሳይሆን ቂጣ ነው!... አዎ ቂጣ ነው!... ቂጣ ነው!" ገመናዬ ይዘው እንደሰቀቋት ወፍ በሶሲ ጆሮ በኩል አድርጋ ሬዲዮኑን ተጠቅማ ወደ ፖሊስ ጣቢያ፣ በጣቢያው አንቴና ወደ ዓለም፣ ከዓለም በናሳ አማካኝነት ህዋ ውስጥ ስትበር አየኋት። እንዳትያዝ ሆና አፈተለከች። የተኛሁባት እንደ ቅቤ ቀልጬ ሳልነሳ ብቀር...



t.me/OLDBOOKSPDF

# ባሻ ወሌ

**(እውነት ወካይ አጭር ልቦለድ)**

ደርሶ ቁጣ ከሚለው ሰማይ ስር.... ቀበሌዋ ታምሳለች። ግቢዋ የበላው እንደተጣላው ሆድ ይጉረመረማል። እምምምም... ከሚለው ጉርምርምታ በላይ የሚሰማ ፉከራ በቴፕ ተከፍቷል።

ባሻ ወሌ እንደ ላይኛን ቢፒ ድቅቅ ያሉና የተቆላለፉ ጥርሶቻቸውን ከርችመው መዝጋቢውን ለደቂቃ ከተመለከቱት በኋላ "ቂም በቀል ሌላ፣ ሀገር ሌላ" ሲሉ ደነፉበት።

"ባሻ ወሌ፣ የምዝገባ መመዘኛ አለን፣ በመመሪያ መስራትና ቂም በቀል ይለያያ..." አለ መዝጋቢው

"ነው እንጂ - ነው እንጂ። አባትህ ካንዴም ሁለቴ መንገድ በቋለክለኝ እርግጥ ነው በዘዘራዬ አቅምሼዋለሁ። ኧረ እንደውም



t.me/OLDBOOKSPDF

ለምጬ ትቼዋለሁ። ይሄንን ፍ/ቤትም ቀርቤ አልዋሽሁም። ካስ ተብዬም ከሻለሁ።"

ጠረጴዛ ላይ የለበሰው ባንዲራ እየተንበባረቀ የሶስት ቀለም ህብር ፊቱ ላይ የሚጫወተው ወጣት ረጋ እንዳለ መለሰላቸው "ያ ተራ ግጭት ነበር..."

"ተራ ግጭት ቢሆንማ ኖሮ አንድ ዓመት ሙሉ የመንደራችን ሴቶች አያወሩትም ነበር። እኔንም አያዳንቁኝም ነበር።" ሾጠጥ ያለ ራሳቸው ላይ ቂብብ ያለችውን ቡሽ ባርኔጣ እየነቀነቁ በሹሙጥ መለሱለት። "ያም ሆነ ይህ እኔም ቤጋ ነኝ፣ በባንዲራው ለሀገሬ መገዝግበኝ" አሉና አፈጠጡ።

"ስንት ዓመትዎ ነው?" ሲል በአርምሞ ጠየቀ መዝጋቢው።

"ሰላሳ - ሶስት" ጋቢያቸውን ወደ ትከሻቸው ገፋ አደረጉ።

"ጡረታ ወጥተው የለም እንዴ?" ዛሬ የተላጩትን ጺማቸውን አሁን ገና ልብ አለው።

"ስለማልታገስ ጠላት ይበዛብኛል ለዚህ ነው ያለዕድሜዬ..."

"ባሻ ወሌ ያም ሆነ ይህ ከ25 ዓመት በላይ መዝግበ አልተባልንም።"

"ይቺ ናት በቀል! የማርዬ ልጅ ተበቀልከኝ። ጊዜ ጠብቀህ ተበቀልከኝ። ሀገሬን እንደምወድ እያወክ በዚህ ይጨክናል? ኧረ ተው! ኧረ ተው!"

"በቀል አይደለም መመሪያ ነው።"

"በቀል መሆኗን መች አጥቼ! በቀል ነው። ስማኝ ደንቆሮው!" አሉና የተቆለፈ ጥርሳቸውን ፈታ አድርገው ቀጠሉ። "ስማኝ ደንቆሮዬ፣ ጥንትም ቢሆን የጦር ነጋሪት ሲጎስም የሚባለው 'ጉልበት ያለህ በጉልበትህ፣ ጉልበት የሌለህ በጠሉትህ እርዳኝ ነው። ስለዚህ



t.me/OLDBOOKSPDF

አንተ እዚህ ተገኝረህ ዕድሜህ በልቁል አልተለቀም በማለትህ ሳይሆን እችላለሁ ያለ ሄዶ ይሞጋል፣ አልችልም ያለ ይጠልያል። ይሄ ያባት አደሩ ደንብ ነው። እኔ ወሌ ደሞ ካናሳ ወጣት አልተናነስም! ብቻ ተበቅለኸኛል ይሁን..." ድንገት ግልፍ ብሏቸው "ደሞ አለትህም፣ የበላይህን አናግራለሁ..." ብለው እየተቆናጠሩ ፊት ለፊት ወዳለው አግዳሚ ወንበር አቀኑ - ቱማ።

መዝጋቢው ምዝገባውን ቀጥሏል...

...አንድ አስር ወጣት በሰላም እንደመዘገበ ጋሙዳው መጣ። ጋሙዳው ባልተስማማበት ነገር ላይ "እምቢ" ከማለት ይልቅ አንድ በጢ ማሳረፍ ይቀናዋል። ከመዝጋቢው ፊት ለፊት ተቀምጦ ግንድ እጁን ጠረጴዛው ላይ አሳረፈ። "መዝግቢና ያራዳ ልጅ" አለ ልምጥጥ ባዘለ አነጋገር። በአብዛኛው መመዘኛ ተሟልቶ የተገኘው ጋሙዳ ባንዷ ላይ ጎደለ...

"መመሪያው ከ10ኛ ክፍል በላይ ይላል። አንተ ደግሞ 3ኛ ነኝ እያልክ ነው ስለዚህ..."

"ስለዚህ ምን?" አለ ጋሙዳው

"ስለዚህማ ልትመዘገብ አትችልም!"

"ፍሬንድ፣ ውጊያው በእንግሊዘኛ ነው እንዴ?" ሲል አፈጠጠ። "ለዚህ ለዚህማ እንግሊዛዊ መመዝገቡ አይቀልም?" በሱም ፊት ላይ የባንዲራው ሶስት ህብር ቀለም ይጫወታል። "ነው ወይስ..."

"ጋሙዳው፣ በአንድ ነገር እንስማማ። አይሆንም ያልኩህን ቀይሬ ልመዝግብህ አልችልም። ቅር ያለህ ካለ ሊቀመንበሩ ሲመጣ አነጋግረው" ብሎ ፊት ለፊቱ ያለውን አግዳሚ ወንበር አሳየው።

"ቀላል እናግረው!" ብሎ ባሻ ወሌ ጎን ቁጭ አለ። ባሻ ወሌ ድንገት -

"እሱንም?" ሲሉ አምባረቁ። "እሱን የመሰለ ኛርግና? ብሶባችኋላ!"



t.me/OLDBOOKSPDF

ምዝገባውን ቀጠለ - መዝጋቢው::

...ቀጠን ብሎ ዘለግ ያለው ቢሆንኝ መጣ:: እግር ኳስ ሲጫወት ነው አሉ ወድቆ ግራ እግሩ ተሰብሯል:: በዚች እግሩ የተነሳ ከ6 ወር በላይ አልጋ ላይ ከርሟል:: በኂላ ድኖ ቢነሳም ይቺ እግሩ ወደጎን ገደድ ብላ በማጠሯ ታስነክሰዋለች::

"ቢሆንኝ አንተ አትችልም" አለው መዝጋቢው

"ለምን?"

የሚለው እንዳያስከፋው ቃላት መረጣ ላይ ጊዜ አጠፋ "ያው እንዳየሁው ዕድሜህ 24 ነው... ጥሩ፣ በትምህርትም 12ኛን ጨርሰሃል፣ ይሄም ጥሩ፣ ግን... ግን አንድ እግርህ... ትንሽ ቀረት ይላል..." በምጥ ተነፈሰው::

"በአውቶቡስ ከኬድኩ እኩል እደርሳለሁ" አለና ቀጠለ:: "ያም ሆነ ይህ እኔ የምፈልገው ደሞዝ አይደለም" - ሀገሬን ከወራሪ መከላከል ነው::"

"ነው፣ ግን..."

"ጦሩ ሁሉ እግረኛ ነው ያለህ ማነው? ታንከኛስ መሆን አልችልም? ቁጭ ብሎ መተኮስ ነው"

"ቢሆንኝ የኔ ኃላፊነት በመመሪያው መሠረት መመዝገብ ብቻ ነው:: ቅር ያሰኘህ ነገር ካለ ሲቀመንበሩ ያብራራልሃል:: እዚያ ጋ..." አግዳሚ ወንበሩን ጠቆመው:: እያልጎመጎመ ሄዶ ከነባሻ ወሌ ጋር ተቀላቀለ...

"አንተንም - ሎጋውን?" ባሻ ወሌ አጋነነ::

መዝጋቢው ሥራውን ቀጥሏል... አንዷት ባልቴት ጠጋ አሉ:: ኩላቸው እንደ መነፅር እጀታ ጆሯቸው አናት ላይ ወጥቷል... "ወ/ሮ አስናቀች ይሄ እርሶን የሚመለከት ምዝገባ አይደለም::"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት?" አሉ "ሴቶቹ ሁሉ ዘምተው ሰራዊቱን እየቀለቡም አይደለም? እኔ ከነሱ በምን እንሻል - ንሺቱ አስናቀች" ቱግ አሉ።

"የሱ ምዝገባ በሴቶች ማህበር በኩል ነው።" አላዳመጡትም...

"እድሜስ ቢሆን ከባሻ ወሌ በልጬ ነው? ይኸው አሳቸው'ኳ..." ጠቆሙ ወደ ባሻ ወሌ የተመዘገቡ መስሏቸው። የባሻ ወሌ ዚፕ ጥርስ ከርችም አለ...

"ሴትዮ እራስሽን ችለሽ ሞማች!" አሉ ባሻ። "እኔ ላይ ምን አንጠላጠለሽ?"

"ቢሆንም እርሶ ተመዝግበው..." ተነቀነቁ...

"የራስሽ ጉዳይ!"

"እርሶም የራሶ ጉዳይ" ግቢው ተብጠበጠ።

በዚህ መሃል የቀበሌው ሊቀመንበር ከቅስቀሳ መመለሱ ነበር። ውጥረቱ በመከራ ረገብ አለና ወደ ቁምነገሩ ተገባ..

"...የሀገራችን ጥቂት ክፍል በጠላት በመወረሩ ምክንያት የቀረበውን ጥሪ ተቀብላችሁ ለመመዝገብ በመምጣታችሁ እናመሰግናለን..." ሊቀመንበሩን ባሻ አቋረጡት

"መች እንደ ሀሳባችን ሆነና!"

"ቆይ'ንጂ" አለ ሊቀመንበሩ "እንደማመጥ" ጉሮሮውን ጠራርጎ ቀጠለ... "ሀገርን ከጠላት መከላከል የዜግነት መብት ቢሆንም ሁሉም ዜጋ ደግሞ ሀገሩን የሚከላከለው በጦር ግንባር ላይ በመፋለም ብቻ ነው ማለት አይደለም።"

"ጉድ ኮ ነው!" አሉ ባሻ። "እሱማ በጠሎትም ይቻላል፣ ግን..."

በተራው አቋረጣቸው... "ስለዚህ እናንተ ምንም'ኳ በግንባር ወራሪ ጠላትን ለመፋለም በፈቃዳችሁ ብትመጡም የምዝገባ



t.me/OLDBOOKSPDF

መመዘኛው እናንተን ስለማይጠቅስ ትግላችሁን በደጀንነት እንድትቀጥሉ ነው የሚፈለገው..."

"አንድ ጥያቄ!" አሉ ባሻ፡፡ "መቼም ላይም ተጠግ ታች አልቻልንም፡፡ ግን ብረት ስጡን አንልም፤ ቀለብ ስፈሩልንም አይወጣንም፡፡ ብቻ የራሳችንን ዱላና ቀለብ ይዘን የሠራዊታችን ፋኖ እንድንሆን ፍቀዱልን፡፡ ከቀናን ከጠላት ብረት እንነጥቃለን፤ ካልሆነም ዱላውን እንደጨበጠ መሞት የፋኖ ወጉ ነው"...

የመሰሎቻቸውን ድጋፍ በጭብጨባ አገኙ፡፡ ጭብጨባው ያቋረጠው የሊቀመንበሩ ድምፅ ነበር...

"ባሻ" አለ "ለሀገርዎ የሚጠቅመው ዱላ ይዘው ግንባር በመሰለፍ አላስፈላጊ መስዋዕትነት መክፈል አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ እርስዎ እዚህ ጠንካራ ደጀንነትዎን በማረጋገጥ የሚወዷት ሀገርዎን መጥቀም ይችላሉ፡፡"

"የማይሆነውን!" አሉ ባሻ ጥርሳቸውን ጠርቅመው፡፡ ፊታቸው ላይ ያወረዛው ልምምጥ መጠጠ "ቁርጡን ልንገራችሁና ጎረቤቶቼን ተሰናብቼ በድል ተመለስ ብለውኝ ነው የመጣሁት፡፡ የትኛውን የድል ብስራት ይዤ ነው የምመለሰው? አልመለስም!"

"ባሻ፣ ጀግንነት በመዋጋት ብቻ አይገለፅም፡፡ ፈቃደኛ ሆነው..."

"በቃ! አልኩ - አልኩ" አሉና ረጃጅም እጆቻቸውን እያወነጫጨፉ "ለመሆኑ በሀገር ላይ አመሳሶ ምን አመጣው?"

"ባሻ፣ እነሱ የገባቸው ይመስለኛል" ብሎ ወደ ተቀሩት ተሚጋቾች ጠቆመ፡፡ "ጠላትን በግንባርና በደጀንነት ብቻ አይደለም፡፡ ለሀገራችን የሚጠቅሙ መሰል መመሪያዎችንም ባግባቡ በመተግበር መሆን ይገባዋል፡፡"

ባሻ የነገሩ ክብደት ጠልቶ የተሰማቸው መሰሉ፡፡ ወዲህ ደግሞ ግንባር ሄደው ለሀገራቸው አጥር የመሆን ከፍተኛ ምኞት



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዘርክኳቸዋል "ቢሆንም…" አሉ ባለመሸነፍ ያህል "ቢሆንም ወደ በሳዮቻችሁ ሄጀ እነሱ ይመልሱኝ፡፡ እዚህ ጥርጣሬ አለኝ፡፡ እም ደባ የተሰራብኝ ይመስለኛል፡፡ የኛረ ቱም በተል ቀስቅሶ የማርዬ ልጅ…" ተነስተው ወደ በሩ ሲያመሩ ጆሮአቸው ከዮት እተጣጫ እንዳመጣው ያላረጋገጡትን ድምፅ ያዳምጡ ነበር፡፡ የሙቀጫ ድውድውቻ… የማበረታቻ ጭብጨባ… "ጉሮ ወሸባዬ ጉሮ ወሸባ፤ ዘማች ድል አድርጎ ሲገባ"… ልባቸው ወደዚያ አቀና…

* * *

ኩዋ - ኩዋ - ኩጥ -፣ ግግም - ግም ግም… ግም-ኳ!

"ጀመረም አይደል?" አሉ ባሻ ወሴ እየተቻኮሉ በመነሳት "ደርሶ ከጀመረንማ እንደለመደው ፈሱን ማስረጨት ነው" ከምሽጉ አጭርነት የተነሳ መቆም ስላልቻሉ እንደተኙ ቀበቶአቸውን አጠበቁ፡፡ ቡሽ ባርኔጣቸውንና ዱላቸውን አፈፍ አድርገው ወጡ…

የቡሬ ግንባር ጸሃይ ገና ከማለዳው መቆጣት ይዛለች፡፡ ቁጣዋ ያሸማቀቃቸው የሚመስሉት ቁጥቋጦዎች መሬት ላይ በደረቱ የሚሳብ ያደፈጠ አነር ይመስላሉ፡፡ ከነሱም ውስጥ አንዳንዶቹ ለሰራዊቱ የታረደውን የከብት ሲጋ ተሸፋፍነው አሸልበዋል፡፡

ኩዋ - ኩዋ - ግግም - ግግም - ግም ፃም ኳ!

"እንዲህ ነው!" ፊታቸውን ተከስ ወዳደመጡበት አቀኑ፡፡ የታያቸው የከሰል ክምር የሚመስለው ድንጋያማ ጉብታ ብቻ ነው፡፡ "ደርቤ!" ሲሉ ተጣሩ አይናቸውን ሳይነቅሉ፡፡ ፈርጣማው ደርቤ ካደረበት የጎረቤት ምሽግ ብቅ አለ፡፡ "ና ወዲህ" አሉት፡፡ "እንግዲህ ጊዜው ደርሷል፤ ሻዕቢያ ጦርነቱን ጀምሯል፡፡ እችላለሁ የምትል ከሆነ እኔ የጠገበ ዱላዬን ይዤ ስቀላቀል አንተ ከበስተኋላዬ አድፍጠህ መከተልና ከተናህ መሳሪያ ከጠላት መንጠቅ ነው፤ ካልሆነም…"

ደርቤ ከወፍራም አጥንት የተዋቀረ ሰፊ ፊቱን በሽሙጥ አተራምሶ "አይ ባሻ ተኩሱ የጦርነትኮ አይደለም ልምምድ ነው" አለ።

"ይህ ሁሉ ጥይት ለልምምድ? አብደዋላ..."

"አይመስለኩቱም'ንጂ፡ ጥባባቢያችን ያሉት ወታደሮች እንደተረጋጉ ናቸው። ጦርነት ቢጀምር..."

"አዎ ልጄ፣ እንደው በሜዳ ልምምድ እያሉ ከሚተኩሱ እላዩ ላይ ቢያንዘንቡበት ምን ችገራቸው። እኛም ሲተራመስ መሀከሉ ገብተን የልባችንን እንሰራ ነበር፣ ወይ ነዶ! ያም ሆነ ይህ ወርም ፈጀ ሁለት ወር ጦርነቱ እንዲሁ መጀመሩ አይቀር፣ ያኔ እንተያያለን..."

ደርቤ ግር በተሰኘ ሁኔቴ እያያቸው "ዛሬ'ኮ ወደ አዲሳባ መንቀሳቀሳችን ነው።" አላቸው።

"እናንተ ተንቀሳቀሱ እኔ እቆያለሁ" አሉ ደቃቅ ጥርሶቻቸውን እንደ ዜጉ አቀላልፈው።

"ባሻ ዕድርዎ ወክሎ የላኩት ሰወገን ጦር በቁሳቁስና በመልዕክት ድጋፉን እንዲያረጋግጡለት ነው..."

"ታዲያ ምናለ፣ እኔ ደሞ ዕድሬን ወክዬ ከሰራዊቱ ጐን በፈቃዶ ተሰለፍኩ። በቃ! ሌላ ምን አጠፋሁ?"

"ትክክል አይመስለኝም" አለና "አስፈላጊ ከሆነ ከዚያው ከአዲስ አበባ በትክክለኛው መንገድ ይመጣሉ'ንጂ ዕድር ወክሎ መጥቶ መቅረት አደራ ማጉደል ነው።"

"ማነው አደራ የሚያጓድል አንተ?" አሉና ጥርሳቸውን እንደ ከረቸሙ አፈጠጡ።

"እኔ ነኝ አንተ አደራ ያጓደልነ? ምነው ልጅ ደርቤ እንተዋወቃለን። ከዚህ ቀደም'ኮ ለቡጢ ግጥሚያ ወደ ባህር ማዶ ብትላክ፣ በዚያው ልትቀር ስትንደፋደፍ ነው የፈጥኝ ታስረህ የመጣኸው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያ ሌላ ጉዳይ ነው፤ ከዚህ ጋር አይገናኝም"

"ቢሆንም ሃገር መክዳት ነው!"

"ባሻ እሱ ያለፈ ነው አያከራክረንም። አሁን ግን እዚሁ መቅረት አይችሉም ነው ርዕሳችን"

"አንተ ምን አግብቶህ ነው ከልካይ የሆንከው?"

"የቡድኑ መሪ ነኝ..."

"ነህ ለካ!" ቀዝቀዝ ብለው ወደ ልምምጡ አደሉ። "ያው ልጅ ደርቤ እኔ ልጅም ሳለሁ ገና ነፍስ ሳላውቅ ሃገሬን አጥብቄ እወድ ነበር እሱ። በሀገሬ የመጣ ሞቴ ነው። እንኳንስ እሷው ተደፍራ ገና ለገና ወዳጆቿ ሃገሮች ተነኩም ሲሉ አልወድ። ለዚህ ነው፤ ኮሪያ ኮንጎ ሳይቀር በፈቃዴ የዘመትኩት። ቃዲያ ዛሬ..."

"ዛሬ አንድ ሰው ሰራዊቱን የሚቀላቀልበት የራሱ ሃይት አለው። ስለዚህ..."

"ልጅ ደርቤ አትጨክን"

"ህገ-ወጥነት ነው!" የፊቱ ጥላ ጋረዳቸው። ባሻ ወሌ ከልምምጣቸው ጋብ ሳይሉ "ይኸውልህ ልጅ ደርቤ፣ ምስጢር ነው'ንጂ እኔ ብቻ ሳልሆን ከኛ ጋር የመጡት ሁሉ ሊቀሩ ምክክር አድርገዋል። ብርቱ'ንኳ ሳትቀር እዚሁ ቀርቼ ሰራዊቱን እቀላቀላለሁ ስትል ውልብ ብሎ'ኛል። ይልቅዬ እንደዜ የቦክስ አሰልጣኝ ሆነህ ባህር ማዶ ይዘሃቸው የሄድከው ቡጢኛች ሁሉ ቀርተው አንተ ብቻህን እንደተመለስከው እንዳይሆን እነሱን ተከታተለህ ወደ መጡበት መልስ። እኔ ግን..."

"የነሱን ግዴለም። እርሶ ግን ካሁን በኋላ ከእይታዬ እንዳይሰወሩ..."

ባሻ ፊታቸው ቀላ፣ ጉንጫቸው ተንቀጠቀጠ፣ ዱላቸውን አጥብቀው እንደያዙ ጥርሳቸውን ከርችመው



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔን እስረኛ ማድረግህ ነው?" ሲሉ አፈጠጡበት

ጠንቀቅ እያለ "ሳይሆን..." ሲል

"ነው'ንጂ" አሉና "በል ወንድ ከሆንክ እንግዲህ ያዘኝ" ብለው የተኩስ ድምጽ ወደሚሰማበት አቅጣጫ ዱላቸውን እየነቀነቁ አቀኑ።

"በህግ - በህጋምላክ - ባሻ! ስነ-ስርዓት ይያዙ..." እያለ ሲከተላቸው አንዳንድ የሰራዊቱ አባላትና የህዝብ ወኪል በመሆን ከመሀል ሃገር የሄዱ ሰዎች መሰባሰብ ጀመሩ።

ባሻ "ካብር አደግህ ጋር አትሰደድ አሉ። ምን ታደርግ አንተ የምታውቀኝ መንደር" እያሉ በነገሯቸው ቀጠሉ...

"ምንድነው... ምንድነው.. ምን አጣላችሁ... ምንድነው?"

"ይሄኔኮ ባህር ማዶ ቢሆን ለመትረት እይኑን ባላሽ ነበር..." ባሻ ጥርሳቸውን ከርችመው ይቆናጠራሉ "በሃገሬ መጥተሃልና ከእንግዲህ እኔና አንተ አጥፊና ጠፊ ነን፤" ዱላቸውን እየነቀነቁ ይዝታሉ። "እ ከከከ... በላ ዜግነቴን ግፈፈኝ!"

"በህግ - ሥነ-ሥርዓት ይያዙ... አስቁሙልኝ"

"ጀግና ከሆንክ አንተ አታስቆመኝም? ያንተ ቡጢና የኔ ሽመል ይለይለት ነበር።"

"ምንድነው?" የሚል ጫን ያለ ድምፅ ተሰማ። ባሻ መቆናጠራቸውን ገታ አድርገው መለስ አሉ። ከዚህ በፊት የሚያውቁት ፊት ነበር። ህዝቡ ለሰራዊቱ የላከውን ቁሳቁስና መልዕክት የተረከባቸው ሻለቃ ጭንቅላቱ ላይ ሽርጥ ጠምጥሟል... ባሻ በመለዮ ለባሽ ደንብ ሰላምታ ሰጥተው ተጠንቅቀው ቆሙ። "ችግር አለ?" ሲል ጠየቃቸው።

"ጌታዬ" ሲሉ በመሽተዳደም ጀመሩ "ለውጊያ አዲስ አይደለሁም። አድሜዬን የፈጀሁት አገሬን ከወራሪ ስከላከል ነው። አሁንም በገዛ ፈቃዴ ሰራዊቱን ተቀላቅያለሁ" አሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዲህ የማይሆነው የሰራዊት አቀላቀሉን ደንብ በመከተል ነው'ንጂ..." እያለ ደርቤ ክሱን ማቅረብ ሲጀምር...

"ተው ልጅ ደርቤ" አሉ ባሻ በልምምጥ ዓይን "ተው፣ ምነው ያኔ ከባህር ማዶ አልሳ፣ ብለው ተጠፍረህ ስትመጣ እንደ ለቀስተኛ እየተመላለስኩ አላፅናናሁህም? አሁን የዚያ ቀውጢ ጊዜ ወዳጅነት ይረሳል?..."

"እሱ ሌላ፣ የዕድር ሃላፊነት ሌላ..." ደርቤ በሰፊ ፊቱ ሙሉ ተቆጣ

"ያኔ እንዴት ቅስምህ እንደተሰበረ ትዝ አይልህም? አሁን እኔ ከዚህ ተመልሼ ሰው የምሆን ይመስልሃል? ልጅ ደርቤ ኧረ ተው..."

"ያም ሆነ ይህ..." አለ ሻለቃው ጉሮሮውን አጽድቶ "ያም ሆነ ይህ እሱ እንዳለው እዚህ በመትረት ሰራዊቱን መቀላቀል አይቻልም..."

"ጌታዬ ያልገባዎት አለ" አሉ ባሻ "ቀለብ ከሰራዊቱ አልጠይቅም፣ ባለቤቴ በየስድስት ወሩ ቀለቤን በሶ እያስፈጨች ልትልክ ውል አስረናል፡፡ ብረትም ስጡኝ አልል፡፡ በጠገበ ሽመሌ ተጠቅሜ ከጠላት መንጠቁን አውቅበታለሁ፡፡ ልጅ ሆኜ ሩኖ ነበርኩ፡፡"

ሻለቃው ፈገግ ብሎ "ጉዳዩ'ኮ ሃገርንም ይመለከታል፡፡ በዓለም ህግ ነው የምንተዳደረው፡፡ ስለዚህ ይሁን ብለን ብናስቀርዎት'ኳ ከሰድሚያዎ መግፋት የተነሳ እንወቀሳለን፡፡ ውትድርና የዕድሜ ገደብ አለው፡፡"

"እነሱስ ያለም ህግ ብለው ይውቀሱን፣ እኛ ብንረታ ማንን ልንወቅስ ነው? ይሄማ አይሆንም! በሃገር ይሉኝታ የለም! ጥንትም እችላለሁ ያለ ተጠራርቶ ጠላትን ድል በማምታት ነው ኢጦቢያን ያቆየናት፡፡ አይሆንም!"

"ወደድንም ጠላንም" በአለም ህግ ነው የምንመራው፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጌታዬ አሁን መጥመም ነው'ንጂ ሰራዊት መሆኑን ማን ልብ ይላል? ጦርነቱ እስኪጀመር ከምሽግ ሳልወጣ አርፌ ቁጭ እላለሁ..."

"እኛም የህሊና ፍርድ አለን። ደግሞም'ኮ እኛን አድርሰዋል - ሃገር የመከላከል ተራው የኛ ነው። በስተርጅና ለዚህ ሃሳብ የዳረጉት በኛ ላይ እምነት ማጣት ያስመስልበታል።"

"እረ በስመአብ በል!"

"ካልሆነ ሃገራችንን ለኛ በአደራ ሰጥተው ሊያከናውኑ ወደማችሉት ተግባር ይመለሱ።"

ባሻ ዚገ ጥርሳቸውን ቆላልፈው "የማይሆነውን!" አሉ። "እንዲህ ማድረግማ ከፅድቅ አውጥቶ ኩነኔ የመጣል ያህል ነው። ሀገሬ ከወራሪዎች ዓይን ቁራኛ ሳትላቀቅ ወደ መሃል ሀገር አልሄድም! እንደ'ትስ ያለ እንቅልፍ ይወስደኛል? አልመለስም!!"

"ባሻ በመጀመሪያ ደረጃ ወታደርን ወታደር የሚያደርገው ስሥነ-ሥርዓት መገዛት ነው። ሥነ-ሥርዓት!" አለ ደርቤ።

ባሻ ግራ ቀኛቸውን አዩ፤ በሰዎች ተከበዋል። ሚሊሻሬ የለበሱ፣ ያለበሱ... በሃሳብ የተዋጡ በመምሰል መሰስ ብለው ከሰዎቹ መካከል ወጡ፤ ከበቡን ብዙም ሳይርቁ የመሮጥ ያህል ጎፍ ጎፍ እያሉ ዘለው ወደ ምሽጉ ገቡ...

"ባሻ ምን እያደረጉ ነው?" አለ ደርቤ፤

"ውርድ ከራሴ ነው - እንዳትጠጋኝ!" ሽመላቸው ብቅ አለች፤

"ስነ-ስርዓት ይውጡ!"

"ስነ-ስርዓት አልወጣም!"



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፌሬጃ

"እንኳን ደህና መጡ - አዲስ ዘመን"

ኪሎ ሜትር ጠቋሚ ሰሌዳ ላይ ቀና ብዬ አነበብኩና "እንኳን ደህና ቆያችሁን - አዲስ አበባ" አልኩ በሆዴ። ከአውቶቡስ ስወርድ እግሬ ከመበዘን ደንዝዞ፣ መቀመጫዬን ደክሞት ነበር። "ሰው እግሩ አያለ በቁጭታ ይመጣል?" የሚል ሀሳብ ውልብ አለብኝና "ዜሮ ሻማ" ፈገግታ አረጨሁ።

ኮተት አላበዛሁም። አንድ የእጅና አንድ የትከሻ ቦርሳዎቼን ጠልጠል አድርጌ ከተማዋን መማተር ያዝኩ። አዲስ ዘመን ከተማ ዘመን መለወጫን የምትጠብቅ ጎታታ ባልቴት መስላ ታየችኝ። እንደ የፊት ጥርስ የተደረደሩት የመንደር ዳር ቤቶቿ ተሰልፈው ከበስተጓላ ያሉትን የገመና ቤቶች ለመሸፈን የሚጣጣሩ ይመስላሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ የአባቴ ትንሽ እህት እዚህ ከተማ አለች። አደግድጉ ትባላለች። ብዙዎቹ ዘመዶቻችን በእሷ ላይ ተሸጋግረው ነው ወደ ትውልድ መንደራቸው የሚያቀኑት። ባለቤቷ አስጨርቂ ያዘው በጋት ተኩል ቁመት ላይ ተሰፍሮ የማያልቅ ተንኮልና ቂም ያሸከመው ሰው ነው ይባላል። በተለይ አባቴን እንደማይወደው ከራሱ ከአባቴ አንደበት ሰምቻለሁ። አደግድጉን ሲጋብቻ በጠየቀ ጊዜ አባቴ "ትምህርቷን ትማር!" ብሎ ከእባቷ በላይ ያገድዳል። "ባሏ'ኳ የተማረ ቢሆን ደግ። ሁለት ያልተማረ ትዳር የተጣመደ እህያ እንደማለት ነው" ማለቱ አስጨርቂ ጆሮ ደረሰ። ኋላ ተሳክቶለት አደግድጉን ካደባ በኋላ አባቴ አባቴጋ ሲሄድ አዲስ ዘመን በመጣ ቁጥር እንደ ቀልድ እያደረገ-

"ሁለት ያልተማረ ጥንድ አህያ ነው እልክ አሉ ጋሼ" ይሰዋል። "እንት ያልተማረ ልበ-ብርሃን አለ መሰለህ?" ጋት ተኩል ቁመቱን ከአባቴ ጋር ለማስተካከል ራቅ ብሎ እያየው። ቢሞት ሰው መቅረብ አይሆንለትም። አገጩ ከሰው አንገቱ እስኪስተካከልለት ወደኋላው ያፈገፍጋል።

በእርግጥም አባቴ ይሄን ዘዬ አድርጎ ይዞታል። "የማይማር ልጅ ያህያ ውርንጭላ እንደማለት ነው" ይለናል እኛ ልጆቹን "ያልተማረ አዛውንት ሠርቶ የደከመ አርጌ አህያ እንደማለት ነው" ይላል ዘመዶቹን።

የአደግድጉን ቤት በምሪት ደረስኩበት። ባሏ በር ላይ ቁጭ ብሎ ለጥልቶ የሚሆን ዛቢያ ይጠርባል። አስተያየቱ ደስ አላለኝም። ሳመል ያህል ጠረባውን ተወት አድርጎ "ቁርጥ አባትክን" አለኝ። "ግባ" ብሎኝ ጥልቆውን ማበጃጀት ያዘ። ለደቂቃዎች ሳልገባ እየሁት። ጠላሁት መሰለ። አጠገቡ የኋላ ግራ እግሩን ሰብሰብ አድርጎ የቆመ አህያ አለ። አባቴ ቢኖር ኖሮ "ያልተማረ ሰው ድንክ አህያ ነው" ያለው ነበር ስል እያሰብኩ ወደ ቤት ዘለቅሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጭልም... ቅዝቅዝ ያለ ቤት፡፡ አደግድጉ አልነበረችም፡፡ እዚህ ቤት ማደር እንደሌለብኝ ወሰንኩ፡፡ ቶሎ የመጣሁበትን ደነማ እያቴን አይቼና ታይቼአቸው ምልስ ወደ አዲስ አበባ፡፡ አይዋ እያቴ፣ አባቴ እየተከላከላቸው የልጅ ልጆቻቸውን ካደግን ወዲህ አላዩንም፡፡ አሁን ትምህርቴን ጨርሼ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ከያዝኩ በኋላ ፈቅዶልኝ በምልክት እንድመጣ ልኮኛል፡፡ "ብቻ አስጨርቂን ተጠንቀቀው፡፡ እኔን አገኘሁ መስሎት!" ብሎኛል፡፡ እና የአስጨርቂ ሁኔታ አካባቢውን ቶሎ ጥዬ እንድሄድ ገፋፋኝ፡፡ ግን የእያቴን ቤት፣ አባቴ ተወልዶ ያደገባት ሲውላልን አላውቃትም፡፡ ለጉብዝ ሰው የግማሽ ሰዓት መንገድ ነው አሉ፡፡

አደግድጉ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን መጣች፡፡ አስር ጊዜ እየተነሣች አስር ጊዜ ሳመችኝ፡፡ "ደምህን አሽትተህ መጣህ?" እያለች አስር ጊዜ አርፋ ሌላ አስር ጊዜ ሳመችኝ፡፡ በመጨረሻ ልሄድ ተነሣሁ፡፡

"ኸ-ገ-ገ-ገ-ገ-ገ" አለች አደግድጉ፡፡ "ኩቴም ዛሬ ነው እምትሄድ? ነገም በሆነልህ?"

"እንዴት?"

"ዛሬን አድረህ፤ ነገን ደግመህ ተዚያ በስቲያ ለቅዳሜ ገበያ የሚመጡ አያይዝህና አይዋ ዘንድ ይጥሉሀል፡፡"

ሁለት ቀን ሙሉ ከአስጨርቂ ጋር ልፋጠጥ? አላደርገውም! አልኩ በልቤ፡፡ "አድርሶኝ የሚመለስ የለም?"

"ኩቴም በእርሻው?"

"ዛልሆነ አቅጣጫውን ጠቁሚኝና..."

"እሄዳለሁ እንዴትል?"

"ምናለበት?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እውጥ ጫካን እንዴት አልፈኸው? አይራራ ወንዝን እንዴት ተሻግረኸው?... ኩሩም ጥጃ!" ስትል ተረተችብኝ።

እኔና አክስቴ ብዙ ተጫጫወቅን። ጨኸቶችን ሲበረክትብት አስጨርቂ የጥልቆ ማበጃጃ መጥረቢያውን ይዞ መጣ። "ምን ይሆናል መስሎሽ ነው እንዲህ የምታገኚው? ይልቅ ሳይመሽበት ይሄድና ከአይዋ ጋር ሲያወጋ ይደር" አላት ኩርማን ሰውነቱን ከኛ ለማስተካከል ራት ብሎ።

"አንተ ደሞ ሰማይ ምድሩ ነህ" አለች አደግድጉ።

"አንቺ ደሞ ምድር ሰማዩ ነሽ" አላት ከግልምጫ ጋር "ማማሽ መንገድ አመራዋለሁ። ወዲያውም ፈረሻ ለትዳሜ ምናምን እንዲጫንበት ለአይዋ ይደርስላቸዋል። እዚህ ሦስት ቀን አስረን ከምናከርምባቸው..."

ፈረሻ ውጭ ታስሮ ያየሁት እሀያ መሆን አለበት።

አስጨርቂ ወንዳወንድ ድምፅ አለው። ይሄ ወንዳወንድ ድምፁ ጭብጦ አካሉ ከወንዳወንድ ልቡ የተዋሰው ይመስላል። አይኔን ጨፍኜ ድምፁን አደመጥኩ። አደግድጉ ስታንገራግር "አይ እንግዲህ ይብቃ!" አላት በድምፁ ገዝፎ። እውነትም አበቃ። ሻንጣዎቼን አንጠለጠልኩ። አስጨርቂ ሻንጣዎቹን ተቀብሎ ውጭ የታሰረው እሀያ ላይ ጫነልኝ። አደግድጉ እየመላለሰች ስማ ተሰናበተችኝ።

እኔ፣ አስጨርቂና ፈረሻ መንገዱን ተያያዝነው። እውጥ ጫካ ጥንት በጥንካሬው ዘመን የወጣለት ሥም የከበደው ይመስላል። አይራራ ወንዝም የተፈራውን ያህል አልሆነም። አስጨርቂ ፈረሴኛ እንዳይመጣብን እያስጠነቀቀንና እየመራን እኔና ፈረሻን ይዞ ወጣ። የአይራራን ጉድባ እንደጨረስን አስጨርቂ ቆም አለና "በል እንግዲህ ፈረሻ ይምራህ" አለኝ። "መንገዱን ጠንቅቆ ያውቀዋል። አሁን አሁን



t.me/OLDBOOKSPDF

እየፈራን እንለቀውም እንጂ ድሮ ጭነት ይዞ ሳይቀር ከኛ አይዋ ዘንድ ብቻውን ይሄዳል" ብሎ ተንጠራርቶ የያዘውን የአህያ ጆሮ እየጎተተ ወደ እኔ አቀረበው፡፡ "መጫኛውን አጥብቀህ ያዝ፡፡" እንደውም ወገብህ ላይ ብታስረው ይሻላል፡፡ በአቋራጭ በአቋራጭ እየመራ ይወስድሃል፡፡ አትስጋ" ሻንጣ ተጭኖ የተረፈውን መጫኛ ወገቤ ላይ ማስር ያዘ፡፡ "ብሎ እንግዲህ ደህና ግቡ፤ ጠዋት አዲስ ዘመን መጪ ፈልጋችሁ ደህና መግባታችሁን ላኩብኝ" ብሎ በሽሙጥ ፈገግታ ከነፈሩን ወደ ግራ አሽራመመው፡፡

አንዲት ነገር ጭንቅላቴ ላይ ደወለች

"ደህና ግቡ!... ደህና ግቡ!... ደህና ግቡ!"

ምንም አማራጭ እንደሌለኝ ገባኝ፡፡ እኔና ፈረሼ በአንድ ላይ ተጠፍረን በጅምላ ተጠርተናል፡፡ "ደህና ግቡ! ደህና ግቡ? ደህና ግቡ? ምን ማለቱ ይሆን?" ግልፅ ነበር፡፡ ላስበው ከምል ይልቅ አላስበውም ማለት ፈልጌ ነው'ንጂ ግልፅ ነበር፡፡ እኔ የመማርን ክብር ለራሴ የምሰጥ የተማርኩት ሰው በአህያ ሰመራ ማየት ይሻል አስጨርቂ! አህያ የማያውቀውን ባለማወቁ አህያ ስከተል ማየት ይፈልጋል፡፡ እናም ተመራሁ... ተከተልኩ፡፡ እየተመራራን ከአይኑ እስከንጠፋ ድረስ አስጨርቂ በኩራት አየን፡፡ አቀረቀርኩ፡፡ የአህያ ኮቴ ያተመውን ዳና የሰው ጫማ ሲወርሰው ተመለከትኩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ዓለማየሁ ገላጋይን "ኒሻን"፣ "አዲስ አድማስ" እና "ፍትህ"ን ጨምሮ በተለያዩ ጋዜጦችና መፅሔቶች ላይ በሚያቀርባቸው መጣጥፎቹ ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪ "አጥቢያ"፣ "ሰብሐት ገብረእግዚአብሔር ህይወትና ክህሎት" እንዲሁም "ቅበላ" የተሰኙ የጥበብ ሥራዎች አሉት። እነሆ አሁን ደግሞ "ኩርቢት" የተሰኘ አዲስ ሥራ ይዞልን መጥቷል።

ወንድሜ ያሳዝነኛል። በእማትና ምራት መታኮስ መካከል ቆሞ የሁለቱንም ጥይት እየቃመ ይቆስላል። ለጦርነቱ እሱ ያለውን አስተዋፅኦ ልብ አይለውም... የወንድ ልጅ ህይወት ባለ አራት ተቃራኒ ግድግዳዎች ነው። ግድግዳዎቹም እናት፣ ሚስት፣ ሴት ልጅና እህት ናቸው። ያደለው ወይም ያወቀበት ወንድ እነዚህን ሳጋ፣ ማገር፣ ቱሻ፣ ልጥፍ፣ ልስን... የማይሉ ግድግዳዎቹ ላይ ጣሪያ መክደን ብቻ ባለ ጎጆ ያደርገዋል። እንግዲህ ወንድ ልጅ እዚህ "ጎጆ" ውስጥ አራቱን ግድግዳዎች የሚያገናኝ የአማካይ ትክል ምሰሶ እንጂ ነዋሪ አይደለም። እናት ወደ በላሰማዊ ልጅነት ትጉትተዋለች። ወንድ ልጅ በጉተታው አማካይ ሥፍራውን መተት የለበትም። ሚስት ደግሞ የተዋጣለት ባል እንዲሆን ወደራሷ መሳብ [illegible] እዚያው አማካይ ላይ ሆኖ የሚስቱ አሳባብ ከመጠ[illegible] ነው። ሴት ልጅና እህትም በየፊናቸው ወደ አባት[illegible] ለአሳሳባቸው በልገዙ መልስ መስጠት ተገዢ ነው።

ልቤና [illegible] እብሬው ብትስቅል፣ ብክሳ፣ ባልበላ፣ ባልጠጣ [illegible] እንዴት? አፍቻዋ ጥሬ እንደ ዓሣ የሰባት [illegible] አታሳስርም? ፍቅር ባለበት በፈረሰ [illegible] አያብብም? ቂጥኝ ውሃ አያፈልቅም? [illegible]...
ይጠራኛል አስታለዋለሁ... [illegible] ላይ ቢኖር... እንደፍልፌል ቤቴ ጉድጓድ ቢሆን... እንደ ጨሌሌ ቅርንጫፍ እንቀ ብያድር... ደንታ አልነበረኝም።

"ሙትዬ" አለ ህውልት .
"ህውልትዬ" አለ ሙት
"ምነው አላምን አልኩ? ፍርሃት፣ ፍርሃት ይለኛል"
"ልብህ ስለሌለ ነዋ፣ ይልቅዬ እኔ ደስ፣ ደስ ይለኛል፣ አመን አመን ይለኛል"
"እንጉልህ ስለሌለ ነዋ፣ እንጉል ፍርሃት ነው"
"እንጉል አለመኖሩ እንዴት ጥሩ ነው ጃል"
"ልብ አለመኖሩስ? ዓለም ነው"
"በፊት አንስማማም ነበር - ሐውልትዬ"
"አሁን ተስማማን ሙትዬ" አለና ጎጠኮሱ እያሉ መንገዳቸውን ተያያዙት
"ሁለት ልብ፣ ሁለት እንጉል። እንዴት መጥፎ ነገር ነው እባክህ፣ ያማል"

t.me/OLDBOOKSPDF